




# ኒኮላይ ፡ ጐጐል ።

# ታራስ ፡ ቡልባ ።


## ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪክ ።


*From the Library of*

*ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃን*

*FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANN*

የፕሮግሬስ ፡ የመጻሕፍት ፡ ማዘጋጃና ፡
ማሳተሚያ ፡ ቤት ።
ሞስኮ ።





# ኒኮላይ ፡ ጎጎል ።

# ታራስ ፡ ቡልባ ።

## ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪክ ።

*From the Library of*

*ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃን*

***FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANN***

የፕሮግሬስ ፡ የመጻሕፍት ፡ ማዘጋጃና ፡
ማሳተሚያ ፡ ቤት ።
ሞስኮ ።

ተርጓሚው ፤ በካፋ ፡ ኃይለ ፡ የሱስ።

Н. В. Гоголь

ТАРАС БУЛЬБА

ПОВЕСТЬ

*На амхарском языке*

Г $\frac{70301 - 585}{014 (01) - 75}$ без объявл.

## ምዕራፍ ፡ አንድ ።

«እስቲ ፡ ዘወር ፡ ብለህ ፡ ልይህ ፡ ልጄ! እንዴት ፡ ያለ ፡ ማስፈራሪያ ፡ መስለሃል! ደግሞ ፡ የምን ፡ የቄስ ፡ ቀሚስ ፡ ነው ፡ የለበስኸው? በተማሪ ፡ ቤት ፡ ሁሉም ፡ የሚለብሱት ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ እንዴ?»

ቡልባ ፤ በኪዬቭ ፡ በሚገኘው ፡ ከፍተኛ ፡ መንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ትምህርታቸውን ፡ ጨርሰው ፡ የተመለሱትን ፡ ሁለት ፡ ወንዶች ፡ ልጆቹን ፡ የተቀበላቸው ፡ እንዲህ ፡ ባሉ ፡ ቃላት ፡ ነው ።

ልጆቹ ፡ ገና ፡ ከፈረሶቻቸው ፡ መውረዳቸው ፡ ነው ። ሁለቱም ፡ ፍርጥም ፡ ያሉና ፡ እንደማናቸውም ፡ ወጣት ፡ ተማሪ ፡ ዓይነ ፡ አፋሮች ፡ ነበሩ ። ወላጃቸው ፡ እንዲህ ፡ ባለ ፡ አኳኋን ፡ ስለተቀበላቸው ፡ እጅግ ፡ ደንግጠው ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ እያዩ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ቆሙ ።

«ቆዩ ፡ እስቲ! እስቲ ፡ ደህና ፡ አድርጌ ፡ ላስተውላችሁ!» ብሎ ፡ እያዟዟረ ፤ «እንዴት ፡ ያለ ፡ ዘርፋፋ ፡ ካፖርት ፡ ነው ፡ የለበሳችሁ! እንዲህ ፡ ያለ ፡ ልብስ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በዓለም ፡ ታይቶም ፡ አይታወቅ ። እስቲ ፡ አንዳችሁ ፡ ትንሽ ፡ ሩጡ! ቀሚሳችሁ ፡ ጠልፎ ፡ ሲያጋድማችሁ ፡ እስቲ ፡ እያለሁ ፡» አለ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ትልቁ ፡ ልጅ ፤ «አትሳቅብን ፡ አባባ ፤ አትሳቅ!» አለው ።

«እዩት ፡ ደግሞ ፡ ኩራቱን! ለመሆኑ ፡ ለምንድን ፡ ነው ፡ የማልስቀው?»

«ምክንያቱም ፤ ምንም ፡ አባቴ ፡ ብትሆን ፤ ከሳቅህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስክር ፡ እደበድብሃለሁ!»

«እንዴት! አንት ፡ የሰይጣን ፡ ልጅ! የገዛ ፡ አባትህን ፡ ትደበድባለህ?» አለና ፡ ቡልባ ፡ በመገረም ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ፈግፈግ ፡ ብሎ ፡ ቆመ ።

«አባቴ ፡ ብትሆንስ? ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ እንዲሰድብኝ ፡ አልፈቅድለትም ።»

«ለመሆኑ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ድብድብ ፡ የምትገጥመኝ? በቡጢ ፡ ነው?»

«በሆነው ፡ ነገር ።»

«ደግ ፤ እንግዲያው ፡ በቡጢ ፡ ይሁን ። በቡጢ ፡ ጠብ ፡ እንዴት ፡ ያለህ ፡ ወንድ ፡ እንደሆንህ ፡ እስቲ ፡ አያለሁ!» አለና ፡ ቡልባ ፡ ከናጁን ፡ ሰበሰበ ።

ከዚያ ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ተለያይተው ፡ የተገናኙት ፡ አባትና ፡ ልጅ ፡ በናፍቆት ፡ ሰላምታ ፡ ፈንታ ፡ ግብ ፡ ግብ ፡ ገጥመው ፡ በቡጢ ፡ ይቀጣቀጡ ፡ ጀመር ።

ቀጭን ፡ የገረጣና ፡ ገራገር ፡ ፊት ፡ ያላቸው ፡ የልጆቹ ፡ እናት ፡ ተወዳጅ ፡ ልጆቻቸውን ፡ ለመሳም ፡ ጊዜ ፡ ሳያገኙ ፡ ቀርተው ፡ እበሩ ፡ ላይ ፡ እንደቆሙ ፤ «እዩልኝ ፡ ሰዎቹ! ሽማግሌው ፡ አበደ! ጨርሶ ፡ አዕምሮውን ፡ ነስቶታል! ከዓመት ፡ በላይ ፡ ተለይተውን ፡ የቆዩት ፡ ልጆቻችን ፡ ገና ፡ ከመግባታቸው ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ መደባደብ ፡ ጀመረ!» ብለው ፡ ጮኹ ።

ቡልባም ፡ ቆም ፡ አለና ፤ «እንዴ ፤ ለመሆኑ ፡ ደህና ፡ ይማታልና! ኧረግ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ግሩም ፡ ተደባዳቢ ፡ ሆኗል! እንዲያውም ፡ ባልሞከረው ፡ ይሻለኝ ፡ ኖሯል ። እንግዲህ ፡ ጥሩ ፡ ኮዛክ ፡ ይወጣዋል ፡ ማለት ፡ ነው! መልካም ፡ ነው ፡ ልጄ ፤ እንኳን ፡ ደህና ፡ መጣህ! አሁን ፡ አባትህን ፡ መሳ



ም ፡ ትችላለህ!» አለና ፡ አባትና ፡ ልጅ ፡ ተቃቅፈው ፡ ተሳሳሙ ። «እንዲያ ፡ ነው ፡ ልጄ! ከኔ ፡ ጋር ፡ እንደተማታኸው ፡ ለሌላም ፡ ሰው ፡ ጠንክረህ ፡ መመከት ፡ አለብህ! ለማንም ፡ ቢሆን ፡ ፊት ፡ አትስጥ! ሆኖም ፡ ልብስህ ፡ እጅግ ፡ የሚያስቅ ፡ ነው ። ደግሞ ፡ ይኸ ፡ የተንዘላዘለው ፡ ገመድ ፡ ምንድን ፡ ነው?» ካለ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ታናሽየው ፡ ልጅ ፡ ዞሮ ፤ «አንተ ፡ ሞኝ ፡ ደግሞ ፡ ምን ፡ ዝም ፡ ብለህ ፡ ትገተራለህ? በል ፡ ና ፡ አንት ፡ የውሻ ፡ ልጅ ፤ አትሞክረኝም ፡ እንዴ?» አለው ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ታናሽየውን ፡ ልጅ ፡ አቅፈው ፡ ይስሙ ፡ የነበሩት ፡ እናትየዋ ፤ «ያንተ ፡ ሃሳብ ፡ ይኸው ፡ ብቻ ፡ ነው! ለመሆኑ ፡ ልጆች ፡ ከገዛ ፡ አባታቸው ፡ ጋር ፡ ሲደባደቡ ፡ ማን ፡ ሰምቶ ፡ ያውቃል? አሁን ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ ጠፋና ፡ ነው? እሱ ፡ ለራሱ ፡ ገና ፡ ሕፃን ፤ ደግሞ ፡ ከሩቅ ፡ መንገድ ፡ መግባቱ ፡ ነው ። ደክሞታል ። ማረፍና ፡ እህል ፡ መቅመስ ፡ ሲገባው ፡ አንተ ፡ ካልተደባደብን ፡ ትለዋለህ!» አሉ ። ይህ ፡ እናቱ ፡ የሚከራከሩለት ፡ ሕፃን ፡ የተባለው ፡ ልጅ ፡ እድሜው ፡ ከሃያ ፡ ዓመት ፡ በላይና ፡ ቁመቱም ፡ ሎጋ ፡ ነበር ። እናትየዋ ፡ ንግግራቸውን ፡ በመቀጠል ፤ «አሁን ፡ ማረፍና ፡ እህል ፡ መቅመስ ፡ ሲገባው ፡ ድብድብ ፡ ካልገጠምን ፡ ትለዋለህ!» ብለው ፡ በቁጣ ፡ ተናገሩ ።

ቡልባም ፡ «ለካ ፡ ሴታ ፡ ሴት ፡ ነህ! እናትህ ፡ የምትልህን ፡ አትስማት ፡ ልጄ ፤ እሷ ፡ ሴት ፡ ናትና ፡ ምንም ፡ አታውቅም ። ለአንተ ፡ የሚገባህ ፡ ኑሮ ፡ ለጥ ፡ ያለው ፡ መስክና ፡ ጥሩ ፡ ፈረስ ፡ ነው! ተመልከት ፡ ይህን ፡ ጐራዴ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የአንተ ፡ እናት ፡ ማለት ። በተማሪ ፡ ቤት ፡ አእምሯችሁን ፡ የሞሉት ፡ መጻሕፍቱ ፡ ፍልስፍናው ፡ ሌላውም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የማይረባ ፡ ነው!» አለና ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ለማተም ፡ የማይገባ ፡ ቃል ፡ ጨምሮ ፡ ተናገረ ። ከዚያም ፡ ቀጠለና ፡ «እንዲያውም ፡ በሚቀጥለው ፡ ሳምንት ፡ ወደ ፡ ዛፖሮዥዬ ፡ ብልካችሁ ፡ ይሻላል ፤ መዘግየት ፡ የለባችሁም ፡ የሚያስፈልጋችሁን ፡

ትምህርት ፡ የምታገኙት ፡ እዚያ ፡ ነው ። ለእናንተ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ማለት ፡ እሱ ፡ ነው ። አእምሮም ፡ ልታገኙ ፡ የምትችሉት ፡ እዚያው ፡ ብቻ ፡ ነው!» አላቸው ።

ባልቴትዋ ፡ እናታቸው ፡ በዓይኖቻቸው ፡ እንባ ፡ ተንቀርዞ ፡ «አንድ ፡ ሳምንት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ በቤታቸው ፡ የሚቆዩት? ልጆቼ ፡ እቤታቸው ፡ በመምጣታቸው ፡ ለመደሰት ፡ እንኳን ፡ ጊዜ ፡ ሳያገኙ ፤ ቤታቸውንም ፡ ለማወቅ ፡ ጊዜ ፡ ሳይበቃቸው ፡ እኔም ፡ አይቼ ፡ ሳልጠግባቸው ፡ ሊሔዱ ፡ ነው?» ብለው ፡ በኃዘን ፡ ጠየቁ ።

«በቃሽ ፡ አትነጫነጭብኝ ፡ አንቺ ፡ ባልቴት! አንድ ፡ ኮዛክ ፡ እድሜውን ፡ ከሴቶች ፡ ጋር ፡ ለማሳለፍ ፡ አልተፈጠረም ፤ በቀሚስሽ ፡ ውስጥ ፡ ሸፍነሽ ፡ እንቁላል ፡ እንደምትፈለፍል ፡ ዶሮ ፡ ልትታቀፊያቸው ፡ ትፈልጊያለሽ ። ይልቅስ ፡ አሁን ፡ ሒጅና ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ ያለሽን ፡ ሁሉ ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ ሥሪልን ። የማር ፡ ብስኩት ፤ ቂጣ ፡ ገንፎ ፡ የምትይውን ፡ ልክስክስ ፡ ምግብ ፡ አንፈልግም ። አንድ ፡ ሙሉ ፡ በግ ፡ ወይም ፡ ፍየል ፤ አርባ ፡ ዓመት ፡ የቆየ ፡ ጠጅ ፡ እንዲሁም ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ ቮድካ ፡ አቅርቢልን ። ደግሞ ፡ በቮድካው ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ ቅመማ ፡ ቅመምሽን ፡ እንዳትጨምሪበት ፤ ንጹህ ፡ ቮድካ ፡ ነው ፡ የምንፈልገው ፡» አለና ፡ ቡልባ ፡ ልጆቹን ፡ ይዞ ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ከሁሉ ፡ ክፍል ፡ ይበልጥ ፡ ወደሚያምረው ፡ ክፍል ፡ አስገባቸው ። በክፍሉ ፡ ውስጥም ፡ እቃ ፡ ሲያደራጁ ፡ የነበሩ ፡ ሁለት ፡ ቆንጃጅት ፡ ገረዶች ፡ ተጣድፈው ፡ ክፍሉን ፡ ጥለው ፡ ወጡ ። የፈሩበትም ፡ ምክንያት ፡ ቁጡና ፡ ጥብቅ ፡ የሆኑት ፡ ወጣት ፡ ጌቶቻቸው ፡ በመምጣታቸው ፡ የተነሳ ፡ ይሆናል ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ወንድ ፡ ሲያዩ ፡ እየጮኹ ፡ መሮጥና ፡ ፊታቸውንም ፡ በቀሚሳቸው ፡ እጅጌ ፡ መጋረድ ፡ የሴቶች ፡ ልማድና ፡ ጠባይ ፡ ስለሆነ ፡ ይህንኑ ፡ ልማድ ፡ ለማክበር ፡ ብለው ፡ ይሆናል ። በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ የቤቱ ፡ እቃ ፡ ዘመኑ ፡ በሚጠይቀው ፡ አኳኋን ፡ የተዘጋጀ ፡



ነበር ። አሁን ፡ ያ ፡ ዘመን ፡ በዘፈንና ፡ በተረት ፡ ብቻ ፡ ተቀርጾ ፡ ነው ፡ የሚገኘው ። እነዚህንም ፡ ዘፈኖችና ፡ ተረቶች ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ኡክሬይን ፡ የግሪክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሮማ ፡ ካቶሊካዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋር ፡ እንዳይተባበር ፡ ባደረገችው ፡ የመጀመርያ ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ይዘፈኑ ፡ እንደነበሩት ፡ አሁን ፡ በኡክሬይን ፡ ውስጥ ፡ የሚዘፍናቸው ፡ የለም ። የክፍሉ ፡ ግድግዳዎችና ፡ ወለል ፡ እንዲሁም ፡ ጣራው ፡ ልክክ ፡ ብለው ፡ በጭቃ ፡ ተለስነዋል ። ጐራዴዎች ፤ የፈረስ ፡ አለንጋዎች ፤ የወፍና ፡ የአሣ ፡ መረቦች ፤ ጠመንጃዎች ፤ በጌጥ ፡ የተሠሩ ፡ የባሩድ ፡ ቀንዶች ፡ ሌላም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የፈረስ ፡ እቃዎች ፡ በግድግዳ ፡ ላይ ፡ ተሰቅለው ፡ ይታያሉ ። የክፍሉ ፡ መስኮቶች ፡ አሁን ፡ በጥንታዊያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ብቻ ፡ እንደሚገኙት ፡ ያሉ ፡ ትንንሽና ፡ በክብ ፡ መስተዋት ፡ የተሠሩ ፡ ናቸው ። የመስኮቶቹና ፡ የበሮቹ ፡ ዳር ፡ ዳር ፡ ቀይ ፡ ቀለም ፡ ተቀብቶአል ። ከአንድ ፡ ጥግ ፡ በኩል ፡ ካለ ፡ ቁም ፡ ሳጥን ፡ ላይ ፡ ከአረንጓዴና ፡ ከሰማያዊ ፡ ቀለማት ፡ ብርጭቆ ፡ የተሠሩ ፡ ማብረጃዎች ፤ የብር ፡ ጽዋዎች ፡ እንዲሁም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መልክ ፡ የተሠሩ ፡ በዚያ ፡ የዘመቻ ፡ ዘመን ፡ እንደተለመደው ፡ ከብዙ ፡ ሰው ፡ ተላልፈው ፡ ከቡልባ ፡ እጅ ፡ የገቡ ፡ የቬኔጺያን ፤ የቱርክና ፡ የቸርካሲያን ፡ ሥራ ፡ የሆኑ ፡ ብርጭቆና ፡ መለኪያዎች ፡ ተደርድረዋል ። በክፍሉ ፡ ጥግ ፡ ጥግ ፡ ዞረው ፡ የገጠሙት ፡ አግዳሚ ፡ ወንበሮች ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ከቅዱሳኑ ፡ ሥዕል ፡ ሥር ፡ ያለው ፡ ትልቅ ፡ ጠረጴዛ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለማት ፡ ከአጌጡ ፡ ጡቦች ፡ የተሠራው ፡ ምድጃ ፡ እኒህ ፡ ሁሉ ፡ በያመቱ ፡ ለእረፍት ፡ ወደቤታቸው ፡ ለሚመጡት ፡ ለሁለቱ ፡ ወጣቶች ፡ የተለመዱ ፡ ነገሮች ፡ ነበሩ ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ለእረፍት ፡ ወደቤታቸው ፡ ሲመጡ ፡ ገና ፡ ፈረሶች ፡ ስላልነበሩዋቸውና ፡ እንዲሁም ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ ፈረስ ፡ መቀመጥ ፡ ከተማሪዎች ፡ ልማድ ፡ ውጭ ፡ ስለነበር ፡ በእግራቸው ፡ ነበር ፡ የሚመጡት ። ለወንድነታቸው ፡ ምልክት ፡ የነበራ

ቸው ፡ ረጅም ፡ ጉንጉን ፡ ጐፈሪያቸው ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ ይህንኑንም ፡ መሣሪያ ፡ የያዘ ፡ ማናቸውም ፡ ኮዛክ ፡ ሊጐትተው ፡ መብት ፡ ነበረው ። ቡልባ ፡ ከፈረሶቹ ፡ መንጋ ፡ ሁለት ፡ ሰንጋዎች ፡ መርጦ ፡ የላከላቸው ፡ ትምህርታቸውን ፡ ጨርሰው ፡ በተመረቁ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

የልጆቹን ፡ መምጣት ፡ ለማክበር ፡ ሲል ፡ ቡልባ ፡ የመቶ ፡ አለቆችና ፡ እንዲሁም ፡ በሱ ፡ ጓድ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ የጦር ፡ ሹማምንት ፡ ጋብዞ ፡ ስለነበር ፡ ከነሱ ፡ ውስጥ ፡ ሁለቱ ፡ ከጥንት ፡ ጓደኛው ፡ ከካፒቴን ፡ ድሚትሮ ፡ ቶቭካች ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ «ተመልከቱ ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ጐልማሶች ፡ እንደሆኑ! በቅርቡ ፡ ወደ ፡ ሴች ፡ ልልካቸው ፡ ነው ፡» አለና ፡ ወዲያው ፡ ልጆቹን ፡ አስተዋወቀ ። እንግዶቹም ፡ ለቡልባና ፡ ለሁለቱ ፡ ወጣቶች ፡ ደስታቸውን ፡ በመግለጽ ፡ የታሰበው ፡ አሳብ ፡ የሚገባ ፡ መሆኑንና ፡ ለአንድ ፡ ወጣት ፡ ጐልማሳም ፡ ከዛፖሮዥያን ፡ ሴች ፡ የበለጠ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የማይገኝ ፡ መሆኑን ፡ ገለጹላቸው ።

«በሉ ፡ ወንድሞቼ ፡ መኮንኖች ፤ በገበታው ፡ በመረጣችሁት ፡ ስፍራ ፡ ተቀመጡ ። አሁን ፡ ልጆቼ ፡ መጀመርያ ፡ ትንሽ ፡ ቮድካ ፡ እንጠጣ!» አለ ፡ ቡልባ ። «የእግዚአብሔር ፡ ፀጋ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ይሁን! ለጤናችሁ ፡ ልጆቼ ፤ ለአንተ ፡ ለአስታፕ ፤ ለአንተም ፡ ለአንድሬይ ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ አህዛብን ፡ ሁሉ ፡ ቱርኮችን ፡ ታታሮችን ፡ እንዲሁም ፡ የእኛን ፡ እምነት ፡ ከተጋፉ ፡ ፖሊሾችን ፡ ጭምር ፡ እንድትመቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ድሉን ፡ ያጐናጽፋችሁ ። በሉ ፡ ጽዋችሁን ፡ አንሱ ፤ ቮድካው ፡ ጥሩ ፡ አይደለም? በላቲን ፡ የቮድካ ፡ ስም ፡ ምንድነው? አየህ ፡ ልጄ ፤ ላቲኖች ፡ ሞኞች ፡ ኖረዋል ። በዓለም ፡ ላይ ፡ እንኳ ፡ ቮድካ ፡ መኖሩን ፡ አያውቁም ። ያ ፡ የላቲን ፡ ጥቅሶች ፡ የጻፈው ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ማን ፡ ነበር? እኔ ፡ መቼም ፡ በትምህርት ፡ ረገድ ፡ እንደነገሩ ፡ ነኝ ፡ ስለዚህ ፡ እርግጠኛ ፡ አይደለሁም ፤ ሆራሲይ ፡ ኖሮአል?»



በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ትልቁ ፡ ልጅ ፡ ኦስታፕ ፡ በልቡ ፡ «ይኼው ፡ ነው ፡ እንግዲህ! ይህ ፡ ብልጥ ፡ ሽማግሌ ፡ ሁሉን ፡ ነገር ፡ ሲያውቅ ፡ ውሸቱን ፡ የማያውቅ ፡ ይመስላል ፡» ብሎ ፡ አሰበ ።

ታራስም ፡ ንግግሩን ፡ ቀጠለና ፡ «እንደሚመስለኝ ፡ አርሂማንደሪቱ ፡ ቮድካ ፡ ለማሽተት ፡ እንኳን ፡ አይፈቅድላችሁም ፡ ነበር ። አሁን ፡ እውነቱን ፡ ንገሩኝ ፡ ልጆቼ ፤ ጀርባችሁንና ፡ አካላታችሁን ፡ ሁሉ ፡ ይገርፏችሁ ፡ አልነበረም? ምናልባትም ፡ ደግሞ ፡ ብዙ ፡ ስታስቸግሩ ፡ በጅራፍ ፡ አልገረፏችሁም ? ይኸውም ፡ በቅዳሜ ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ ሳይወሰን ፡ እሮብንና ፡ ሃሙስንም ፡ ጭምር ፡ አልነበረም?» አላቸው ።

ኦስታፕም ፡ «ያለፈ ፡ ነገር ፡ ማውራት ፡ ፍሬ ፡ የለውም ፤ የሆነው ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሆኖአል ፡» ሲል ፡ አንድሬይ ፡ ተቀበለና ፡ «እስቲ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አሁን ፡ ይሞክር? እስቲ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አሁን ፡ ይንካኝ? አንድ ፡ ታታር ፡ ባይ ፡ የኮዛክ ፡ ጐራዴ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ እንደሆነ ፡ አሳየዋለሁ !» አለ ።

«ጐሽ ፡ ልጄ ፤ ደግ ፡ ተናገርክ ፡ እንዲያውም ፡ ካመጣኸውስ ፡ እኔም ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ መሔዴ ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ ይወቅ ፡ አብሬአችሁ ፡ ነው ፡ የምሔደው ፤ እዚህ ፡ የምቀረው ፡ ምን ፡ ላደርግ ፡ ነው? ስንዴ ፡ ልዘራ? ቤት ፡ ልጠብቅ? በግና ፡ አሳማ ፡ ላግድና ፡ የሚስቴን ፡ ቀሚስ ፡ ልለብስ ፡ ነው? ኧረ ፡ ወዲያ ፡ በሽታ ፡ ያንሳት! እኔ ፡ ኮዛክ ፡ ነኝ ፤ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ኑሮ ፡ ለኔ ፡ አይደለም ፤ ጦርነት ፡ ባይኖርስ ፡ እኔ ፡ ምን ፡ ቸገረኝ? ከእናንተው ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ዛፖሮዥዬ ፡ አብሬ ፡ ሔጄ ፡ እደሰታለሁ ። እግዚአብሔር ፡ ይወቅ ፡ እሔዳለሁ!» አለና ፡ ሽማግሌው ፡ ቡልባ ፡ ወኔው ፡ እየተቀሰቀሰና ፡ እየጋለ ፡ ሔዶ ፡ በመጨረሻ ፡ ብድግ ፡ ብሎ ፡ ቆመና ፡ «እንዲያውም ፡ ነገ ፡ እንሔዳለን! ለምን ፡ እንዘገያለን? እዚህ ፡ የምንጠብቀው ፡ ምን ፡ ጠላት ፡ አለን? ከዚህ ፡ ጐጆ ፡ ምን ፡ ጉዳይ ፡ አለን? እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ለኛ ፡ ምናችን ፡ ናቸው? ይህ ፡ ሁሉ ፡ ቶፋና ፡

ቅራቅንቦ ፡ ምን ፡ ያደርግልናል?» አለና ፡ ማብረጃዎቹንና ፡
የመጠጥ ፡ እቃዎቹን ፡ ሁሉ ፡ እያነሳ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ይከሰ
ክሳቸው ፡ ጀመር ። አሳዛኝዋ ፡ ባልቴት ፡ ሴት ፡ የባላቸውን ፡
ጠባይ ፡ ለምደውት ፡ ስለነበር ፡ በወንበር ፡ ላይ ፡ እንደተቀ
መጡ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ በሃዘን ፡ ይመለከቱት ፡ ነበር ። አንድ
ም ፡ ቃል ፡ ለመተንፈስ ፡ አልደፈሩም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ያን ፡
የጠሉትንና ፡ የፈሩትን ፡ ውሳኔ ፡ ሲሰሙ ፡ እንባቸውን ፡ መግ
ታት ፡ አልቻሉም ፤ ገና ፡ ሳይጠግቡዋቸው ፡ የሚለዩዋቸውን ፡
ልጆቻቸውን ፡ ትክ ፡ ብለው ፡ ሲያስተውሉ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡
ድምጻቸው ፡ ባይሰማ ፡ በዓይናቸውና ፡ በፊታቸው ፡ የሚታ
የውን ፡ ጭንቅና ፡ ሐዘን ፡ ለመግለጽ ፡ የሚያዳግት ፡ ነበር ።

ቡልባ ፡ በራሱ ፡ ሃሳብ ፡ ብቻ ፡ የሚመራ ፡ እጅግ ፡ ደረቅ ፡
ሰው ፡ ነበር ። በአስራ ፡ አምስተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ል
ዑላኖች ፡ ትተውት ፡ የሔዱት ፡ ጥንታዊው ፡ ደቡብ ፡ ሩሲያ ፡
በማይበገሩት ፡ በሞንጐላውያን ፡ ወራሪዎች ፡ ተቃጥሎ ፡ በተ
ደመሰሰበት ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ዘላን ፡ ከነበረው ፡ የኤውሮፓ ፡
ክፍል ፡ መጀመርያ ፡ ከፈለቁት ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ ታራስ ፡
ቡልባ ፡ ነው ። ሰው ፡ ቤት ፡ ንብረቱን ፡ ሲዘረፍ ፡ ደፋር ፡
ይሆናል ። እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ በቤቶቻቸው ፡ አመድ ፡ ላይ ፡
በጠላቶች ፡ ተከበው ፡ ሲቆሙ ፡ ጠላቶቻቸው ፡ ጋር ፡ አዘ
ወትረው ፡ ከመፋጠጣቸው ፡ የተነሳ ፡ ፍርሃት ፡ የሚባለውን ፡
ነገር ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ መኖሩንም ፡ ጨርሰው ፡ ረስተውታል ።
በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ለብዙ ፡ ዘመናት ፡ በሰላማዊነት ፡ ተዳፍኖ ፡
የኖረውን ፡ የስላቮኒክ ፡ መንፈስ ፡ የጦር ፡ ፍላጐት ፡ እንደ
ገና ፡ ሲያጋግለው ፡ ነፃና ፡ አመጸኛ ፡ የሆነው ፡ የኮዛክነት ፡
ጠባይ ፡ ተፈጠረ ። ወንዙ ፤ ሸንተረሩ ፤ ማናቸውም ፡ ምቹ ፡
ስፍራ ፡ ሁሉ ፡ ቁጥራቸውን ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ በማያውቀው ፡
በኮዛኮች ፡ ዘር ፡ ተዘራ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሱልጣኑ ፡ ቁጥራ
ቸውን ፡ ቢጠይቃቸው ፡ ደፋሮቹ ፡ ጀግኖች ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡
መልሰውለታል ፤ «ማን ፡ ያውቃል! በሜዳው ፡ ሁሉ ፡ ተዘር



ተናል ፤ በየአፋፉ ፡ ላይ ፡ ብትመለከት ፡ አንድ ፡ ኮዛክ ፡ አታ
ጣም ፡» ይህ ፡ ከህዝቡ ፡ ልብ ፡ ለመነጨው ፡ እውነተኛ ፡ የሩ
ሲያውያን ፡ ብርታትና ፡ ጥንካሬ ፡ ትክክለኛ ፡ መግለጫ ፡ ሆነ ።
በቀድሞዎቹ ፡ የመሳፍንት ፡ ግዛቶችና ፡ ትናንሽ ፡ ከተሞች ፡
ጥቃቅን ፡ ልዑላን ፡ እርስ ፡ በእርስ ፡ በሚዋጉበትና ፡ ከተሞ
ቻቸውን ፡ በሚቀማሙበት ፡ ቀበሌ ፡ ምትክ ፡ የጋራ ፡ ችግር
ና ፡ በክፉዎቹ ፡ ወራሪዎች ፡ ላይ ፡ የጋራ ፡ ጥላቻ ፡ አንድነት ፡
ያስተሳሰራቸው ፡ ጠንካራ ፡ ሰፈሮች ፡ ተመሰረቱ ። ሁላች
ንም ፡ ከታሪክ ፡ እንደምንረዳው ፡ ኤውሮፓን ፡ እጅግ ፡ ካስ
ፈራት ፡ ከአረመኔዎች ፡ ወረራ ፡ ያዳናት ፡ የነዚህ ፡ ሰዎች ፡
ብርታትና ፡ የማያቋርጥ ፡ ትግላቸው ፡ ነው ። በለቀቁት ፡ ልዑ
ላን ፡ ቦታ ፡ የዚህ ፡ ሰፊ ፡ አገር ፡ የበላይ ፡ ገዢ ፡ የሆኑት ፡ የፖ
ላንድ ፡ ነገሥታት ፡ የኮዛኮቹ ፡ የጦርነት ፡ ወዳድ ፡ መንፈስ
ና ፡ ግድ ፡ የለሽ ፡ አኗኗራቸው ፡ የሚሰጠውን ፡ ጥቅም ፡ ተገን
ዝበው ፡ በመደለል ፡ ሥራቸውን ፡ ያበረታቷቸው ፡ ጀመር ።
በዚህ ፡ ከዋናው ፡ ግዛት ፡ ርቀ ፡ በሚገኘው ፡ አስተዳደራቸው ፡
ከኮዛኮቹ ፡ ከራሳቸው ፡ መካከል ፡ የተመረጡት ፡ ሔትማኖች ፡
ሰፈሮቹን ፡ ሁሉ ፡ በጦር ፡ ክፍል ፡ እያደራጁ ፡ መደቡዋቸ
ው ። ይህ ፡ ቋሚ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ አልነበረም ። ድርጅ
ቱም ፡ የተጨበጠ ፡ አይመስልም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በጦርነት ፡
ሰዓት ፡ እያንዳንዱ ፡ ወንድ ፡ ፈረሱን ፡ ጭኖ ፡ በከተት ፡ ለመ
ሰብሰብና ፡ ከንጉሡ ፡ በሚሰጥ ፡ አንድ ፡ ቼርቮኔትስ ፡ ትእዛ
ዙን ፡ ለማገልገል ፡ ታጥቆና ፡ ቆርጦ ፡ ለመገኘት ፡ ከስምንት ፡
ቀን ፡ ይበልጥ ፡ አይፈጅበትም ፡ ነበር ። በሁለት ፡ ሳምንት ፡
ጊዜ ፡ ውስጥም ፡ ማናቸውም ፡ ቋሚ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡
ሊያደርገው ፡ የማይችል ፡ ድርጅት ፡ ተሰናድቶ ፡ ይገኛል ።
ዘመቻው ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ጦረኛው ፡ ወደ ፡ እርሻው ፤
ወደ ፡ ከብት ፡ እርቢው ፤ ወደ ፡ አሣ ፡ ማጥመዱ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡
ንግዱ ፡ ተሰማርቶ ፡ ነፃ ፡ ኮዛክነቱን ፡ ይቀጥላል ። በጊዜው ፡
የነበሩት ፡ ሌሎች ፡ የውጭ ፡ ሕዝቦች ፡ የየአንዳንዱን ፡ ኮዛክ ፡

የሥራ ፡ ተሰጥኦ ፡ እጅግ ፡ ያደንቁት ፡ ነበር ። አንድ ፡ ኰዛክ ፡ የማያውቀውና ፡ የማይሞክረው ፡ ምንም ፡ ተግባር ፡ አልነበረም ። የወይን ፡ ጠጅ ፡ ይጠምቃል ፤ ሰረገላ ፡ ያንጻል ፤ ባሩድ ፡ ይቀምማል ፡ እንዲሁም ፡ ማናቸውንም ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ከመቻሉም ፡ በላይ ፡ ሲደሰትና ፡ ሲደግስም ፡ ምንም ፡ ወደር ፡ በሌለው ፡ በታወቀው ፡ የሩሲያውያን ፡ ልማድ ፡ ነው ። ዋና ፡ ተግባሩ ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ታጥቆ ፡ ተሰለፎ ፡ ከሆነው ፡ ከተመዘገበው ፡ ኰዛክም ፡ ሌላ ፡ በተፈለገ ፡ ጊዜ ፡ በአስቸኳይ ፡ ፈረሳቸውን ፡ ጭነውና ፡ ታጥቀው ፡ የሚገኙ ፡ ፈቃደኛ ፡ ወታደሮች ፡ ነበሩ ። ለጦር ፡ ክተት ፡ ለማለት ፡ የተፈለገ ፡ እንደሆነ ፡ ኤሳኡሎቹ ፡ በየገበያው ፤ በየመንደሮችና ፡ በየከተሞች ፡ አደባባዮች ፡ በሰረገላ ፡ ላይ ፡ ቆመው ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡ ይጮኹ ፡ ነበር ፤

«ስሙ ፡ እናንት ፡ ጠላ ፡ ጠማቂዎችና ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ጣዮች! የወፈረውን ፡ ገላችሁን ፡ ለዝንቦች ፡ እየመገባችሁ ፡ መቀመጡና ፡ ጠላ ፡ መጥመቁ ፡ በቃችሁ! ኑና ፡ የመኳንንትነት ፡ ዝና ፡ ተጐናጸፉ! እናንተም ፡ አራሾች ፤ ስንዴ ፡ ዘሪዎች ፤ የበግ ፡ እረኞች ፤ እናንት ፡ የሴት ፡ ወዳጆች! ማረሻ ፡ ተከትላችሁ ፡ ስትኩዋትኑ ፡ ቢጫ ፡ ጫማችሁን ፡ ጭቃ ፡ መንከሩ ፡ በቃችሁ ፤ ሴት ፡ ስታባርሩ ፡ የመኳንንትነት ፡ ኃይላችሁን ፡ ማባከኑ ፡ ይበቃል! የኰዛክን ፡ ድል ፡ ለመጐናጸፍ ፡ እነሆ ፡ ሰዓቱ ፡ ደረሰ!»

እነዚህ ፡ ቃላት ፡ ልክ ፡ በደረቀ ፡ እንጨት ፡ ላይ ፡ እንደሚጣል ፡ እሳት ፡ ናቸው ። አራሹ ፡ ማረሻውን ፡ ይሰብራል ፤ መጠጥ ፡ ጠማቂዎች ፡ ደንበጃንና ፡ በርሚሎቻቸውን ፡ ያንካክታሉ ፤ አናጢዎችና ፡ ነጋዴዎች ፡ የሥራ ፡ መሣሪያቸውንና ፡ እቃቸውን ፡ ሁሉ ፡ ይበታትናሉ ። እያንዳንዱ ፡ ወንድ ፡ ፈረሱን ፡ ይጭናል ። ባጭሩ ፡ የሩሲያውያን ፡ ጠባይ ፡ በከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ አሸብርቆና ፡ ጐልቶ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ታየ ፡ ማለት ፡ ነው ።



ታራስ ፡ ቡልባ ፡ ጠንካራና ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በሆነው ፡ ጠባዩ ፡ የታወቀ ፤ የተዋጊነት ፡ መንፈስ ፡ አብሮአቸው ፡ ከተፈጠረው ፡ ከነባር ፡ ኮሎኔሎች ፡ አንዱ ፡ ነበር ። በዚያን ፡ ዘመን ፡ የፖሊሾች ፡ ጠባይ ፡ በሩሲያውያን ፡ መኳንንት ፡ ላይ ፡ መታየት ፡ ጀምሮ ፡ ነበር ። ብዙዎቹ ፡ መኳንንት ፡ የፖሊሾቹን ፡ አለባበስና ፡ የመንደላቀቅ ፡ የምቾች ፡ ኑሮ ፡ ይቀስሙ ፡ ጀመር ። ይህ ፡ ለቡልባ ፡ አላስደሰተውም ። እሱ ፡ የኰዛኮችን ፡ ቀላል ፡ ኑሮ ፡ ስለሚመርጥ ፡ ከጓደኞቹ ፡ መካከል ፡ ወደ ፡ ዋርሶ ፡ ወገን ፡ የሚያዘነብሉትን ፡ ሁሉ ፡ የፖሊሽ ፡ ጌቶቻቸው ፡ ቅምጥሎች ፡ በማለት ፡ ይሸሻቸው ፡ ነበር ። ይህ ፡ የማይደክም ፡ ፍጥረት ፡ ራሱን ፡ ለኦርቶዶክስ ፡ እምነት ፡ ጥበቃ ፡ የተመረጠ ፡ አድርጎ ፡ ይገምት ፡ ነበር ። አንድ ፡ መንደር ፡ በግብር ፡ ሰብሳቢዎቹ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሹማምንት ፡ ተጨቆንን ፡ ያለ ፡ እንደሆን ፡ በፈቃዱ ፡ ሔዶ ፡ በተከታዮቹ ፡ ኰዛኮች ፡ እርዳታ ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ ሕግን ፡ ያስከብራል ። ሰይፍ ፡ የሚመዘዝባቸው ፡ ሶስት ፡ ምክንያቶች ፡ አሉ ፤ የሚል ፡ ሕግ ፡ አወጣ ። አንደኛ ፡ የፖላንድ ፡ ግብር ፡ ሰብሳቢዎች ፡ ለኰዛክ ፡ ሽማግሌዎች ፡ የሚገባቸውን ፡ ክብር ፡ ሳይሰጡ ፡ ከነክንብንባቸው ፡ የቆሙ ፡ እንደሆን ፤ ሁለተኛ ፡ በኦርቶዶክስ ፡ እምነት ፡ ላይ ፡ ዘለፋ ፡ ሲደርስ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ የዘር ፡ ልማድ ፡ ሲሻር ፤ ሶስተኛም ፡ ጠላቶቹ ፡ ሙሰልማን ፡ ወይም ፡ ቱርክ ፡ የሆኑ ፡ እንደሆን ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ ለክርስቲያንነት ፡ ክብር ፡ ሲባል ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ማንሣት ፡ ያስፈልጋል ፡ የሚሉ ፡ ናቸው ።

አሁን ፡ ገና ፡ ሳይሔድ ፡ ጀምሮ ፡ ሴች ፡ ከደረሰ ፡ በኋላ ፡ ሁለቱን ፡ ልጆቹን ፡ ጦር ፡ ከቀመሱት ፡ ጓደኞቹ ፡ ጋር ፡ እንዴት ፡ እንደሚያስተዋውቃቸውና ፡ የልጆቹን ፡ የመጀመሪያ ፡ የጦር ፡ ልምምድም ፡ እንደሚመለከት ፡ በማሰብ ፡ ፈነደቀ ። መጀመሪያ ፡ ለብቻቸው ፡ ሊልካቸው ፡ አስቦ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ትኩስ ፡ ጉልበታቸውንና ፡ ሎጋ ፡ አቋቋማቸውን ፡ ሲመ

ለከት ፡ ጠንካራ ፡ የወንድነት ፡ ውበታቸው ፡ ወኔውን ፡ ቀስቅሶት ፡ ነገውኑ ፡ አብሮአቸው ፡ ሊሔድ ፡ ቆረጠ ። ገና ፡ ከአሁኑ ፡ ትእዛዝ ፡ በመስጠት ፡ የጉዞውን ፡ ድርጅት ፡ ጀምሮ ፡ ለልጆቹ ፡ ፈረሶች ፡ የጦር ፡ መሣሪያና ፡ አብረዋቸው ፡ የሚሔዱ ፡ አሽከሮች ፡ ይመርጥ ፡ ጀመር ። ኤሳኡል ፡ ቶቭካች ፡ ባስፈለገ ፡ ጊዜ ፡ ጦሩን ፡ ወደ ፡ ሴች ፡ እንዲያዘምት ፡ ጥብቅ ፡ ትእዛዝ ፡ ተሰጥቶት ፡ በሰፈሩ ፡ እንደራሴ ፡ ሆኖ ፡ ተወከለ ። ቡልባ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ቮድካው ፡ ራሱ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ ትንሽ ፡ ሞቅ ፡ ቢለው ፡ አንድም ፡ ነገር ፡ አልዘነጋም ። ፈረሶቹ ፡ ውኃ ፡ እንዲጠጡና ፡ ጥሩ ፡ ስንዴ ፡ ፈስሶላቸው ፡ እንዲያድር ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠ ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ ሠርቶ ፡ ሲመለስ ፡ በመጠኑ ፡ ደክሞት ፡ ነበር ።

«በሉ ፡ እንግዲህ ፡ ልጆቼ ፤ አሁን ፡ እንተኛ ። ነገም ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈቃዱ ፡ ሆኖ ፡ እሱ ፡ ያቀደልንን ፡ እንፈጽማለን ። ስለአልጋ ፡ አታስቢ ፡ አሮጊቴ ፤ እውጭ ፡ እንተኛለን ፡» አለ ።

ጨለማው ፡ ገና ፡ መውደቁ ፡ ነው ። ቡልባ ፡ ግን ፡ የሚተኛው ፡ በጊዜ ፡ ስለነበር ፡ በሰፊ ፡ የበግ ፡ ለምድ ፡ ብርድ ፡ ልብስ ፡ ተጠቅሎ ፡ እውጭ ፡ በተዘረጋ ፡ ምንጣፍ ፡ ላይ ፡ ተጋደመ ። ወዲያው ፡ ከመተኛቱም ፡ እንቅልፍ ፡ ወሰደውና ፡ ያንኳርፍ ፡ ጀመር ። የእሱን ፡ ምሳሌ ፡ በመከተል ፡ በሜዳው ፡ ላይ ፡ በየስፍራው ፡ የተጋደሙት ፡ ሁሉ ፡ ማንኳረፍ ፡ ቀጠሉ ። ዘበኝነት ፡ እንዲቆም ፡ ታዞ ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ ወጣቶቹ ፡ ጌቶች ፡ ስለመምጣታቸው ፡ ክብር ፡ ብዙ ፡ ጠጥቶ ፡ ስለነበር ፡ ከሌሎቹ ፡ በፊት ፡ እንቅልፍ ፡ የወሰደው ፡ እሱ ፡ ነው ።

አሳዛኝዋ ፡ እናቲቱ ፡ ብቻ ፡ አልተኙም ። ጐን ፡ ለጐን ፡ በተኙት ፡ ልጆቻቸው ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ አቀርቅረው ፡ በግድ ፡ የለሽነት ፡ የተቆጣጠሩትን ፡ የልጆቹን ፡ ጠጉር ፡ በእጃቸው ፡ እያሻሹና ፡ እያፍታቱ ፡ በእንባቸው ፡ አራሱዋቸው ። በዓይኖቻቸው ፡ በሙሉ ፡ ስሜታቸው ፡ ቢመለከቱዋቸውም ፡ ሊጠግ



ቧቸው ፡ አልቻሉም ። ጡታቸውን ፡ አጥብተው ፡ ታቅፈውና ፡ ተከባክበው ፡ አሳድገዋቸዋል ። አሁን ፡ ግን ፡ አይቶ ፡ ለመጥገብ ፡ እንኳን ፡ ያላቸው ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ አጭር ፡ ነው ። «ልጆቼ ፡ ውድ ፡ ልጆቼ! ምን ፡ ትሆኑ ፡ ይሆን? ምን ፡ እድል ፡ ያጋጥማችሁ ፡ ይሆን?» እያሉ ፡ ሲያለቅሱ ፡ በጊዜው ፡ ውብ ፡ በነበረው ፡ አሁን ፡ ግን ፡ በተጨማደደው ፡ ፊታቸው ፡ እንባቸው ፡ ይወርድ ፡ ነበር ። በእውነትም ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ እንደሌላው ፡ ሴት ፡ ሁሉ ፡ የእኒህም ፡ ሴትዮ ፡ ስቃይ ፡ ከባድ ፡ ነው ። የፍቅር ፡ ጊዜአቸው ፡ በወጣትነት ፡ ዘመናቸው ፡ ለአጭር ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ተወስኖ ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ ኮስታራው ፡ ወዳጃቸው ፡ የሚስቱን ፡ ፍቅር ፡ በጐራዴው ፤ በጦር ፡ ጓደኞቹ ፡ በጦር ፡ ልምምዶቹ ፡ ለወጠው ። በዓመት ፡ ለሁለት ፡ ሶስት ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ ተገናኝተው ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ ይለያያሉ ። አብረው ፡ በሚኖሩበትም ፡ ጊዜ ፡ የሴትየዋ ፡ ኑሮ ፡ ይኼ ፡ ነው ፡ አይባልም ፤ ስድብና ፡ ዱላም ፡ ሳይቀር ፡ ችለው ፡ ሲኖሩ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ የሚያዩት ፡ የፍቅር ፡ ምልክት ፡ የችሮታ ፡ ያህል ፡ ነበር ። የዛፖሮዥዬ ፡ የነፃነት ፡ ኑሮ ፡ ልዩ ፡ መልክ ፡ በሰጣቸው ፡ ሚስት ፡ የለሽ ፡ መኳንንት ፡ መካከል ፡ እኒህ ፡ ሴት ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ልዩ ፡ ፍጥረት ፡ ነበሩ ። ደስታ ፡ ያላገኘው ፡ የወጣትነት ፡ ዘመናቸው ፡ ፈጥኖ ፡ አለፈ ፤ የተዋቡት ፡ ጉንጮቻቸውና ፡ ደረታቸው ፡ በአበባነት ፡ ጊዜያቸው ፡ ሳይሳሙ ፡ ያለጊዜያቸው ፡ ጠውልገው ፡ ተጨማደዱ ። ፍቅራቸው ፤ ስሜታቸው ፤ ማናቸውም ፡ የሴት ፡ ልጅ ፡ የልስላሴ ፡ ተፈጥሮ ፡ ሁሉ ፡ በእናትነት ፡ ፍቅር ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ተመሰረተ ። በልጆቻቸው ፡ ላይ ፡ አቀርቅረው ፡ በፍቅር ፡ ስሜትና ፡ በሃዘን ፡ ተጨበጡ ። ተወዳጅ ፡ ልጆቻቸው ፡ ተነጥለዋቸው ፡ ሊሄዱ ፡ ነው ፤ ምናልባት ፡ ወደፊትም ፡ አይገናኙ ፡ ይሆናል! ማን ፡ ያውቃል ፤ ምናልባት ፡ በመጀመሪያው ፡ ጦርነት ፡ ላይ ፡ ታታሮች ፡ አንገታቸውን ፡ ቆርጠው ፡ እናቲቱ ፡ ሰውነታቸው ፡ የት ፡ እንደወደቀ ፡ እንኳን ፡ ሳያውቁ ፡ ይቀሩ ፡ ይሆናል ፡

ወይም ፡ ጆቢራ ፡ ይቧጨቃቸዋል ። እናቲቱ ፡ ግን ፡ ከልጆቻቸው ፡ ለአንዷት ፡ ጠብታ ፡ ደም ፡ እንኳ ፡ ያላቸውን ፡ ንብረት ፡ ሁሉ ፡ ቢሰጡ ፡ በወደዱ ። ኃይለኛው ፡ እንቅልፍ ፡ የከደናቸውን ፡ የልጆቹን ፡ ዓይኖች ፡ በማልቀስ ፡ እየተመለከቱ ፡ «ወይኔ ፤ ቡልባ ፡ ሲነቃ ፡ የመነሻቸውን ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ እንኳን ፡ እንዲቆይ ፡ ያደርገው ፡ ይሆን? ምናልባት ፡ ነገ ፡ ለመነሣት ፡ ያሰበው ፡ ስለሰከረ ፡ ይሆናል ፡» ብለው ፡ አሰቡ ።

ሌሊቱ ፡ እየገፋ ፡ ሲሄድ ፡ ጨረቃዋ ፡ ደምቃ ፡ ግቢውንና ፡ በአደባባዩ ፡ የተኙትን ፡ ኮዛኮች ፡ ብርሃን ፡ አልብሳቸዋለች ። ሴትየዋ ፡ ግን ፡ ዓይኖቻቸውን ፡ ከተወዳጅ ፡ ልጆቻቸው ፡ ላይ ፡ ሳይለዩ ፡ እንቅልፍም ፡ ሳያስቡ ፡ ራስጌያቸው ፡ እንደተቀመጡ ፡ ናቸው ። ፈረሶቹ ፡ የንጋቱ ፡ መቃረብ ፡ ተሰምቶአቸው ፡ ረግተው ፡ ተጋድመዋል ፤ የዛፎቹ ፡ ጫፍ ፡ ጫፍ ፡ በነፋሱ ፡ ኃይል ፡ መንሾካሾክ ፡ ጀምሮ ፡ ሹክሹክታው ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ከሥር ፡ ወደአሉት ፡ ቅርንጫፎች ፡ ደረሰ ። ሴትየዋም ፡ ምንም ፡ ሳይደክማቸው ፡ ምነው ፡ ሌሊቱ ፡ ማለቂያ ፡ ባልኖረው ፡ ብለው ፡ እየተመኙ ፡ እስኪነጋ ፡ ተቀመጡ ። ከወደ ፡ መስክ ፡ ፈረስ ፡ ሲያሽካካ ፡ ተሰማ ፤ የጋለ ፡ ብረት ፡ የመሰለ ፡ ብርሃንም ፡ በሰማዩ ፡ ላይ ፡ ተፈነጠቀ ።

ቡልባ ፡ በድንገት ፡ ነቃና ፡ ብድግ ፡ ብሎ ፡ ተነሣ ። ባለፈው ፡ ማታ ፡ የሰጠውን ፡ ትዕዛዝ ፡ ሁሉ ፡ በደንብ ፡ አስታወሰ ።

«አሁን ፡ የኔ ፡ ጕልማሶች ፡ እንቅልፍ ፡ ይበቃል! ተነሱ! ፈረሶችን ፡ አጠጡ ፡» አለና ፡ «የታለች ፡ ባልቴትዋ ፡ ሚስቴ? በይ ፡ ፍጠኚ ፡ ባልቴት ፡ ሚስት ፤ የምንበላው ፡ አዘጋጅልን ፤ ረጅም ፡ መንገድ ፡ ነው ፡ የምንሄደው ፡» ብሎ ፡ አዘዘ ። ሁልጊዜ ፡ ሚስቱን ፡ ሲጠራ ፡ ባልቴት ፡ ሚስት ፡ እያለ ፡ ነበር ።

አሳዛኝዋ ፡ ባልቴት ፡ ሴት ፡ የመጨረሻ ፡ ተስፋቸው ፡ ተቆርጦ ፡ በሃዘን ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ገቡ ። እሳቸው ፡ እንባ ፡ እየ



ተናነቃቸው ፡ ቁርስ ፡ ሲያዘጋጁ ፡ ቡልባ ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ትእዛዝ ፡ በመስጠት ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ እየተራወጠ ፡ የልጆቹንም ፡ መሣሪያ ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ መረጠ ። ተማሪዎቹ ፡ ወጣቶች ፡ ወዲያው ፡ ተለወጡ ። ጭቃ ፡ ባጠለቀው ፡ ጫማቸው ፡ ፋንታ ፡ በተረከዛቸው ፡ ላይ ፡ የብር ፡ ጠርዝ ፡ ያላቸው ፡ ቀያይ ፡ የሞሮኮ ፡ ጫማዎች ፡ አደረጉ ። እንደ ፡ ጥቁር ፡ ባሕር ፡ ሰፊ ፡ ሆነው ፡ ሺ ፡ ቦታ ፡ የተጣጠፉት ፡ ሱሪዎቻቸውም ፡ ባለወርቀዘቦ ፡ ሸምቀቅ ፡ ነበሩ ። ከሸምቀቆውም ፡ ጕፍላ ፡ የትንባሆ ፡ ማጤሻና ፡ ሌላም ፡ ይህንን ፡ የመሳሰሉ ፡ ነገሮች ፡ ተንጠልጥለዋል ። እሳት ፡ ከመሰለ ፡ ቀይ ፡ ጨርቅ ፡ የተሠራ ፡ ካዛኪን ፡ ባጌጠ ፡ ጨርቅ ፡ ድግ ፡ ወገባቸው ፡ ላይ ፡ ታብቶ ፡ በውስጡ ፡ ጌጠኛ ፡ የቱርክ ፡ ሽጉጦችና ፡ ጐራዴዎች ፡ ተሸጠዋል ። ብዙ ፡ ጸሐይ ፡ ያልነካው ፡ ፊታቸው ፡ የበለጠ ፡ ተዋበ ። የወጣትነት ፡ ጺማቸው ፡ ጥቁርነትም ፡ ለፊታቸው ፡ የበለጠ ፡ ንጣት ፡ ሰጥቶት ፡ የጕልማሳነት ፡ ጥንካሬና ፡ ጤና ፡ ይታይባቸው ፡ ነበር ። ከጥቁር ፡ የበግ ፡ ለምድ ፡ የተሠራው ፡ በወርቀዘቦ ፡ ያጌጠ ፡ መለዮአቸውን ፡ ሲደፉ ፡ እጅግ ፡ አማረባቸው ። አዬ ፡ ያልታደሉ ፡ እናት! ልጆቻቸውን ፡ እንዲህ ፡ ሆነው ፡ ሲያዩዋቸው ፡ ምንም ፡ ቃል ፡ ሊናገሩ ፡ ስለአልቻሉ ፡ በዓይኖቻቸው ፡ እንባ ፡ ተንቀረዘዘ ።

«ልጆቼ ፤ አሁን ፡ ሁሉም ፡ ተዘጋጅቶአል ፤ ጊዜ ፡ አናጥፋ! ነገር ፡ ግን ፡ መጀመሪያ ፡ የክርስቲያንነት ፡ ልማዳችን ፡ እንደሚጠይቀው ፡ መንገድ ፡ ከመጀመራችን ፡ በፊት ፡ ሁላችንም ፡ ቁጭ ፡ ማለት ፡ አለብን ፡» አለና ፡ ቡልባ ፡ ሲናገር ፡ በአክብሮት ፡ በር ፡ ላይ ፡ ቆመው ፡ የነበሩት ፡ አሽከሮች ፡ እንኳን ፡ ሳይቀሩ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተቀመጠ ።

«በይ ፡ እንግዲህ ፡ ልጆችሽን ፡ መርቂያቸው ። በጀግንነት ፡ እንዲዋጉ ፤ ለክርስቲያንነት ፡ እምነት ፡ እንዲሰለፉና ፡ የመኳንንትነት ፡ ክብራቸውን ፡ እንዲጠብቁ ፤ ይህን ፡ ባያደርጉ ፡ ግን ፡ በምድር ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ምልክት ፡ ሳይ

ተው ፡ እንዲጠፉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጸልይላቸው! በሉ ፡ ልጆቹ ፤ ወደ ፡ እናታችሁ ፡ ቅረቡ ፤ የእናት ፡ ጸሎት ፡ ወንድን ፡ ልጅ ፡ በምድርም ፡ ሆነ ፡ በባህር ፡ ይጠብቀዋል ፡» አለ ፡ ቡልባ ።

እንደ ፡ ማናቸውም ፡ እናት ፡ ደካማ ፡ የሆኑት ፡ ሴትዮ ፡ ልጆቻቸውን ፡ አቅፈው ፡ እያለቀሱ ፡ ሁለት ፡ ትንንሽ ፡ የቅዱሳን ፡ ሥእሎች ፡ በአንገታቸው ፡ ላይ ፡ አንጠለጠሉላቸው ።

«የአምላክ ፡ እናት ፡ ትጠብቃችሁ ፡ … እናታችሁን ፡ አትርሱኝ ፡ ልጆቼ ፡ … ስለሁናቴአችሁም ፡ ወረቀት ፡ ላኩልኝ ፡ … » በማለት ፡ ብቻ ፡ እናቲቱ ፡ ንግግራቸውን ፡ ፈጸሙ ።

«በሉ ፡ እንግዲህ ፡ ልጆቼ ፡ እንነሣ!» አለ ፡ ቡልባ ።

ፈረሶቹ ፡ ተጭነው ፡ በሩ ፡ ላይ ፡ ቆመዋል ። ቡልባ ፡ ጋኔል ፡ በተባለው ፡ ፈረሱ ፡ ላይ ፡ ዘሎ ፡ ሲቀመጥ ፡ እጅግ ፡ ወፍራም ፡ ሰው ፡ ነበርና ፡ ፈረሱ ፡ ክብደቱ ፡ ተሰምቶት ፡ ተቅበጠበጠ ።

እናትዮዋ ፡ ልጆቻቸው ፡ ፈረስ ፡ ላይ ፡ መውጣታቸውን ፡ ሲመለከቱ ፡ አስተያየቱ ፡ ለስለስ ፡ ያለ ፡ ወደመሰላቸው ፡ ወደ ፡ ታናሽየው ፡ ልጅ ፡ ሮጠው ፡ ሄደው ፡ እርካቡን ፡ ያዙና ፡ የኮርቻውን ፡ ቀዳማ ፡ አንቀው ፡ አልለቅ ፡ አሉት ። ወዲያው ፡ ሁለት ፡ ጠብደል ፡ ኮዛኮች ፡ ቀስ ፡ ብለው ፡ አላቀቋቸውና ፡ ተሸክመው ፡ ወደቤት ፡ አስገቡዋቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ወዲያው ፡ መንገደኞቹ ፡ የአጥሩን ፡ በር ፡ ሲወጡ ፡ ሴትዮዋ ፡ እየሮጡ ፡ ተከትለው ፡ ደረሱና ፡ በሚያስደንቅ ፡ ጉልበት ፡ ፈረሱን ፡ አቁመው ፡ አንዱ ፡ ልጃቸው ፡ ላይ ፡ ሲጠመጠሙ ፤ አሁንም ፡ እንደገና ፡ ተይዘው ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ተመለሱ ። ወጣቶቹ ፡ ኮዛኮች ፡ አባታቸውን ፡ በመፍራት ፡ እንባቸውን ፡ ውጠው ፡ ልባቸው ፡ እየተጨነቀ ፡ ጉዞ ፡ ቀጠሉ ። አባትዮውም ፡ እንዳይታወቅበት ፡ ሸፍኖ ፡ ያዘው ፡ እንጂ ፡ ውስጡን ፡ ሐዘን ፡ ተሰምቶት ፡ ነበር ። ቀኑ ፡ ነፋሳማ ፡ ጭው ፡ ያለ ፡ ቀን ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የሜዳው ፡ ሣር ፡ ፈገግ ፡ ብሎ ፡ ያንጸባርቃል ፤



ወፎቹ ፡ ያለስልት ፡ የሚንጫጩ ፡ ይመስላሉ ። ወዲያው ፡ ዘወር ፡ ብለው ፡ ቢመለከቱ ፡ መንደራቸው ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ እንደሰመጠ ፡ ሁሉ ፡ ከምድር ፡ በላይ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የሚታያቸው ፡ ሁለቱ ፡ የቤታቸው ፡ የጢስ ፡ መውጫዎችና ፡ እንዲሁም ፡ በሕፃንነታቸው ፡ እንደ ፡ ጦጣ ፡ ይንጠለጠሉባቸው ፡ የነበሩት ፡ ዛፎች ፡ ጫፍ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በቀር ፡ የሚታየው ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ ድረስ ፡ የተዘረጋው ፡ ለጥ ፡ ያለ ፡ መስክ ፡ ሲሆን ፡ ይህም ፡ መስክ ፡ ጤዛ ፡ ባዘለው ፡ ሣሩ ፡ ላይ ፡ ሲንከባለሉበትና ፡ ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ ሁለቱም ፡ በየበኩላቸው ፡ አንዳንድ ፡ የኮዛክ ፡ ልጃገረድ ፡ ሲጠብቁ ፡ ልጃገረዶቹም ፡ በወጣት ፡ እግራቸው ፡ ሜዳውን ፡ አቋርጠው ፡ ሲሮጡ ፡ ያለፈውን ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ አስታወሳቸው ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ የሚታየው ፡ ብቻውን ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ የቆመው ፡ የውሃ ፡ መሳቢያ ፡ ግመድ ፡ የተንጠለጠለበት ፡ ረጅም ፡ ምሰሶ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ከኋላቸው ፡ የቀረው ፡ ሜዳ ፡ ከሩቅ ፡ ሲመለከቱት ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ እንዳይታይ ፡ ሸፍኖ ፡ የያዘ ፡ ተራራ ፡ ይመስላል ።

ልጅነት ፡ ደህና ፡ ሰንብች ፤ ጨዋታ ፡ ደህና ፡ ሰንብች ፤ ሁሉም ፡ ነገር ፡ ሁሉም ፡ ሰው ፡ ደህና ፡ ሰንብቱ!

## ምዕራፍ ፡ ሁለት ።

ሶስቱም ፡ ፈረሰኞች ፡ በፀጥታ ፡ ይጓዛሉ ። ሽማግሌው ፡ ታራስ ፡ ስለአለፈው ፡ ጊዜው ፡ ያስባል ። ያለፈው ፡ የወጣትነት ፡ ዘመኑ ፡ በዓይኑ ፡ ላይ ፡ ውል ፡ አለ ። ማናቸውም ፡ ኮዛክ ፡ ዕድሜው ፡ ሁሉ ፡ በወጣትነት ፡ ቢፈጸም ፡ ስለሚመኝ ፡ ላለፈው ፡ ለልጅነት ፡ ዘመኑ ፡ ሁልጊዜ ፡ እንዳለቀሰ ፡ ነው ። ቡልባ ፡ ሴች ፡ ሲደርስ ፡ ከቀድሞ ፡ የጦር ፡ ጓደኞቹ ፡ እንግማንን ፡ እንደሚያገኝ ፡ ያስብ ፡ ጀመር ። የሞቱትም ፡ ትዝ ፡ እያሉት ፤ ከነሱም ፡ ውስጥ ፡ ምነው ፡ ቢኖሩ ፡ ኖሮ ፡ የሚላቸውን ፡

አስታወሰ ። በዓይኖቹ ፡ እንባ ፡ ተንቀርዝዞ ፡ ሸበቶ ፡ ራሱ ፡ በሃዘን ፡ አቀረቀረ ።

ልጆቹ ፡ በበኩላቸው ፡ ስለሌላ ፡ ነገር ፡ ያስቡ ፡ ነበር ። የሚያስቡትን ፡ ከመጥቀስ ፡ በፊት ፡ አስቀድሞ ፡ ስለነሱ ፡ መግለጽ ፡ ሳያስፈልግ ፡ አይቀርም ። እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ወጣቶችና ፡ በአሥራ ፡ ሁለት ፡ አመታቸው ፡ ኪዩቨ ፡ ወደሚገኘው ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተላኩ ። የተማሩትን ፡ ነገር ፡ በኋላ ፡ ቢያስረሱዋቸውም ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ ጨዋ ፡ የሚባሉት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ልጆቻቸውን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ማስገባት ፡ እንደ ፡ ግዴታ ፡ አድርገው ፡ የሚቆጥሩት ፡ ነገር ፡ ነበር ። እነዚህ ፡ ልጆች ፡ መጀመሪያ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ሲገቡ ፡ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ አዲስ ፡ ገቢዎች ፡ ሁሉ ፡ አስቸጋሪዎች ፡ ነበሩ ። ሲቆዩ ፡ ግን ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ አስተዳደጋቸው ፡ ተለውጦ ፡ በትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ሕግ ፡ ታነጸ ። ታላቅየው ፡ ኦስታፕ ፡ ገና ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ኮብልሎ ፡ ሲሄድ ፡ ተይዞ ፡ ተመለሰና ፡ ያለ ፡ ርኅራኄ ፡ ተገርፎ ፡ ትምህርቱን ፡ እንዲቀጥል ፡ ተደረገ ። አራት ፡ ጊዜ ፡ ሙሉ ፡ የመማሪያ ፡ መጽሐፉን ፡ መሬት ፡ ቆፍሮ ፡ ሲቀብር ፡ አራቱንም ፡ ጊዜ ፡ በጽኑ ፡ ተገርፎ ፡ አዲስ ፡ መጽሐፍ ፡ ተሰጠው ። አምስተኛውንም ፡ መጽሐፍ ፡ እንደገና ፡ በቀበረው ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አባቱ ፡ የሚሰጥህን ፡ ትምህርት ፡ ከአላጠናቀቅህ ፡ በቀር ፡ ዛፖሮዥዬን ፡ በፍጹም ፡ አታየውም ፤ እንዲያውም ፡ ገዳም ፡ አስገብቼህ ፡ ሃያ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ እዚያው ፡ እንድትቀመጥ ፡ አደርግሃለሁ ፡ ብሎ ፡ ስለዛተበት ፡ ፈርቶ ፡ ተወው ። ቀደም ፡ ብሎ ፡ እንደተረዳነው ፡ ትምህርትን ፡ በማጥላላት ፡ የተናገረው ፡ ያው ፡ ታራስ ፡ ቡልባ ፡ ራሱ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ምክር ፡ መስጠቱ ፡ የሚያስገርም ፡ ነው ። ኦስታፕ ፡ አባቱ ፡ በማስፈራራት ፡ ከመከረው ፡ ጀምሮ ፡ በሚጠላቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ላይ ፡ ተግቶ ፡ አቀረቀረና ፡ በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ጎበዝ ፡ የሚባሉትን ፡ ተማሪዎች ፡ በለጣቸው ።



በዚያን ፡ ዘመን ፡ የሚሰጠው ፡ ትምህርት ፡ ከኑሮው ፡ ጋር ፡ እጅግ ፡ የተለያየ ፡ ነበር ። ተማሪዎቹም ፡ በኑሮአቸው ፡ አነስተኛውን ፡ ትምህርት ፡ እንኳን ፡ ከጥቅም ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ሥፍራ ፡ አያገኙለትም ፡ ነበር ። መምህራኑ ፡ ራሳቸው ፡ ልምምድ ፡ ስለሚያንሳቸው ፡ የተማሩትን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በማዋል ፡ ረገድ ፡ ከተማሪዎቹ ፡ የባሱ ፡ ነበሩ ። ጥብቅ ፡ የሆነው ፡ የትምህርት ፡ ቤት ፡ ኑሮና ፡ የልበ ፡ ሙሉ ፡ ጐረምሶች ፡ ብዛት ፡ ከትምህርት ፡ ውጭ ፡ የሆኑ ፡ አንዳንድ ፡ ተግባሮችን ፡ ለመፈጸም ፡ ምክንያት ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። መጨቆን ፤ ተደጋግሞ ፡ በረሃብ ፡ መቀጣት ፤ እነዚህን ፡ የመሳሰሉት ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ልበ ፡ ሙሉውንና ፡ ጠንካራውን ፡ ጐልማሳ ፡ ኋላ ፡ በዛፖሮዥዬ ፡ እየገነነ ፡ ወደሚሄደው ፡ የግድ ፡ የለሽነት ፡ ጠባይ ፡ ይመሩታል ። የተራቡት ፡ ተማሪዎች ፡ በኪዩቨ ፡ መንገዶች ፡ ሲዘዋወሩ ፡ ለሕዝብ ፡ ታላቅ ፡ ስጋት ፡ ነበሩ ። በገበያ ፡ ተቀምጠው ፡ ዳቦ ፤ የዱባ ፡ ፍሬና ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ነገሮች ፡ የሚሸጡት ፡ ሴቶች ፡ አንድ ፡ ተማሪ ፡ ሲያልፍ ፡ ያዩ ፡ እንደሆን ፡ ጫጩቶችዋን ፡ ከጠላት ፡ ለማዳን ፡ እንደምታቅፍ ፡ አሞራ ፡ እቃቸውን ፡ ከድነው ፡ ይይዛሉ ። ጓደኞቹን ፡ እንዲጠባበቅ ፡ የተሾመው ፡ የተማሪዎች ፡ አለቃ ፡ ራሱ ፡ የሚያስፈሩ ፡ ትልልቅ ፡ የሱሪ ፡ ኪሶች ፡ ስለነበሩት ፡ አንዲት ፡ ነጋዴ ፡ ሴት ፡ ለመሸጥ ፡ ያስቀመጠችውን ፡ እቃ ፡ ሁሉ ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ከቶ ፡ ለመሄድ ፡ የሚችል ፡ ነበር ።

ተማሪዎቹ ፡ ለብቻቸው ፡ የተለየ ፡ ዓለም ፡ አበጁ ። የሩሲያና ፡ የፖላንድ ፡ መኳንንት ፡ ወደሚገኙበት ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ እንዲቀላቀሉ ፡ አይፈቀድላቸውም ። የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ራሳቸው ፡ አዳም ፡ ኪሴል ፡ ተማሪዎቹ ፡ ከሕዝቡ ፡ እንዳይቀላቀሉና ፡ ጥብቅ ፡ ቁጥጥርም ፡ እንዲደረግባቸው ፡ አዝዘዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ትዕዛዝ ፡ አስፈላጊም ፡ ባልሆነ ፡ ነበር ። ምክንያቱም ፡ መምህራኑ ፡ ባይታዘዙም ፡ እንኳን ፡ ጥብቅ ፡ ቁጥጥራቸውን ፡ ችላ ፡ ብለው ፡ አያውቁም ። ሲጋረ

ፉም ፡ ከጨካኝነታቸው ፡ የተነሣ ፡ የተገረፉት ፡ ተማሪዎች ፡ ለብዙ ፡ ሳምንት ፡ ሱሪአቸውን ፡ ሲያኮ ፡ ይሰነብቱ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ለብዙዎቹ ፡ ተማሪዎች ፡ ትንሽ ፡ በርበሬ ፡ ጣል ፡ ካለበት ፡ ጥሩ ፡ ቮድካ ፡ ብዙም ፡ የጠነከረ ፡ ሆኖ ፡ አይሰማቸውም ፡ ነበር ። አንዳንዶቹም ፡ ፀየጊዜው ፡ ያለ ፡ ርኅራኄ ፡ መገረፍ ፡ ሲመርራቸው ፡ መንገዱን ፡ ካወቁትና ፡ ተይዘው ፡ ካልተመለሱ ፡ በቀር ፡ ወደ ፡ ዛፖሮዥዬ ፡ ጠፍተው ፡ ይሄዳሉ ።

ኦስታፕ ፡ ቡልባ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ወደ ፡ ትምህርቱና ፡ ወደ ፡ መንፈሳዊነትም ፡ ለማዘንበል ፡ ቢጣጣር ፡ ዱላው ፡ አልቀረለትም ። ግን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ልዩ ፡ የሆነውን ፡ የኮዛክ ፡ ጠንካራ ፡ ጠባዩን ፡ የበለጠ ፡ ከማጠንከር ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ አልለወጠውም ። ኦስታፕ ፡ በብዙዎች ፡ ዘንድ ፡ ጥሩ ፡ ጓደኛ ፡ ሆኖ ፡ የሚገመት ፡ ነበር ። የሰውን ፡ አታክልት ፡ ለመዝረፍ ፡ ሌላም ፡ ይህንን ፡ የመሳሰሉ ፡ ተግባሮች ፡ ለመፈጸም ፡ ጓደኞቹን ፡ መርቶአቸው ፡ አያውቅም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ የተንኮል ፡ ማሕበር ፡ ሲቋቋም ፡ አባል ፡ ለመሆን ፡ ቀዳሚ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ቢደርስበት ፡ ጓደኞቹን ፡ አሳልፎ ፡ አይሰጣቸውም ፡ ነበር ። ጓደኞቹን ፡ እንደያሳጣ ፡ የሚያደርገው ፡ ምንም ፡ ሽመልና ፡ አለንጋ ፡ አይገኝም ። ከድብድብና ፡ ይህን ፡ ከመሳሰሉ ፡ የጦርነት ፡ ተግባሮች ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ተንኮል ፡ በሃሳቡ ፡ አይገባም ። ለጓደኞቹ ፡ ልቡ ፡ ንጹህና ፡ ግልጽ ፡ ነበር ። ደግና ፡ ሩኅሩኅም ፡ ነበር ። የአሳዛኝዋ ፡ እናቱ ፡ እንባ ፡ ልቡን ፡ ነክቶታል ፤ አሁንም ፡ ያሳዘነውና ፡ አንገቱን ፡ ያስደፋው ፡ ይኼው ፡ ነው ።

የታናሽ ፡ ወንድሙ ፡ የአንድሬይ ፡ አስተያየት ፡ የነቃና ፡ ከታላቁ ፡ ይበልጥ ፡ እንደመብሰል ፡ ያለ ፡ ነበር ። ትምህርቱን ፡ በፈቃደኝነትና ፡ ያለችግር ፡ ነው ፡ የዘለቀው ። ከወንድሙ ፡ ይበልጥ ፡ ብልጥና ፡ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ የአደገኛ ፡ ተንኮል ፡ መሪ ፡ ነበር ። ብልጠቱም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ከቅጣት ፡



ያድነዋል ፤ ወንድሙ ፡ ኦስታፕ ፡ ግን ፡ መሽቆጥቆጥን ፡ በመጥላት ፡ ይቅርታ ፡ ለመለመን ፡ በፍጹም ፡ ሳያስብ ፡ ወዲያው ፡ ኮቱን ፡ አውልቆ ፡ ለመገረፍ ፡ ይጋደማል ። አንድሬይም ፡ የጀብዱ ፡ ፍላጎት ፡ በልቡ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ይነዳል ። ነገር ፡ ግን ፡ የሱ ፡ ልብ ፡ ለሌላ ፡ ስሜቶችም ፡ ክፍት ፡ ነበር ። አሥራ ፡ ስምንተኛ ፡ ዓመቱን ፡ ሲያልፍ ፡ በፍቅር ፡ ስሜቱ ፡ መጋል ፡ ጀመረ ። ሴት ፡ በሕልሙ ፡ መምጣት ፡ አዘወተረች ። የፍልስፍና ፡ ክርክር ፡ በሚደረግበት ፡ በትምህርት ፡ ሰዓትም ፡ ንጹህ ፤ የረጋችና ፡ ዓይነ ፡ መልካም ፡ ሆና ፡ ትታየዋለች ። የአጐጠጐጠው ፡ ደረትዋ ፤ የለሰለሰው ፡ ውብ ፡ ክንድዋና ፡ ከቀሚስ ፡ ዘልቆ ፡ የሚታየው ፡ ትከሻዋ ፡ ከዓይኑ ፡ አልለይ ፡ አለ ። ለጋውን ፡ አካላትዋን ፡ የሚሸፍነው ፡ ቀሚስዋ ፡ እንኳን ፡ ሳይቀር ፡ ሕልም ፡ እየሆነ ፡ ይታየው ፡ ጀመር ። በዚያ ፡ እድሜው ፡ ጦር ፡ ሜዳ ፡ ከመዝመቱ ፡ በፊት ፡ ስለሴት ፡ ማሰብ ፡ ለአንድ ፡ ኮዛክ ፡ ሃፍረትና ፡ ውርደት ፡ ሆኖ ፡ ስለሚቆጠር ፡ ይህንን ፡ የወጣትነት ፡ የፍቅር ፡ ስሜቱን ፡ ለጓደኞቹ ፡ አይገልጽም ፡ ነበር ። ተማሪ ፡ ቤት ፡ በነበረበት ፡ በመጨረሻው ፡ ዓመት ፡ የተንኮል ፡ አድማዎችን ፡ መምራቱን ፡ ችላ ፡ ብሎ ፡ በኪዬቭ ፡ ከተማ ፡ ዳር ፡ ዳር ፡ በአታክልት ፡ በተከበቡት ፡ ቤቶች ፡ መካከል ፡ ብቻውን ፡ መጓዝ ፡ አዘወተረ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የኡክሬኒያንና ፡ የፖሊሽ ፡ መኳንንት ፡ መኖሪያ ፡ ወደ ፡ ነበረው ፡ አሁን ፡ አሮጌው ፡ ኪዬቭ ፡ ወደሚባለው ፡ ሰፈርም ፡ ይሄድ ፡ ነበር ።

አንድ ፡ ጊዜ ፡ በዚሁ ፡ ሰፈር ፡ አፉን ፡ ከፍቶ ፡ እንደቆመ ፡ የአንድ ፡ የፖሊሽ ፡ መኳንንት ፡ ሰረገላ ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ሊሄድበት ፡ ለትንሽ ፡ ሲስተው ፡ የሚያስፈራ ፡ ጢም ፡ ያለው ፡ የሠረገላው ፡ ነጅም ፡ በያዘው ፡ አለንጋ ፡ ደህና ፡ አድርጐ ፡ አቀመሰው ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ወጣቱ ፡ ተማሪ ፡ በንዴት ፡ ገነፈለና ፡ በድፍረት ፡ የሠረገላውን ፡ መሽከርከሪያ ፡ በጠንካራ ፡ እጆቹ ፡ ይዞ ፡ አቆመው ። የሠረገላው ፡ ነጅም ፡ ጠቡን ፡

በመፍራት ፡ ለማምለጥ ፡ ፈረሶቹን ፡ መትቶ ፡ ሲያስጋልብ ፡
አንድሬይ ፡ ተሽከርካሪውን ፡ ቶሎ ፡ በመልቀቁ ፡ ብቻ ፡ ከከ
ባድ ፡ ጉዳት ፡ ድኖ ፡ ጭቃው ፡ ላይ ፡ በፊቱ ፡ ተደፋ ። ከወደ
ላይ ፡ እንደሙዚቃ ፡ ጣፋጭ ፡ የሆነ ፡ የሳቅ ፡ ድምጽ ፡ ተሰማ
ው ። ቀና ፡ ብሎ ፡ ሲያስተውልም ፡ ዓይነ ፡ መልካምና ፡ እንደ ፡
በረዶ ፡ የነጣች ፡ ወደር ፡ የሌላት ፡ ቆንጆ ፡ ልጃገረድ ፡ በመስኮ
ት ፡ ቆማ ፡ ተመለከተ ። የምትስቀው ፡ ከልብዋ ፡ ነበር ። አሳሳቅዋ
ም ፡ ለአስደናቂው ፡ ውበትዋ ፡ የበለጠ ፡ መልክ ፡ ሰጠው ።
ደንዝዞ ፡ ቆሞ ፤ ልቡ ፡ እሷ ፡ ዘንድ ፡ ሆኖ ፤ እጆቹ ፡ ግን ፡ ጭ
ቃውን ፡ ለመጥረግ ፡ ሲሞክሩ ፡ ፊቱን ፡ የበለጠ ፡ በማቆሸ
ሽ ፡ እየቀባባ ፡ በመገረም ፡ ይመለከታት ፡ ጀመር ። ይች ፡
ቆንጆ ፡ ልጃገረድ ፡ ማን ፡ ትሆን? የዚህን ፡ መልስ ፡ በሩ ፡ ላይ ፡
ተሰብስበው ፡ አንድ ፡ ወጣት ፡ ባንዱራ ፡ ሲጫወት ፡ የሚያ
ዳምጡትን ፡ አሽከሮች ፡ ለመጠየቅ ፡ አሰበ ። ነገር ፡ ግን ፡ አሽ
ከሮቹ ፡ በጭቃ ፡ የተለወሰውን ፡ ፊቱን ፡ በማየት ፡ ከመሳ
ቅ ፡ በቀር ፡ መልስም ፡ አልሰጡት ። በመጨረሻ ፡ ግን ፡ ለጉ
ብኝት ፡ የመጡት ፡ የኮቭኖ ፡ ወይወዳ ፡ ልጅ ፡ መሆንዋን ፡ ተረ
ዳ ። በማግሥቱ ፡ ማታ ፡ በኪየቭ ፡ ተማሪዎች ፡ ዘንድ ፡ ብቻ ፡
በተለመደ ፡ የተለየ ፡ ታላቅ ፡ ድፍረት ፡ በልጅትዋ ፡ ግቢ ፡ አጥ
ር ፡ ዘሎ ፡ ገብቶ ፡ በስተጓሮ ፡ ባለ ፡ በአንድ ፡ ዛፍ ፡ ተንጠ
ለጥሎ ፡ ጣራው ፡ ላይ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ በጢስ ፡ መውጫው ፡
ቁልቁል ፡ ወርዶ ፡ እልጅትዋ ፡ መኝታ ፡ ቤት ፡ ዱብ ፡ አለ ።
በዚያን ፡ ሰዓት ፡ ውቢቱ ፡ ልጃገረድ ፡ ከሻማ ፡ መብራት ፡ ፊት ፡
ለፊት ፡ ተቀምጣ ፡ የከበሩ ፡ ጉትቻዎችዋን ፡ ከጆሮዋ ፡ ታወ
ልቅ ፡ ነበር ። ወዲያው ፡ ይህ ፡ እንግዳ ፡ ሰውዬ ፡ ሳይታሰብ ፡
እክፍልዋ ፡ ገብቶ ፡ ስታየው ፡ ከድንጋጤ ፡ የተነሳ ፡ መናገር ፡ ተ
ሳናት ፤ ግን ፡ ከፊትዋ ፡ የቆመው ፡ ተማሪ ፡ ለመንቀሳቀስ ፡ እን
ኳን ፡ አፍሮ ፡ አንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ ቆሞ ፡ ስታይና ፡ እሱም ፡ መንገ
ዱ ፡ ላይ ፡ ሲወድቅ ፡ ያየችው ፡ ልጅ ፡ መሆኑን ፡ ስታስታውስ ፡
እንደገና ፡ ትስቅ ፡ ጀመር ። ወዲህም ፡ ደግሞ ፡ የአንድሬይ ፡



መልክ ፡ የሚያስፈራ ፡ አልነበረም ። እጅግ ፡ መልከ ፡ ቀና ፡
ጎልማሳ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ስትስቅ ፡ ቆየች ።
ውቢቱ ፡ ልጃገረድ ፡ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ የፖሊሽ ፡ ልጃገረድ ፡
ሁሉ ፡ ቀበጥና ፡ እብድ ፡ ቢጤ ፡ ነበረች ። ነገር ፡ ግን ፡ ዓይ
ኖችዋ ፡ እነዚያ ፡ ቁልጭ ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ጦር ፡ የሚወረወሩ ፡
ግሩም ፡ ዓይኖችዋ ፡ ያለማቋረጥ ፡ ይመለከቱት ፡ ነበር ። የወ
ይወዱ ፡ ልጅ ፡ በድፍረት ፡ ወደሱ ፡ ቀርባ ፤ የሚያንጸባርቀ
ውን ፡ አክሊሏን ፡ እራሱ ፡ ላይ ፡ ደፍታ ፤ የጆሮ ፡ ጉትቻዎ
ችዋን ፡ ከንፈሩ ፡ ላይ ፡ ስታንጠለጥል ፡ ባለወርቀ ፡ ዘቦ ፡ ዘርፍ ፡
የሆነ ፡ ስስ ፡ ጨርቅ ፡ አምጥታም ፡ ስትሸፍነው ፡ ተማሪው ፡
ከእንጨት ፡ የተሠራ ፡ ይመስል ፡ ደርቆ ፡ ቆመ ። በዚህ ፡ አኳ
ኋን ፡ በሺ ፡ የሚቆጠሩ ፡ የተንኮል ፡ ጨዋታዎች ፡ ስትጫ
ወትበት ፡ ተማሪው ፡ የበለጠ ፡ ግራ ፡ ገባው ። አፉን ፡ ከፍቶ ፡
ዓይን ፡ ዓይንዋን ፡ ሲመለከት ፡ ልዩ ፡ ፍጥረት ፡ ይመስል ፡ ነ
በር ። ወዲያው ፡ በሩ ፡ ሲንኳኳ ፡ ሰማችና ፡ ደንግጣ ፡ አልጋ
ው ፡ ሥር ፡ እንዲደበቅ ፡ ጠየቀችው ። ትንሽ ፡ ቆይታም ፡ አ
ገር ፡ አማን ፡ ሲሆን ፡ ደንገጡርዋን ፡ አንዲት ፡ የተማረከች ፡
ታታር ፡ ጠራችና ፡ ወደ ፡ ጓሮ ፡ ወስዳ ፡ ከአጥሩ ፡ እንድታስ
ወጣው ፡ አዘዘችለት ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ተማሪው ፡ አወጣጡ ፡ ላይ ፡
እንደ ፡ አገባቡ ፡ አልቀናውም ። ዘበኛው ፡ ነቃበትና ፡ በአጥ
ሩ ፡ ላይ ፡ እንደተንጠለጠለ ፡ እግሩን ፡ ሲመታው ፡ ሌሎቹም ፡
አሽከሮች ፡ መንገድ ፡ ድረስ ፡ እያባረሩት ፡ ልቡ ፡ እስቲጠፋ ፡
ሮጦ ፡ አመለጠ ። የወይወዱ ፡ ጭፍሮች ፡ ብዙ ፡ ስለነበሩ ፡ ከዚያ ፡
ወዲያ ፡ በግቢው ፡ ዙሪያ ፡ መድረስ ፡ አደገኛ ፡ ሆነ ። አንድ ፡
ቀን ፡ በአንድ ፡ የሮማውያን ፡ ካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
ልጅትዋን ፡ ዳግመኛ ፡ አያትና ፡ እሷም ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንዳ
ወቀችው ፡ ሁሉ ፡ ልብ ፡ ትርትር ፡ የሚያደርግ ፡ ፈገግታ ፡ አሳ
የችው ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እንዲሁ ፡ በጨረፍ
ታ ፡ ካየት ፡ በኋላ ፡ የኮቭኖ ፡ ወይወዳ ፡ ጉብኝታቸውን ፡ ፈ
ጽመው ፡ ተመለሱ ። ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ በውቢቱ ፡ የፖሊሽ ፡

ልጃገረድ ፡ ምትክ ፡ ሌላ ፡ ወፍራም ፡ አስቀያሚ ፡ ፊት ፡ በመስኮቱ ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡ ይታይ ፡ ጀመር ።

አሁን ፡ አንድሬይ ፡ አንገቱን ፡ አቀርቅሮና ፡ ዓይኖቹን ፡ ከፈረሱ ፡ ጋማ ፡ ላይ ፡ ተክሎ ፡ የሚያሰላስለው ፡ ይህንኑ ፡ ነበር ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ታላቁ ፡ መስክ ፡ ለምለም ፡ አረንጓዴ ፡ አጐናጽፎ ፡ አቅፎአቸው ፡ በዙሪያቸው ፡ ባለው ፡ ረጅም ፡ ሣር ፡ ተውጠው ፡ ከላይ ፡ ዘልቆ ፡ የሚታየው ፡ ጥቁሩ ፡ የኮዛክ ፡ ቆባቸው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቡልባ ፡ ተውጦበት ፡ ከነበረው ፡ ከግል ፡ አሳቡ ፡ ነቃና ፡ «ምነው ፡ ዝም ፡ አላችሁ ፡ የኔ ፡ ጐልማሶች? እንደ ፡ ባህታዊ ፡ ተከዛችሁሳ! ሃሳባችሁን ፡ ሁሉ ፡ ለሰይጣን ፡ ጣሉለት ! ትንባሆአችሁን ፡ አቀጣጥሉና ፡ ፈረሶቻችንን ፡ ኮልኩለን ፡ እንደወፍ ፡ እንብረር!» አለ ።

ኮዛኮቹ ፡ ፈረሶቻቸውን ፡ ቀስቅሰው ፡ በጓሣው ፡ ውስጥ ፡ ጠለሙ ፡ ጥቁር ፡ ቆባቸውም ፡ እንኳን ፡ ተሰወረ ። ጋልበው ፡ ለማለፋቸው ፡ የነበረው ፡ ምልክት ፡ ጥሰውት ፡ ያለፉት ፡ ሳር ፡ ብቻ ፡ ነበር ።

ፀሐይዋ ፡ ከፍ ፡ ብላ ፡ ሜዳውን ፡ በሞቃት ፡ ብርሃንዋ ፡ አልብሳዋለች ። ጭፍግግ ፡ ያለው ፡ ሃሣብ ፡ ሁሉ ፡ ከኮዛኮቹ ፡ አእምሮ ፡ ጠፍቶ ፡ ሔዶ ፡ ልባቸው ፡ እንደ ፡ ወፍ ፡ ይርገበገብ ፡ ጀመር ።

ሜዳው ፡ ከፊታቸው ፡ እየተዘረጋ ፡ ሲሔድ ፡ የበለጠ ፡ ያማረ ፡ ሆነ ። አሁን ፡ ኖቮሮሲያ ፡ የሚባለው ፡ እስከ ፡ ጥቁር ፡ ባህር ፡ ያለው ፡ ደቡባዊ ፡ አገር ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ድንግል ፡ ለምለም ፡ መስክ ፡ ነበር ። ያን ፡ ወሰን ፡ የሌለውን ፡ ለጥ ፡ ያለ ፡ መስክ ፡ ምንም ፡ ማረሻ ፡ ገና ፡ አልነካውም ። እንደ ፡ ጫካ ፡ የሚውጠውን ፡ ይህን ፡ ረጃጅም ፡ ሳር ፡ እየጣሱት ፡ የሚያልፉት ፡ ፈረሶች ፡ ብቻ ፡ ነበሩ ። እንደዚያ ፡ ያለ ፡ የተፈጥሮ ፡ ውበት ፡ በየትም ፡ አልነበረም ። የምድርዋን ፡ ገጽ ፡



በሚሊዮን ፡ የሚቆጠሩ ፡ አበቦች ፡ ጣል ፡ ጣል ፡ ያሉበት ፡ ወርቅማ ፡ አረንጓዴ ፡ ውቅያኖስ ፡ ያለበሰው ፡ ይመስል ፡ ነበር ። ረጃጅምና ፡ ቀጫጭን ፡ በሆኑት ፡ የሳር ፡ ዘለላዎች ፡ መካከል ፡ ሰማያዊ ፡ የወይን ፡ ጠጅና ፡ ሌላም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለማት ፡ ያላቸው ፡ አበቦች ፡ ብቅ ፡ ብቅ ፡ ብለዋል ፤ ከየት ፡ እንደመጣ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይወቅ ፡ አንድ ፡ ዘለላ ፡ ስንዴ ፡ በጓሳው ፡ ውስጥ ፡ አፍርቶ ፡ ይታያል ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ ቆቆች ፡ ከሳሩ ፡ ሥር ፡ አንገታቸውን ፡ ብቅ ፡ አድርገው ፡ ይመለከታሉ ። የሺ ፡ አእዋፍ ፡ ዜማ ፡ ሜዳውን ፡ ሞልቶታል ፤ በሰማዩ ፡ ላይ ፡ ጭልፊቶች ፡ በእርጋታ ፡ እያንዣበቡ ፡ ቁልቁል ፡ ያለውን ፡ ሳር ፡ አተኩረው ፡ ይመለከታሉ ። ሰማይና ፡ መሬት ፡ የገጠመ ፡ ከሚመስልበት ፡ ስፍራ ፡ ዝዮች ፡ እየጮኹ ፡ በአጀብ ፡ ሲበሩ ፡ ይታያሉ ። ከሳሩ ፡ ውስጥ ፡ አንዲት ፡ አሞራ ፡ ተነሥታ ፡ በሰማያዊው ፡ አየር ፡ እየታጠበች ፡ በረረች ። ወዲያው ፡ ጥቁር ፡ ነጥብ ፡ እስክትመስል ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ አየር ፡ ርቃ ፡ ተጓዘች ። አሁን ፡ ለአጭር ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ክንፍዋ ፡ በጸሃይ ፡ ብርሃን ፡ ብልጭ ፡ ሲል ፡ ይታያል ። አዬ ፡ መስኩ ፡ አገር ፡ እንዴት ፡ የተዋበክ ፡ ነህ!

መንገደኞቻችን ፡ ለምሳ ፡ የሚቆሙት ፡ ለጥቂት ፡ ደቂቃዎች ፡ ብቻ ፡ ነው ። በዚያም ፡ ጊዜ ፡ አጃቢዎቹ ፡ አስር ፡ ኮዛኮች ፡ በእንጨት ፡ ደንበጃኖች ፡ የተጫነውን ፡ ቮድካ ፡ አውርደው ፡ ለመጠጫ ፡ የሚያገለግሉትንም ፡ ቅሎች ፡ ያቀርባሉ ። የሚበሉት ፡ ዳቦ ፡ ወይም ፡ የስንዴ ፡ ብስኩት ፡ ከአሳማ ፡ ሥጋ ፡ ጋር ፡ ብቻ ፡ ነው ። ከዚያም ፡ አንዳንድ ፡ መለኪያ ፡ ቮድካ ፡ ይጠጣሉ ። ቡልባ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ሰው ፡ ሞቅ ፡ እንዲለው ፡ ስለማይፈልግ ፡ ከአንድ ፡ መለኪያ ፡ በላይ ፡ አይፈቅድም ፤ ከዚያ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ጉዞአቸውን ፡ ይቀጥላሉ ። በአመሻሽ ፡ ላይ ፡ የመስኩ ፡ መልክ ፡ ይለወጣል ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለማት ፡ ያለው ፡ ሰፊ ፡ ገጹ ፡ የጸሐይዋ ፡ ብርሃን ፡ እየሸሸ ፡ ሲሔድ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ አብሮ ፡ ይደብዛል ። ጥቁር ፡ አረ

ንጓዴ ፡ ቀለም ፡ የተቀባ ፡ በሚመስለው ፡ ሜዳ ፡ ላይም ፡ ጭ
ጋግ ፡ ይዘረጋል ። በዚያ ፡ ሰዓት ፡ እየአንዳንዱ ፡ አበባና ፡ እጽ
ዋት ፡ ሁሉ ፡ መአዛቸውን ፡ ይተነፍሳሉ ። በታላቅ ፡ ብሩሽ ፡
የተቀቡ ፡ የሚመስሉ ፡ ጽጌረዳ ፡ ቀለምና ፡ ወርቅማ ፡ መስመ
ሮች ፡ በሰማዩ ፡ ላይ ፡ ተዘርግተው ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ስስና ፡
ነጭ ፡ ቁርጥራጭ ፡ ደመና ፡ ይታያል ። ንጹህና ፡ አስደሳች ፡
አየር ፡ እንደ ፡ ለስላሳ ፡ የባህር ፡ ማእበል ፡ የሳሩን ፡ ጫፍ ፡
ጫፍ ፡ በእርጋታ ፡ እያንቀሳቀሰ ፡ ሽው ፡ ይላል ። ቀኑን ፡ ሞል
ቶት ፡ የነበረው ፡ የሙዚቃ ፡ ድምጽ ፡ ይጠፋና ፡ በምትኩ ፡ ሌላ ፡
ድምጽ ፡ ይሰማል ። ዝጉርጉር ፡ ፍልፈሎች ፡ ከየጉድጓዳቸው ፡
ወጥተው ፤ በኋላ ፡ እግሮቻቸው ፡ ቆመው ፡ ፉጨታቸው ፡
በሜዳ ፡ ያስተጋባል ። የፌንጣዎች ፡ ጫጫታም ፡ እያ
የለ ፡ ሔደ ፤ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ከአንድ ፡ ራቅ ፡ ያለ ፡ ኩሬ ፡ የሚ
መጣ ፡ የባህር ፡ አሞራ ፡ ጩኸት ፡ ቃጭል ፡ መስሎ ፡ ይሰ
ማል።

መንገደኖቹ ፡ ይቆሙና ፡ ለሌሊት ፡ መስፈሪያቸው ፡ ቦታ ፡
ይመርጣሉ ። ከዚያ ፡ እሳት ፡ አንድደው ፡ የብረት ፡ ድስታ
ቸውን ፡ ይጥዱና ፡ ገንፎቻውን ፡ ይቀቅላሉ ። ከእራት ፡ በኋላ ፡
ኮዛኮቹ ፡ የተቀየዱ ፡ ፈረሶቻቸውን ፡ እንዲግጡ ፡ በሜዳው ፡
ይለቁና ፡ በካባቸው ፡ ተጠቅልለው ፡ ይጋድማሉ ። ከዋክ
ብት ፡ ቁልቁል ፡ ይመለከቷቸዋል ። የሌሊቱ ፡ ጭርታ ፡ ጉል
ህ ፡ አድርጎ ፡ የሚያሰማውን ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ነፍሳት ፡ ድምጽ ፡
ጆሮዎቻቸው ፡ እየሰሙ ፡ እንቅልፍ ፡ ይወስዳቸዋል ። ከመካ
ከላቸው ፡ አንዱ ፡ ድንገት ፡ ነቅቶ ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ቢያስተውል ፡
የሚያበሩ ፡ ትሎች ፡ ከሩቅም ፡ ከቅርብም ፡ ሲያብለጨልጩ ፡
ያያል ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ በየመስኩና ፡ በየ
ወንዙ ፡ ዳር ፡ ዳር ፡ የደረቀው ፡ ሳር ፡ በቁዋያ ፡ እሳት ፡ ሲያ
ያዝ ፡ ብርሃኑ ፡ በጨለማው ፡ ሰማይ ፡ ተፈንጥቆ ፡ ይታያል ።
በዚህን ፡ ጊዜም ፡ የባህር ፡ አሞሮች ፡ ጥቁር ፡ ሆነው ፡ ወደ ፡
ሰሜን ፡ ሲበሩ ፡ የጽጌረዳ ፡ አበባ ፡ የመሰለው ፡ ብርሃን ፡ ያ



ርፍባቸውና ፡ ቀይ ፡ መሃረቦች ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ የሚበሩ ፡
ይመስላሉ ።

መንገደኞቹ ፡ ምንም ፡ እንቅፋት ፡ ሳያጋጥማቸው ፡ ቀ
ጠሉ ። በመንገዳቸው ፡ ላይ ፡ አንድም ፡ ዛፍ ፡ አላለፉም ፤ ያው ፡
የተዋበውና ፡ ነፃው ፡ ማለቂያ ፡ የሌለው ፡ መስክ ፡ ብቻ ፡ ነበ
ር ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ ብቻ ፡ በድኔፐር ፡ ወንዝ ፡ ዳር ፡ ዳር ፡ ያለ
ው ፡ ጫካ ፡ ጫፍ ፡ ጫፉ ፡ ሰማይ ፡ ገጠም ፡ መስሎ ፡ ይታያ
ቸዋል ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ታራስ ፡ ጥቁር ፡ ነጥብ ፡ መስሎ ፡
በሩቁ ፡ የሚታይ ፡ ነገር ፡ ለልጆቹ ፡ እያመለከተ ፡ «ተመል
ከቱ ፡ ልጆቼ ፤ እዚያ ፡ ወዲያ ፡ አንድ ፡ ታታር ፡ ይጋልባል!»
አላቸው ። ትንሹ ፡ ባለጢም ፡ የታታሩ ፡ ፊት ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡
በጠባብ ፡ ዓይኖቹ ፡ ከሩቅ ፡ ከአስተዋላቸው ፡ በኋላ ፡ አየሩ
ን ፡ እንደውሻ ፡ አሽትቶ ፡ ኮዛኮቹ ፡ አሥራ ፡ ሶስት ፡ መሆና
ቸውን ፡ ሲገነዘብ ፡ እንደ ፡ ብሆር ፡ ፈርጥጦ ፡ ጠፋ ። ቡልባ
ም ፡ «ታዲያስ ፡ ጐልማሶች! ያን ፡ ታታር ፡ ትደርሱበት ፡ ይ
ሆን? ግን ፡ ቢቀር ፡ ይሻላል ፤ ምንም ፡ አትደርሱበትም ፤ ፈ
ረሱ ፡ ከኔው ፡ ዲያብሎስ ፡ እንኳን ፡ የፈጠነ ፡ ነው ፡» አለ ።
ሆኖም ፡ ቡልባ ፡ ድንገት ፡ ደፈጣ ፡ ያጋጠመን ፡ እንደሁ ፡ ብሎ ፡
በመስጋት ፡ መጠንቀቁን ፡ ችላ ፡ አላለም ። ወዲያው ፡ ወደ ፡
ድኔፐር ፡ ወደምትፈሰው ፡ ታታርካ ፡ ወደተባለችው ፡ ትንሽ ፡
ወንዝ ፡ ጋልበው ፡ ሔደው ፤ ዱካቸውን ፡ ለማጥፋት ፡ ከነ
ፈረሶቻቸው ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ በዋና ፡ ብዙ ፡ ከተጓ
ዙ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ ወጥተው ፡ ጉዞአቸውን ፡ ቀጠሉ ።

ከሶስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ከጉዞአቸው ፡ መድረሻ ፡ ተቃረ
ቡ ። አየሩም ፡ ቀዝቀዝ ፡ እያለ ፡ ሔደ ። ድኔፐር ፡ እንደቀረበ ፡
ተሰማቸው ፤ ወዲያው ፡ ከሰማይ ፡ ጋር ፡ የገጠመ ፡ መስሎ ፡
ከሩቅ ፡ ይታይ ፡ ጀመር ። ቀዝቃዛ ፡ አየር ፡ እየተነፈሰና ፡ እየ
ቀረበ ፡ መጥቶ ፡ በመጨረሻ ፡ የምድሩን ፡ ግማሽ ፡ አልብሶ ፡
ታያቸው ። አንድ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ድኔፐር ፡ የሚቀላቀሉት ፡
ፈጣን ፡ ወንዞች ፡ ኃይል ፡ ጨምረውለት ፡ እንደሞገደኛ ፡ ባህር ፡

እየደነፋ ፡ በሰፌው ፡ ይፈሳል ፤ ሌላ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ በመሃሉ ፡ ያሉት ፡ ደሴቶች ፡ ውኃውን ፡ ስለሚገፉት ፡ ከደሴቶቹ ፡ የሚሸሸውን ፡ ውኃ ፡ የሚያግደው ፡ ገደል ፡ ወይም ፡ ጉብታ ፡ ስለሌለ ፡ የበለጠ ፡ ሰፊ ፡ ሆኖ ፡ ከወሰኑ ፡ አልፎ ፡ ይንጣለላል ። ኮዛኮቹ ፡ ከፈረሶቻቸው ፡ ወርደው ፡ በአንድ ፡ ጀልባ ፡ ከተሳፈሩ ፡ በኋላ ፡ ሶስት ፡ ሰዓት ፡ ተጉዘው ፡ ዘላኑ ፡ ሴች ፡ ከሚገኙበት ፡ ከሆርቲጻ ፡ ደሴት ፡ ወደብ ፡ ደረሱ ።

ወደቡ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተሰብስበው ፡ ከባለጀልባዎች ፡ ጋር ፡ ይንጫጩ ፡ ነበር ። ኮዛኮቻችን ፡ የፈረሶቻቸውን ፡ መቀነቻ ፡ አጠበቁ ። ታራስ ፡ ቀበቶውን ፡ አጥብቆ ፡ ጢሙን ፡ በኩራት ፡ እየዳሰሰ ፡ ይጀነን ፡ ጀመር ። ጐልማሳ ፡ ልጆቹም ፡ ሽብር ፡ በተቀላቀለው ፡ የደስታ ፡ ስሜት ፡ አለባበሳቸውንና ፡ ትጥቃቸውን ፡ አስተካከሉ ። ከዚያ ፡ ሁሉም ፡ ተነስተው ፡ ከሴቹ ፡ ግማሽ ፡ ቬርስት ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ ወደሚገኝ ፡ አንድ ፡ የገጠር ፡ ሰፈር ፡ አመሩ ። ከሰፈሩ ፡ ሲደርሱም ፡ ሃምሳ ፡ የሚሆኑ ፡ አንጠረኞች ፡ በየስፍራው ፡ ብረት ፡ ሲቀጠቅጡ ፡ የመዶሻቸው ፡ ድምጽ ፡ ጆሮአቸውን ፡ አደነቆረው ። ክንዳማ ፡ የሆኑ ፡ ፋቂዎች ፡ በመንገዱ ፡ ዳር ፡ በየበረንዳው ፡ ጥላ ፡ ሥር ፡ ተቀምጠው ፡ የበሬ ፡ ቆዳ ፡ ይወጥራሉ ። ነጋዴዎች ፡ ከፊታቸው ፡ ብረታ ፡ ብረትና ፡ የባሩድ ፡ እቃ ፡ ሌላም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሸቀጣ ፡ ሸቀጥ ፡ ደርድረው ፡ በድንኳኖቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጠዋል ። እዚህ ፡ አንድ ፡ አርመን ፡ ዋጋቸው ፡ ውድ ፡ የሆነ ፡ ጨርቃ ፡ ጨርቆቹን ፡ ሰቅሎአል ። እዚያ ፡ አንድ ፡ ታታር ፡ የተከተፈ ፡ የበግ ፡ ሥጋ ፡ በሊጥ ፡ እየጠቀለለ ፡ ይጠብሳል ። አንድ ፡ አይሁድ ፡ አንገቱን ፡ አቀርቅሮ ፡ ቮድካ ፡ ከበርሚል ፡ ይቀዳል ። ነገር ፡ ግን ፡ መጀመሪያ ፡ ያዩት ፡ ሰው ፡ እጅና ፡ እግሮቹ ፡ ተዘረጋግተው ፡ ተንጋሎ ፡ መሃል ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ጭው ፡ ያለ ፡ እንቅልፍ ፡ የወሰደውን ፡ የዛፖሮዥያዊ ፡ ኮዛክ ፡ ነው ። ታራስ ፡ ቡልባ ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ ቆሞ ፡ ሳያደንቅ ፡ ለማለፍ ፡ አልቻለም ።



«እንዴት ፡ ግሩም ፡ ትይንት ፡ ነው! እንዴት ፡ ያለ ፡ የወንድነት ፡ መልክ ፡ አለው!» ብሎ ፡ በአድናቆት ፡ ጮኸ ።

በእውነትም ፡ ትይንቱ ፡ የጀግንነት ፡ መልክ ፡ ያለው ፡ ትይንት ፡ ነበር ። መሃል ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ የተዘረጋው ፡ ኮዛክ ፡ የተጐነጐነው ፡ ጐፈሬው ፡ ክንድ ፡ ሙሉ ፡ ይሆናል ፤ ሰፊውን ፡ ሱሪውን ፡ ከአማረ ፡ ቀይ ፡ ጨርቅ ፡ መሰፋቱን ፡ በመናቅና ፡ ከምንም ፡ ባለመቁጠር ፡ በጥቁር ፡ ዘይት ፡ አበላሽቶታል ።

ቡልባ ፡ ይህን ፡ ኮዛክ ፡ ከልቡ ፡ ካደነቀው ፡ በኋላ ፡ በሞያተኞች ፡ በተጣበበ ፡ ቀጭን ፡ መንገድ ፡ ጉዞውን ፡ ይቀጥላል ። የሴቹ ፡ ባልደረቦች ፡ ከመተኮስና ፡ ጦር ፡ ከመስንዘር ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ ስለማያውቁ ፡ የሚያለብሱዋቸውና ፡ የሚመግቡዋቸው ፡ ከየዘሩ ፡ የተጠራቀሙት ፡ እነዚህ ፡ ሞያተኞች ፡ ነበሩ ።

በመጨረሻ ፡ ይህን ፡ ሰፈር ፡ አልፈው ፡ ሳር ፡ ክዳን ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ታታሮች ፡ ልማድ ፡ ቆዳ ፡ ክዳን ፡ ያሏቸውን ፡ የኮዛክ ፡ ጐጆዎች ፡ ፈንጠር ፡ ፈንጠር ፡ ብለው ፡ ያዩሉ ። በዚሀ ፡ ቀበሌ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ ባለፉት ፡ ሰፈር ፡ እንዳዩት ፡ ያለ ፡ ባለአጥር ፡ ከበሩም ፡ ላይ ፡ ጥላ ፡ የሚሆን ፡ በረንዳ ፡ ያለው ፡ ቤት ፡ አይታይም ። አንዳንዶቹ ፡ የኮዛኮቹ ፡ ጐጆዎች ፡ ብቻ ፡ በዙሪያቸው ፡ መድፍ ፡ ተጠምዶአል ። አጭር ፡ ሆኖ ፡ የተሠራና ፡ በምንም ፡ ዘበኛ ፡ ያልተጠበቀ ፡ በእንጨትና ፡ በአፈር ፡ ክምር ፡ የተሠራ ፡ ምሽግ ፡ ለግድ ፡ የለሽነት ፡ ድፍረትና ፡ ለጥንቃቄ ፡ ማነስ ፡ ምልክት ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ። ጥቂቶች ፡ ጠብደል ፡ ኮዛኮች ፡ የትንባሆ ፡ ማጤሻቸውን ፡ እንደጐረሱ ፡ መሃል ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ተኝተው ፡ መንገደኞቹ ፡ ሲያልፉ ፡ በቸለተኝነት ፡ ከመመልከት ፡ በቀር ፡ አልተሸበሩም ። ታራስና ፡ ልጆቹ ፡ «እንዴት ፡ ዋላችሁ ፡ ጐበዝ!» ብለው ፡ በጥንቃቄ ፡ በመካከላቸው ፡ ሲያልፉ ፡ ዛፖሮዥያኖቹ ፡ «እንዴት ፡ ዋላችሁ!» በማለት ፡ መለሱላቸው ። በየስፍራው ፡ ተሰብ

ስበው ፡ የቆሙት ፡ ሰዎች ፡ በጦር ፡ ሜዳና ፡ በማናቸውም ፡ የጀብዱ ፡ ሞያ ፡ የተፈተኑ ፡ ለመሆናቸው ፡ የጠየመው ፡ ፊታቸው ፡ ምስክር ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ። ሴቹ ፡ ማለት ፡ ይሄ ፡ ነው! እንደ ፡ አንበሳ ፡ ኩሩና ፡ ጠንካራ ፡ የሆኑት ፡ የወንዶች ፡ ሰፈር ፡ ይህ ፡ ነው! ነፃነትና ፡ ኮዛካዊነት ፡ በሞላው ፡ ኡክሬይን ፡ የሚፈሰው ፡ ከዚህ ፡ ፈልቆ ፡ ነው!

መንገደኞቹ ፡ ራዳ ፡ የሚባለው ፡ የኮዛኮች ፡ ሸንጎ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ከሚሰበሰብበት ፡ ሰፊ ፡ አደባባይ ፡ ደረሱ ። በዚያ ፡ አደባባይ ፡ አንድ ፡ ዛፖሮዥያን ፡ በአፉ ፡ በተደፋ ፡ ትልቅ ፡ በርሚል ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ሸሚዙን ፡ አውልቆ ፡ ቀዳዳውን ፡ ይጠቅማል ። እልፍ ፡ ሲሉ ፡ ሙዚቀኞች ፡ ተሰብስበው ፡ በመሃላቸው ፡ አንድ ፡ ወጣት ፡ ዛፖሮዥያን ፡ ሲጨፍር ፡ ተመለከቱ ። ወጣቱ ፡ ጨፋሪ ፡ እየደጋገመ ፡ እንዲህ ፡ ይል ፡ ነበር ። «ሙዚቃውን ፡ ፈጠን ፡ አድርጉት ፡ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ፎማ ፡ እነዚህን ፡ ክርስቲያኖች ፡ ከቮድካው ፡ አትንፈጋቸው!» ፎማ ፡ የተባለው ፡ ኮዛክም ፡ በትልቅ ፡ ዋንጫ ፡ ቮድካ ፡ እየቀዳ ፡ ለሚመጣው ፡ ሁሉ ፡ ይሰጣል ። በወጣቱ ፡ ዛፖሮዥያን ፡ ዙሪያ ፡ አራት ፡ ጠና ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ሽብረክ ፡ ቀና ፡ እያሉና ፡ እንደ ፡ አውሎ ፡ ነፋስ ፡ እየተሽከረከሩ ፡ ይጨፍራሉ ። በጭፈራቸው ፡ መሬቱን ፡ ሲረግጡትም ፡ ሩቅ ፡ ድረስ ፡ ይሰማል ። ከመካከላቸው ፡ አንዱ ፡ ጭፈራው ፡ ከሁሉ ፡ የፈጠነና ፡ ጩኸቱም ፡ ከሁሉም ፡ የበለጠ ፡ ነበር ። የተንጎነጎነው ፡ ጸጉሩ ፡ በነፋሱ ፡ ይውለበለባል ፤ ጡንቻማ ፡ ደረቱ ፡ ባዶ ፡ ሲሆን ፡ የለበሰው ፡ ከበግ ፡ ቆዳ ፡ የተሠራ ፡ ሞቃት ፡ ኮት ፡ ብቻ ፡ ስለነበር ፡ ከሰውነቱ ፡ የሚወርደው ፡ ላብ ፡ በባልዲ ፡ የሚቀዳ ፡ ይመስላል ። ይህን ፡ በተመለከተ ፡ ጊዜ ፡ ታራስ ፤ «ኮትህን ፡ አውልቀው ፤ በሙቀት ፡ ቀለጥህ ፡ አይደለም ፡ እንዴ !» አለው ፤ ዛፖሮዥያኑ ፡ «የለም ፡ አልችልም ፡» በማለት ፡ ጮኾ ፡ መለሰ ። «ለምን?» «የለም ፡ ተፈጥሮዬ ፡ ነው ፤ አውልቄ ፡ የምጥለውን ፡ ነገር ፡



ሁሉ ፡ ቮድካ ፡ ነው ፡ የምገዛበት!» በውነትም ፡ ጎልማሳው ፡ ቆብም ፡ በኮፍታኑ ፡ ላይ ፡ የሚውለው ፡ ጨርቅም ፡ እንዲሁም ፡ ያጌጠ ፡ ባለጥልፍ ፡ መሃረብ ፡ አልነበረውም ። ሁሉም ፡ እንደተለመደው ፡ ሔደዋል ፡ ማለት ፡ ነው ። በዘፈኑ ፡ ቦታ ፡ ሕዝቡ ፡ እየበረከተ ፡ ሔዶ ፤ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ በጭፈራው ፡ ተካፋይ ፡ ሆኑ ። ከተመልካቾቹ ፡ መካከል ፡ ይህን ፡ አስደናቂ ፡ ጭፈራ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ የማይነሽጠው ፡ አልነበረም ። ጭፈራው ፡ ከታላቆቹ ፡ መሥራቾቹ ፡ ባገኘው ፡ ስም ፡ ኮዛቾክ ፡ የሚባለው ፡ ጭፈራ ፡ ነው ።

«ምነው ፡ ፈረስ ፡ ላይ ፡ ባልሆንኩ ፡ ኖሮ ፡ እኔም ፡ ከጭፈራው ፡ በገባሁ ፡ ነበር!» አለ ፡ ታራስ ። ይህ ፡ ሲሆን ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ በጀብዱ ፡ ሞያቸው ፡ በሴቹ ፡ በሞላ ፡ የሚከበሩት ፡ የተጎነጎነው ፡ ጠጉራቸው ፡ የሸበተ ፡ ጠና ፡ ያሉት ፡ ኮዛኮች ፡ ብቅ ፡ ይሉ ፡ ጀመር ። ወዲያው ፡ ታራስ ፡ የሚያውቃቸውን ፡ ሰዎች ፡ አገኘ ። «አንተ ፡ ነህ ፡ እንዴ ፡ ፔቼሪጺ! እንደምነህ ፡ ኮዞሉፕ!» «ምን ፡ እግር ፡ አመጣህ ፡ ታራስ?» «አንተ ፡ ደግሞ ፡ እዚህ ፡ ምን ፡ ታደርጋለህ ፡ ዶሎቶ?» «እንደምነህ ፡ ኪርዱግ! እንደምነህ ፡ ጉስትይ! እንደገና ፡ እንገናኛለን ፡ ብዬ ፡ አላሰብኩም ፡ ነበር ፡ ሬሜኝ!» እያለ ፡ ታራስ ፡ ከነዚህ ፡ ከሩሲያ ፡ መስክ ፡ ከተሰበሰቡት ፡ ጀግኖች ፡ ጋር ፡ ተሳስሞ ፡ ጥያቄ ፡ መጠየቅ ፡ ሲቀጥል ፡ ሁለቱ ፡ ልጆቹ ፡ ያዳምጡት ፡ ነበር ። «ካስያን ፡ እንዴት ፡ ነው? ቦሮዳቭካ ፡ የት ፡ አለ? ኮሎፔርስ? ፔድስቶክ ፡ እንደምነው?» ነገር ፡ ግን ፡ ታራስ ፡ ለጥያቄዎቹ ፡ ያገኘው ፡ መልስ ፡ ቦሮዳቭካ ፡ በቶሎፓን ፡ ተሰቀለ ፤ ኮሎፔር ፡ ከነነፍሱ ፡ እንዳለ ፡ ቆዳው ፡ ተገፈፎ ፡ በኪዚኪርሜን ፡ አቅራቢያ ፡ ሞተ ፤ የፔድስቶክ ፡ ጭንቅላት ፡ በጨው ፡ ታጅሎ ፡ በቶፋ ፡ ወደ ፡ ኮንስታንቲኖፖል ፡ ተልኳል ፡ የሚሉ ፡ መርዶዎች ፡ ነበሩ ። «አዬ ፡ ጉድ ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ጥሩ ፡ ኮዛኮች ፡ ነበሩ!» ብሎ ፡ ተከዘ ።

## ምዕራፍ ፡ ሶስት ።

ታራስ ፡ ቡልባና ፡ ልጆቹ ፡ አንድ ፡ ሳምንት ፡ ያህል ፡ አልፎአቸዋል ። አስታፕና ፡ አንድሬይ ፡ በጦር ፡ ትምህርት ፡ ያጠፉት ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ አጭር ፡ ነበር ። በመሠረቱ ፡ ሴቹ ፡ በጦር ፡ ትምህርት ፡ ረገድ ፡ ለመቸገርና ፡ ጊዜውን ፡ ሊያጠፉ ፡ አይፈቅድም ። የድርጅቱ ፡ ጐልማሶች ፡ የሚሰለጥኑትና ፡ ጦር ፡ የሚለምዱት ፡ በዋናው ፡ የጦር ፡ ሜዳ ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ለዚህም ፡ ሲባል ፡ ኮዛኮቹ ፡ አዘውትረው ፡ ጦርነት ፡ እንደገጠሙ ፡ ነው ። ለኢላማ ፡ ተኩስ ፡ ከመለማመድ ፡ አልፎ ፡ አልፎም ፡ ከፈረስ ፡ እሽቅድድምና ፡ በሜዳው ፡ ላይ ፡ አውሬ ፡ ከማባረር ፡ በቀር ፡ ለኮዛኮች ፡ ሌላውን ፡ የጦር ፡ ዘዴ ፡ ሁሉ ፡ ማጥናት ፡ የሚሰለችና ፡ ጊዜ ፡ ማባከን ፡ ሆኖ ፡ የሚቆጠር ፡ ሲሆን ፡ ዋናው ፡ የጊዜ ፡ ማሳለፊያቸው ፡ መደሰትና ፡ መጨፈር ፡ ነው ።

ሴቹ ፡ ያልተለመደና ፡ ማለቂያ ፡ የሌለው ፡ የጭፈራና ፡ የፈንጠዝያ ፡ ስፍራ ፡ ነበር ። አንዳንዶቹ ፡ በእጅ ፡ ሥራ ፡ ጊዜ ፡ ሲያሳልፉ ፡ ጥቂቶች ፡ ደግሞ ፡ ንግድ ፡ ሲሞክሩ ፡ አብዛኞቹ ፡ ኮዛኮች ፡ ግን ፡ የዘረፉዋቸው ፡ ንብረቶች ፡ ከነሱ ፡ አልፈው ፡ በነጋዴዎች ፡ እጅ ፡ እስኪገቡና ፡ ገንዘባቸው ፡ ከኪሳቸው ፡ እስኪያልቅ ፡ ድረስ ፡ ከጧት ፡ አንስቶ ፡ እስከማታ ፡ ድረስ ፡ በመፈንጠዝ ፡ ነው ፡ ጊዜያቸውን ፡ የሚያሳልፉት ። ፈንጠዝያቸው ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ አይነት ፡ ደስ ፡ የሚል ፡ ለዛ ፡ ነበረው ። ስብሰባቸውና ፡ ድግሳቸው ፡ ኃዘናቸውን ፡ በመጠጥ ፡ ለመሸፈን ፡ እንደሚጥሩ ፡ ሰዎች ፡ ያለ ፡ ሳይሆን ፡ ከልብ ፡ የመነጨ ፡ የእውነተኛ ፡ ደስታ ፡ ድግሥ ፡ ነው ። በዚያ ፡ የፈንጠዝያ ፡ ስብሰባ ፡ የሚገኝ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ማናቸውንም ፡ ችግሩን ፡ ከኋላ ፡ አራግፎ ፡ መምጣት ፡ አለበት ፡ በጠቅላላው ፡ ዋናው ፡ ዓላማው ፡ ያለፈውን ፡ ሕይወቱን ፡ ሁሉ ፡ እንዳልነበረ ፡ አድርጎ ፡ በመጣል ፤ ከላይ ፡ ከተንጣለለው ፡ ሰማይና ፡



ከውስጣዊ ፡ የሕይወት ፡ ደስታቸው ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ቤት ፡ ንብረት ፡ ከሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ በኅብረት ፡ ወደ ፡ ነፃው ፡ የዘላንነት ፡ ኑሮ ፡ ብቻ ፡ መግፋት ፡ ነው ። ይህ ፡ ዓላማ ፡ ነው ፡ ያንን ፡ ታላቅ ፡ የፈንጠዝያ ፡ መንፈስ ፡ ያመነጨው ። ያለሥራ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ተጋድመው ፡ የሚያወጉትን ፡ ቀልድና ፡ ጨዋታ ፡ ሰምቶ ፡ ሳይስቁ ፡ ለማለፍ ፡ እጅግ ፡ አዳጋች ፡ ነው ። አንድ ፡ ዛፖሮዥያን ፡ ጊዜውን ፡ የሚያሳልፈው ፡ በስካርና ፡ በፈንጠዝያ ፡ ቢሆንም ፡ ፈንጠዝያው ፡ በመጠጥ ፡ ቤት ፡ እንደሚገኘው ፡ ያለ ፡ የውሸት ፡ ደስታ ፡ የሚሰጥ ፡ አልነበረም ። የኮዛኮች ፡ ኑሮ ፡ በአንድ ፡ ትምህርት ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ እንደተመደቡ ፡ ተማሪዎች ፡ የተሳሰረ ፡ የጓደኝነትና ፡ የኅብረት ፡ ኑሮ ፡ ነው ። ከተማሪ ፡ ቤት ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ በትምህርት ፡ ክፍል ፡ ተጐልቶ ፡ የአስተማሪውን ፡ ወሬ ፡ ሲያዳምጡ ፡ በመዋል ፡ ፈንታ ፡ ኮዛኮቹ ፡ አምስት ፡ ሺ ፡ ፈረስ ፡ ጭነው ፡ ለወረራ ፡ሲዘምቱ ፡ መታየታቸው ፡ ነው ። በትምህርት ፡ ቤታቸው ፡ ኳስ ፡ በሚጫወቱበት ፡ ሜዳ ፡ ምትክ ፡ አንድ ፡ ፈጣን ፡ ታታር ፡ ወይም ፡ ባለአረንጓዴ ፡ ጥምጥም ፡ ቱርክ ፡ ድንገት ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡ ሰልሎት ፡ የሚሔድ ፡ ከድፍረት ፡ የተነሳ ፡ ዘብ ፡ ያልቆመበት ፡ ጠረፍ ፡ ነው ፡ ያላቸው ። በአንድ ፡ በኩልም ፡ ደግሞ ፡ ጐልማሶቹ ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ የተሰበሰቡት ፡ ያለፈቃዳቸው ፡ እየተገደዱ ፡ ሲሆን ፡ እዚህ ፡ የመጡት ፡ ግን ፡ ከእናት ፡ ከአባታቸው ፡ ቤት ፡ እየኮበለሉ ፡ እውነተኛውን ፡ የጀግንነት ፡ ኑሮ ፡ በመምረጥ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ስፍራ ፡ የተሰበሰቡት ፡ ሰዎች ፡ በጀግንነት ፡ ባሕሪያቸው ፡ መሠረት ፡ በኪሳቸው ፡ አንዲት ፡ ኮፔክ ፡ እንኳን ፡ የማያስቀምጡና ፡ ሃብት ፡ ለማከማቸት ፡ የማይጥሩ ፡ ናቸው ። በነዚህ ፡ ጐልማሶች ፡ መካከል ፡ የተማሪ ፡ ቤትን ፡ አለንጋ ፡ በመሰልቸት ፡ ሲኮበልሉ ፡ ከፊደላት ፡ አንዲት ፡ ቀለም ፡ እንኳን ፡ ሳይጨብጡ ፡ የመጡ ፡ ሲኖሩ ፡ አንዳንዶቹ ፡ ደግሞ ፡ ስለሆራስ ፤ ስለሲዜሮና ፡ ስለሮማውያን ፡ ሪፑብሊክ ፡ ታሪክ ፡ የሚ

ያውቁ ፡ የተማሩ ፡ ናቸው ። ኋላ ፡ በፖላንድ ፡ ንጉሥ ፡ አርማ ፡ ሥር ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ያገኙ ፡ የጦር ፡ መኮንኖችና ፡ እንዲሁም ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ውለን ፡ ክብራችን ፡ ከጠበቅን ፡ የየትም ፡ ወገን ፡ ብንሆን ፡ ግድ ፡ የለም ፡ በሚል ፡ ዓላማ ፡ የሚመሩ ፡ ብዙ ፡ ጀግኖች ፡ በነዚሁ ፡ በኮዛኮች ፡ መካከል ፡ ነበሩ ። ብዙዎች ፡ ደግሞ ፡ ሴች ፡ ደርሰን ፡ የጀግና ፡ መኳንንትነት ፡ ደርሰናል ፡ ለማለት ፡ ብቻ ፡ የመጡ ፡ አሉ ። በዚህ ፡ ሰፍራ ፡ ማን ፡ የሌለ ፡ አለ? ይህ ፡ የዘመኑ ፡ ድንቅ ፡ የሆነ ፡ ልዩ ፡ ሪፑብሊክ ፡ ነበር ። የወርቅ ፡ ጽዋዎች ፤ የከበሩ ፡ ጨርቃ ፡ ጨርቅና ፡ የወርቅ ፡ ሳንቲሞችም ፡ እንዲሁም ፡ ጦርነት ፡ ወዳዶች ፡ በዚህ ፡ ሰፈር ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቦታ ፡ አያጡም ። ሰፍራ ፡ የማይገኝላቸው ፡ ለሴት ፡ ወዳዶች ፡ ብቻ ፡ ነበር ። አንዲት ፡ ሴት ፡ ከሴች ፡ ዳርቻ ፡ እንኳን ፡ ደርሳ ፡ አታውቅም ። እስታፕና ፡ አንድሬይ ፡ ወደ ፡ ሴቹ ፡ ሲገቡ ፡ ከአዩዋቸው ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ እነማናችሁ ፡ ከየትስ ፡ መጣችሁ ፡ በማለት ፡ ስማቸውን ፡ እንኳን ፡ የጠየቀ ፡ አንድም ፡ ሰው ፡ ስላልነበር ፡ ገረማቸው ። አዲስ ፡ ገቢዎች ፡ ሁሉ ፡ ሁናቴአቸው ፡ ሲታይ ፡ ለአንድ ፡ ሰዓት ፡ ብቻ ፡ ተለይተውት ፡ ወደ ፡ ቆዩት ፡ ቤታቸው ፡ ተመልሰው ፡ የሚገቡ ፡ እንጂ ፡ ለሰፈሩ ፡ እንግዳ ፡ አይመስሉም ። አዲስ ፡ መጪው ፡ መምጣቱን ፡ የሚገልጸው ፡ ለኮሼቮይ ፡ አታማኑ ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ ግንኙነታቸውም ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነበር ።

«እንኳን ፡ ደህና ፡ መጣህ ፡ ወዳጄ! በክርስቶስ ፡ ታምናለህ?»

«አምናለሁ ፡» ይላል ፡ አዲስ ፡ መጪው ።

«በሶስቱ ፡ ሰላሶችስ ፡ ታምናለህ?»

«አዎ ፤ አምናለሁ ።»

«ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትስማለህ?»

«አዎ ።»

«እስቲ ፡ ስታማትብ ፡ እንይህ ።»

አዲስ ፡ መጪውም ፡ ያማትባል ።



ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኮሼቮይው ፡ «መልካም ፤ ሒድና ፡ የመረጥከውን ፡ ጐጆ ፡ ውሰድ ፡» ይልና ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ ተፈጸመ ፡ ማለት ፡ ነው ።

በሴቹ ፡ ያሉት ፡ ሁሉ ፡ ጾምና ፡ ሱባኤን ፡ በፍጹም ፡ የማይሞክሩ ፡ ቢሆኑም ፡ በአንድ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተሰብስበው ፡ እየጸለዩ ፤ ይህንኑም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለመጠበቅ ፡ እስከመጨረሻው ፡ ጠብታ ፡ ደማቸውን ፡ ለማፍሰስ ፡ ዝግጁ ፡ ነበሩ ። ዛፖሮዥያኖቹ ፡ እጃቸው ፡ ከኪሳቸው ፡ የሚያወጣውን ፡ ገንዘብ ፡ ያለክርክር ፡ የሚያፈሱ ፡ ስለነበሩ ፡ አንዳንድ ፡ አይሁዶች ፤ አርመኖችና ፡ ታታሮች ፡ በሴቹ ፡ ዳር ፡ ሰፍረው ፡ ይነግዳሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ የነዚህ ፡ ብልጥ ፡ ነጋዴዎች ፡ መጨረሻቸው ፡ ዘወትር ፡ የጭንቅ ፡ ኑሮ ፡ ነበር ። ምክንያቱም ፡ ዛፖሮዥያኖቹ ፡ ገንዘባቸውን ፡ አባክነው ፡ ሲጨርሱ ፡ የነጋዴዎቹን ፡ መደብር ፡ እየሰባበሩ ፡ የፈለጉትም ፡ ሁሉ ፡ በዘረፋ ፡ ይወስዳሉ ።

ሴቹ ፡ ስልሳ ፡ መንደሮች ፡ ሲገኙበት ፡ እያንዳንዱም ፡ መንደር ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ነፃ ፡ ሪፑብሊክ ፡ ያለና ፡ ከአንድ ፡ የአዳሪ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የሚመሳሰል ፡ ነው ። ማንም ፡ ቤት ፡ ንብረት ፡ ለማበጀት ፡ ፍላጐት ፡ አልነበረውም ። ማናቸውም ፡ ነገር ፡ ባትኮ ፡ (አባት ፡) ተብሎ ፡ በሚጠራው ፡ በመንደሩ ፡ አለቃ ፡ እጅ ፡ ነው ። የገንዘብ ፤ የልብስ ፤ የምግብ ፤ የሚነደው ፡ እንጨት ፡ እንኳን ፡ ሳይቀር ፡ አላፊው ፡ ይኸው ፡ ባትኮ ፡ ነው ። ገንዘባቸውን ፡ እንዲያስቀምጥላቸው ፡ ለሱ ፡ ይሰጡታል ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ መንደረተኞቹ ፡ እርስ ፡ በእርስ ፡ የሚጣሉበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ። እንዲህ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ የጠቡ ፡ ጭቅጭቅ ፡ ወደ ፡ ዱላ ፡ ይደርስና ፡ የተጣሉት ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ እስኪያሸንፍ ፡ ድረስ ፡ ተቀጣቅጠው ፡ በመጨረሻው ፡ ሁሉም ፡ ያለቂም ፡ አብረው ፡ እየፈነጠዙ ፡ ጠቡ ፡ በዚህ ፡ ይፈጸማል ። በዚህ ፡ በዚህ ፡ ሴቹ ፡ ጐልማሶችን ፡ የሚማርክ ፡ ብዙ ፡ መልክ ፡ ነበረው ።

እስታፕና ፡ አንድሬይ ፡ በዚህ ፡ የደስታና ፡ የፈንጠዝያ ፡
ውቅያኖስ ፡ በሙሉ ፡ የወጣትነት ፡ ልባቸው ፡ ገብተው ፡ ተደ
ባለቁና ፡ የአባታቸውን ፡ ቤት ፤ ተማሪ ፡ ቤታቸውን ፡ ሌላ
ውንም ፡ ቀድሞ ፡ በአእምሮአቸው ፡ የነበረውን ፡ ሁሉ ፡ ወዲ
ያው ፡ ረስተው ፡ አዲሱን ፡ ኑሮአቸውን ፡ ይከታተሉ ፡ ጀመር ።
እዚህ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አስደሰታቸው ፤ ረብሻው ፡ ቀላ
ሉ ፡ አስተዳደርና ፡ ሕግጋቱ ፡ አስደሳች ፡ ሆነው ፡ ታዩዋቸው ።
ሕግጋቱ ፡ በብዙ ፡ ረገድ ፡ ቀላል ፡ ሆኖ ፡ ቢታይም ፡ አንዳ
ንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ እንዲህ ፡ ላለ ፡ ነፃ ፡ ሪፑብሊክ ፡ አለመ
ጠን ፡ ጥብቅ ፡ ደንቦች ፡ ነበሩ ። ለምሳሌ ፡ ሲሰርቅ ፡ የተገኘ ፡
ኮዛክ ፡ ስርቆቱ ፡ ምንም ፡ አነስተኛ ፡ ቢሆን ፡ ለጠቅላለው ፡
የኮዛካዊነት ፡ ክብር ፡ አሳፋሪ ፡ ሆኖ ፡ ስለሚገመት ፡ የሃፍረ
ት ፡ ምሰሶ ፡ ከሚባል ፡ አንድ ፡ ግንድ ፡ ጋር ፡ ይታሰርና ፡ ከ
ጐኑ ፡ አንድ ፡ ከንተሮ ፡ ተጋድሞ ፡ አላፊው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡
ከንተሮውን ፡ እያነሳ ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ ይቀጠቅጠዋ
ል ። እዳውን ፡ አልከፈለም ፡ ያለ ፡ ኮዛክ ፡ ሲገኝ ፡ ከመድ
ፍ ፡ ጋር ፡ በሰንሰለት ፡ ይታሰርና ፡ አንዱ ፡ ጓደኛው ፡ እዳው
ን ፡ ከፍሎ ፡ ካላስፈታው ፡ በቀር ፡ እዚያው ፡ እንደታሰረ ፡
ይቀራል ። ከሁሉም ፡ ይበልጥ ፡ አንድሬይን ፡ ያስደነቀው ፡
በነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ ላይ ፡ የሚፈጸመው ፡ ቅጣት ፡ ነው ። አን
ድሬይ ፡ ዓይኑ ፡ እያየ ፡ ጉድጓድ ፡ ተቆፍሮ ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዩ ፡
ጉድጓዱ ፡ ውስጥ ፡ ከነነፍሱ ፡ ተጥሎ ፡ የሟቹን ፡ ሬሳ ፡ የያዘ
ውም ፡ ሳጥን ፡ እዚያው ፡ ጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ተጨምሮ ፡ ሁለ
ቱም ፡ አብረው ፡ ሲቀበሩ ፡ ተመለከተ ። ከነሕይወቱ ፡ ከሬ
ሳ ፡ ሳጥን ፡ ጋር ፡ የተቀበረው ፡ ሰው ፡ በሃሳቡ ፡ እየመጣ ፡ አን
ድሬይ ፡ በዚህ ፡ አሰቃቂ ፡ ፍርድ ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ አእምሮው ፡
ታውኮ ፡ ነበር ።

በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሁለቱ ፡ ጐልማሶች ፡ በኮዛ
ኮቹ ፡ መካከል ፡ መልካም ፡ ስፍራ ፡ ለመያዝ ፡ በቁ ። ብዙ ፡
ጊዜ ፡ ከመንደረተኛ ፡ ጓደኞቻቸው ፡ ጋር ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡



ጠቅላላው ፡ ሰፈር ፡ በሙሉ ፡ ድርጅት ፡ ሲነሳ ፡ አብረው ፡
በፈረስ ፡ እየወጡ ፡ ስፍር ፡ ቁጥር ፡ የሌላቸው ፡ አእዋፍና ፡
የሜዳ ፡ እንስሳት ፡ በማደን ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ኩሬ
ዎችና ፡ ወደ ፡ ወንዞች ፡ እየሔዱ ፡ ለመንደራቸው ፡ ምግብ ፡
ለማከማቸት ፡ አሣ ፡ በማጥመድ ፡ የሥራ ፡ ተካፋይ ፡ ሆኑ ።
እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ የኮዛክነት ፡ ችሎታቸውን ፡ ለመፈ
ተን ፡ በቂ ፡ ባይሆንም ፡ በእድለኝነትና ፡ በድፍረታቸው ፡ የተ
ነሳ ፡ በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ከሌሎቹ ፡ ጐልማሶች ፡ የበ
ለጡ ፡ ሆነው ፡ ይታዩ ፡ ጀመር ። ደፋርና ፡ አነጣጣሪ ፡ ተኳ
ሾች ፡ ነበሩ ። የድኔፐርን ፡ ወንዝ ፡ ፈረሰኛውን ፡ ውኃ ፡ ታግ
ሎ ፡ ማቋረጥ ፡ ከኮዛኮች ፡ መካከል ፡ ክፍ ፡ ያለ ፡ ጉብ
ዝና ፡ ሆኖ ፡ ስለሚቆጠር ፡ ሁለቱ ፡ ጐልማሶች ፡ ይህንኑ ፡
ፈተና ፡ በሚገባ ፡ በማለፍ ፡ የውሃ ፡ ዋና ፡ ችሎታቸውን ፡ አስ
መሰከሩ ።

ሽማግሌው ፡ ታራስ ፡ ግን ፡ ለልጆቹ ፡ ያሰበላቸው ፡ ሌላ ፡
ዓላማ ፡ ነበረው ። በሚያሳልፉት ፡ የስንፍና ፡ ኑሮ ፡ መንፈ
ሱ ፡ ስለታወከ ፡ ለእውነተኛ ፡ የጀብዱ ፡ ሞያ ፡ ይጓጓ ፡ ጀ
መር ። በዚህም ፡ መሠረት ፡ መላውን ፡ የሴች ፡ ሰፈር ፡ ለዘ
መቻ ፡ እንዴት ፡ እንደሚያነሳሳው ፡ ብዙ ፡ ሲያሰላስል ፡ ከ
ቆየ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ኮሼቮይው ፡ ሔዶ ፤

«ታዲያስ ፡ ኮሼቮይ ፡ ዛፖሮዥያን ፡ ለዘመቻ ፡ የምን
ሰለፍበት ፡ ጊዜ ፡ አልደረሰምን?» ሲል ፡ በቀጥታ ፡ ጠየቀው ።

ኮሼቮዩም ፡ በአፉ ፡ የያዘውን ፡ የትንባሆ ፡ ማጤሻ ፡ አው
ጥቶ ፡ «ምንም ፡ የምንዘምትበት ፡ ስፍራ ፡ የለም ፡» አለው ።

«እንዴት ፡ የለም? በታታሮች ፡ ወይም ፡ በቱርኮች ፡
ላይ ፡ ልንዘምት ፡ እንችላለን!»

«በቱርኮችም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በታታሮችም ፡ ላይ ፡ ልን
ዘምት ፡ አንችልም ፡» አለና ፡ ኮሼቮዩ ፡ እንደገና ፡ የትንባ
ሆ ፡ ማጤሻውን ፡ ነከሰ ።

«ለምን ፡ አንችልም ?»

«ለሱልጣኑ ፡ የሰላም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገብተናል ።»

«ይህ ፡ እንዴት ፡ ይሆናል? እሱ ፡ የማያምን ፡ ነው ፤ የማያምኑትንም ፡ ሁሉ ፡ እንድንቀጣ ፡ አምላክና ፡ ቅዱስ ፡ ትእዛዙ ፡ ይፈቅዱልናል ።»

«የለም ፤ መብት ፡ የለንም ፤ በኃይማኖታችን ፡ ምለን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ባንገባ ፡ ኖሮ ፡ እርግጥ ፡ በተቻለ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ በፍጹም ፡ አንችልም ።»

«ለምን ፡ አንችልም? መብት ፡ የለንም ፡ ማለትህ ፡ ምን ፡ ማለትህ ፡ ነው? እኔ ፡ ገና ፡ ጦር ፡ ያልቀመሱ ፡ ሁለት ፡ ወጣት ፡ ልጆቼን ፡ ይዤ ፡ መጥቼአለሁ ፤ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ለዘመቻ ፡ መብት ፡ የለም ፡ ትላለህ ። ዛፖሮዥያኖች ፡ ሊዋጉ ፡ አይችሉም ፡ ማለትህ ፡ ነው?»

«ምንም ፡ ማድረግ ፡ አይቻልም ፡ የተወሰነው ፡ ይህ ፡ ነው ።»

«ታድያ ፡ የኮዛክ ፡ ጉልበት ፡ በከንቱ ፡ ሊጠፋ ፡ ይገባል? አንድ ፡ ወንድ ፡ ለክርስቲያንና ፡ ለሃገሩ ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ሞያ ፡ ሳይሠራ ፡ እንደውሻ ፡ ይሙት ፡ ሊባል ፡ ነው? ታድያ ፡ መኖራችን ፡ ለምን ፡ ይሆን? ንገረኝ ፡ ለምን ፡ ይሆን? አዋቂ ፡ ሰው ፡ ነህ ፤ ኮሼቮይ ፡ ለመሆን ፡ ያለእውቀትህ ፡ በከንቱ ፡ አልተመረጥክም ። እንግዲያው ፡ በል ፡ እስቲ ፡ ለምን ፡ እንደምንኖር ፡ ንገረኝ?»

ኮሼቮዩ ፡ ለጥያቄው ፡ ምንም ፡ መልስ ፡ አልሰጠው ፤ ከተናገረው ፡ የማይዛባ ፡ ኮዛክ ፡ ነበር ። ለትንሽ ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ «የሆነው ፡ ሆኖ ፡ ምንም ፡ ጦርነት ፡ አይደረግም ።» አለ ።

«ጦርነት ፡ አይደረግም ፡ አልከኝ?» አለና ፡ ታራስ ፡ ዳግመኛ ፡ ጠየቀው ።

«የለም ።»

«ታድያ ፡ ስለዚህ' ፡ ጉዳይ ፡ ማሰብም ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ ማለትህ ፡ ነው?»



«አዎ ፡ ምንም ፡ ጥቅም ፡ የለውም ።»

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ቡልባ ፡ በልቡ ፡ «ቆይ ፡ አሳይሃለሁ ፡ አንተ ፡ የሰይጣን ፡ ልጅ!» አለና ፡ ከዚያን ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ኮሼቮዩን ፡ ሊበቀለው ፡ ወሰነ ።

ቡልባ ፡ ብዙ ፡ ጓደኞቹን ፡ ሰብስቦ ፡ ከአነጋገራቸው ፡ በኋላ ፡ መጠጥ ፡ በሰፊው ፡ ሲያጠጣቸው ፡ ሞቅ ፡ ያላቸው ፡ ኮዛኮቹ ፡ ራዳውን ፡ ለመሰብሰብ ፡ የሚመታው ፡ ነጋሪት ፡ ወዳለበት ፡ አደባባይ ፡ ተግተልትለው ፡ ሔዱ ። እዚያም ፡ ሲደርሱ ፡ ነጋሪት ፡ መቺው ፡ የመምቻውን ፡ እንጨት ፡ ይዞት ፡ ሔዶ ፡ ስለነበር ፡ ሁሉም ፡ ያገኙትን ፡ ቁራጭ ፡ እንጨት ፡ እያነሱ ፡ ነጋሪቱን ፡ ይደበድቡ ፡ ጀመር ። የነጋሪቱን ፡ ድምጽ ፡ በመስማት ፡ ከሁሉ ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ አደባባዩ ፡ የመጣው ፡ ነጋሪት ፡ መቺው ፡ ራሱ ፡ ሲሆን ፡ እሱም ፡ ቁመተ ፡ ረጅም ፡ አንድ ፡ ዓይና ፡ ኮዛክ ፡ ነበር ። ያንኑ ፡ አንዱን ፡ ዓይኑንም ፡ እንቅልፍ ፡ ተጭኖት ፡ ይጨናበሳል ።

«የማን ፡ ደፋር ፡ ነው ፡ ነጋሪቱን ፡ የሚመታ?» አለና ፡ ጮኸ ።

በስካር ፡ ሞቅ ፡ ያላቸው ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ ኮዛኮቹም ፤ «ዝም ፡ በል! ዱላህን ፡ ያዝና ፡ እንደታዘዝህው ፡ ነጋሪቱን ፡ መምታት ፡ ነው ፡ ያለብህ ።» አሉት ። ነጋሪት ፡ መቺው ፡ እንዲህ ፡ ባለው ፡ ሰዓት ፡ መከራከር ፡ የሚያስከትለውን ፡ ነገር ፡ በደንብ ፡ ስለሚያውቅ ፡ በኪሱ ፡ የያዘውን ፡ አጭር ፡ የነጋሪት ፡ መምቻ ፡ እንደታዘዘው ፡ አወጣ ። ነጋሪቱም ፡ ሲጉስም ፡ ዛፖሮዥያኖቹ ፡ ከቀፎ ፡ እንደሚወጣ ፡ ንብ ፡ እየተግተለተሉ ፡ ወጥተው ፡ በአደባባዩ ፡ ዙሪያ ፡ ተሰለፉ ። በመጨረሻም ፡ ኮሼቮዩ ፤ ዳኛው ፤ ኤሳውሉና ፡ ሌሎቹም ፡ ሹማምንት ፡ መጥተው ፡ ቆባቸውን ፡ እያወለቁ ፡ በዙሪያቸው ፡ እጆቻቸውን ፡ በኩራት ፡ አጣምረው ፡ ለቆሙት ፡ ኮዛኮች ፡ ለጥ ፡ ብለው ፡ እጅ ፡ ነሱ ።

ወዲያው ፡ ኮሼቮዩ ፤ «የዚህ ፡ ስብሰባ ፡ ምክንያት ፡ ምን

ድነው? ፍላጐታችሁ ፡ ምን ፡ ይሆን ፡ ወዳጆቼ?» በማለት ፡ ሲጠይቅ ፡ ጫጫታና ፡ ሰድብ ፡ ዝም ፡ አሰኘው ።

«የስልጣን ፡ በትርህን ፡ አስቀምጥ! አሁኑኑ ፡ አስረክብ ፡ አንት ፡ የሰይጣን ፡ ልጅ! ከእንግዲህ ፡ አንፈልግህም!» እያሉ ፡ ኮዛኮቹ ፡ ይጮኹ ፡ ጀመር ። አንዳንዶቹ ፡ ሞቅ ፡ ያላላቸው ፡ ኮዛኮች ፡ በዚህ ፡ ሃሳብ ፡ አልተስማሙም ፤ በዚህ ፡ መሠረት ፡ የሰከረውም ፡ ያልሰከረውም ፡ ይንጫጫ ፡ ጀመር ።

ኮሼቮዩ ፡ ሊናገር ፡ ሞክሮ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ የተቆጣው ፡ በፈቃዱ ፡ አዳሪ ፡ ሕዝብ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ተደጋግሞ ፡ እንደተደረገው ፡ ሁሉ ፡ ደብድቦ ፡ ሊገድለው ፡ እንደሚችል ፡ ስለሚያውቅ ፡ ለጥ ፡ ብሎ ፡ እጅ ፡ ነሳና ፡ የሥልጣን ፡ ምልክት ፡ በትሩን ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ አጋድሞ ፡ ከሕዝቡ ፡ ተቀላቀለ ።

የቀሩት ፡ ሹማምንትም ፡ «ክቡራን ፡ ሆይ ፤ እኛም ፡ ሥልጣናችንን ፡ እንድናስረክብ ፡ ትፈልጋላችሁን?» ብለው ፡ በመጠየቅ ፡ ሁሉም ፡ ሥልጣናቸውን ፡ ለማስረከብ ፡ ተዘጋጁ ።

ሕዝቡ ፡ ግን ፡ «የለም ፤ እናንተስ ፡ ቀጥሉ ፤ ኮሼቮዩ ፡ ከባልቴት ፡ ሴት ፡ የማይሻል ፡ ስለሆነ ፡ እሱን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ለማስወጣት ፡ ?ፈለግነው ። ኮሼቮይ ፡ እንዲሆን ፡ የምንፈልገው ፡ አንድ ፡ እውነተኛ ፡ ወንድ ፡ ነው ፡» እያሉ ፡ ጮኹ ።

«አሁን ፡ ኮሼቮይ ፡ እንዲሆን ፡ ማንን ፡ ትመርጣላችሁ?»

«ኩኩቤንኮን ፡ ምረጡ!» የሚል ፡ ድምጽ ፡ ከአንድ ፡ ወገን ፡ ይሰማል ።

በሌላ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ «ኩኩቤንኮን ፡ አንፈልግም ። እሱ ፡ የእናቱ ፡ ወተት ፡ ከአፉ ፡ ያልደረቀ ፡ ገና ፡ ሕፃን ፡ ነው!» እያሉ ፡ ይጮኻሉ ።

«ሺሎ ፡ ኮሼቮይ ፡ ይሁን ፡ ሺሎን ፡ ምረጡ!»

«የለም ፡ ሺሎ ፡ ክፉ ፡ ወስላታ ፡ ነው ። ይህ ፡ የውሻ ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ታታር ፡ ሌባ ፡ ሆኖ ፡ ምን ፡ ኮዛክ ፡ ሊባል ፡ ይቻላል! ሰካራሙ ፡ ሺሎ ፡ ገሃነብ ፡ ይግባ!»



«ቦሮዳትይ! ቦሮዳትይን ፡ ኮሼቮያችን ፡ እናድርግ!»

«ቦሮዳትይን ፡ አንፈልግም ፤ ወዲያ ፡ ገደል ፡ ይግባ!»

ታራስ ፡ ቡልባ ፡ በበኩሉ ፡ እየዞረ ፡ «ለኪርዲያጋ ፡ ጩኹ!» እያለ ፡ ይመክር ፡ ነበር ።

ሕዝቡም ፡ «ኪርዲያጋ! ኪርዲያጋ!» እያለ ፡ ጩኸቱን ፡ ቀጠለ ።

«ቦሮዳትይ! ቦሮዳትይ!»

«ኪርዲያጋ! ኪርዲያጋ!»

«ሺሎ!»

«ሺሎ ፡ ገደል ፡ ይግባ!»

«ኪርዲያጋ!»

ተመራጮቹ ፡ ሰዎች ፡ ከውስጥ ፡ ሆነው ፡ የሚጐትጐቱ ፡ እንዳይመስልባቸው ፡ ስማቸው ፡ ሲጠራ ፡ ወዲያው ፡ ከሕዝቡ ፡ ፈንጠር ፡ እያሉ ፡ ቆሙ ።

«ኪርዲያጋ! ኪርዲያጋ!» የሚለው ፡ ጩኸት ፡ እየገነነ ፡ ሔደ ።

«ቦሮዳትይ!» የሚል ፡ ድምጽም ፡ ይሰማል ።

በነዚህ ፡ በሁለቱ ፡ ተመራጮች ፡ ደጋፊዎች ፡ መካከል ፡ የተፈጠረውን ፡ ክርክር ፡ ለመወሰን ፡ ወዲያው ፡ በመራጮቹ ፡ መካከል ፡ ዱላ ፡ ተነሳና ፡ በቡጢ ፡ ከተቀጣቀጡ ፡ በኋላ ፡ የኪርዲያጋ ፡ ወገን ፡ ድል ፡ አደረገ ።

«ሒዱና ፡ ኪርዲያጋን ፡ አምጡት!» ሲባል ፡ ስድስት ፡ የሚሆኑ ፡ ኮዛኮች ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ቮድካ ፡ ጠጥተው ፡ ስለነበር ፡ መራመድ ፡ እቅቶአቸው ፡ እየተወላገዱ ፡ የመመረጡን ፡ ዜና ፡ ለኪርዲያጋ ፡ ለመንገር ፡ ሔዱ ።

ጠና ፡ ያለው ፡ ብልጥ ፡ ኮዛክ ፡ ኪርዲያጋ ፡ ስለሚደረገው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የማያውቅ ፡ መስሎ ፡ ጐጆው ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ።

«ምን ፡ ትፈልጋላችሁ ፡ ወዳጆቼ?» ሲል ፡ ጠየቃቸው ።

«ና ፤ ኮሼቮይ ፡ እንድትሆን ፡ ተመርጠሃል ፡» አሉት ።

«ይቅርታ ፡ አድርጉልኝ ፡ ወዳጆቼ! እንዲህ ፡ ያለው ፡ ክብር ፡ ለኔ ፡ ይበዛብኛል ፡ ደግሞ ፡ እኔ ፡ ብሎ ፡ ኮሼቮይ! ምነው ፡ በሠራዊቱ ፡ ውስጥ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ጠፋ ፡ እንዴ?» እያለ ፡ ተግደረደረ ።

«ና ፡ ነው ፡ እኮ ፡ የምልህ!» አለና ፡ አንዱ ፡ ዛፖሮዥያን ፡ ጮኸበት ።

ሌሎች ፡ ሁለቱ ፡ ደግሞ ፡ ብብትና ፡ ብብቱን ፡ ይዘው ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ለመከራከር ፡ ቢሞክር ፡ «ምን ፡ ይጎትትሃል ፡ አንተ ፡ የሰይጣን ፡ ልጅ! የተሰጠህን ፡ ክብር ፡ መቀበል ፡ ነው ፡ አንት ፡ ውሻ!» በማለት ፡ እየሰደቡ ፡ በርግጫና ፡ በጉሽም ፡ እየጎሻሸሙ ፡ ጎትተው ፡ ወደ ፡ አደባባይ ፡ ወሰዱት ።

በዚህ ፡ ሁናቴ ፡ ኪርዲያጋ ፡ አደባባዩን ፡ ከበው ፡ ከተሰበሰቡት ፡ ኮዛኮች ፡ መካከል ፡ ቀረበ ።

አቅራቢዎቹም ፡ «ታድያስ ፡ ጎበዝ ፡ ይህ ፡ ኮዛክ ፡ ኮሼቮይ ፡ እንዲሆን ፡ ሁላችሁም ፡ ተቀብላችሁታል? » ብለው ፡ ጠየቁ ።

ሕዝቡም ፡ «ተስማምተናል!» በማለት ፡ ሜዳው ፡ እስኪያስተጋባ ፡ ድረስ ፡ ጮኸ ።

ከሹማምንቱ ፡ አንዱ ፡ የሥልጣን ፡ ምልክት ፡ የሆነውን ፡ በትር ፡ አነሳና ፡ ለአዲሱ ፡ ኮሼቮይ ፡ አበረከተ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ኪርዲያጋ ፡ ልማድ ፡ ነውና ፡ አልቀበልም ፡ በማለት ፡ ተግደረደረ ። ሹሙ ፡ እንደገና ፡ አበረከተው ። ኪርዲያጋም ፡ አሁንም ፡ እምቢ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ለሶስተኛ ፡ ጊዜ ፡ ሲያቀርብለት ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ ተቀበለ ። ሥልጣኑን ፡ መረከቡ ፡ ሲረጋገጥ ፡ በዚያ ፡ የተሰበሰቡት ፡ ሁሉ ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ ጮኹ ። ሜዳውም ፡ ጮኸታቸውን ፡ ተቀብሎ ፡ አስተጋባ ። ከዚያ ፡ ጢማቸውና ፡ ጠጉራቸው ፡ የሸበተ ፡ ሽማግሌ ፡ ኮዛኮች ፡ ከሕዝቡ ፡ ነጠል ፡ ብለው ፡ ወጡና ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በዝናብ ፡ የረጠበውን ፡ ጭቃ ፡ አፍሰው ፡ በኪርዲያጋ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ አስቀመጡ ። ጭቃውም ፡ ከጭንቅላቱ ፡ ተንጠፍጥፎ ፡ በጢሙና ፡ በጉንጮቹ ፡ ላይ ፡ እየወረደ ፡ ፊቱን ፡ አለበሰው ። ኪርዲያጋ ፡ ግን ፡ ሳይንቀሳቀስ ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ቆሞ ፡ ስለሰጡት ፡ ክብር ፡ ኮዛኮቹን ፡ አመሰገናቸው ።

በዚህ ፡ መሠረት ፡ የጫጫታ ፡ ምርጫ ፡ ተፈጸመ ። በምርጫው ፡ ውጤት ፡ ከቡልባ ፡ ይበልጥ ፡ የተደሰተ ፡ መኖሩን ፡ እንጃ ። ቡልባ ፡ በቀድሞው ፡ ኮሼቮይ ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ ቂም ፡ ከመበቀሉም ፡ በላይ ፡ ኪርዲያጋ ፡ በባሕርም ፡ በምድር ፡ በብዙ ፡ ስፍራ ፡ ወታደራዊ ፡ ልፋትን ፡ አብሮት ፡ የተቀበለ ፡ የጥንት ፡ ጓደኛው ፡ ስለነበር ፡ በመመረጡ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደስታ ፡ ተሰማው ። ወዲያው ፡ ሕዝቡ ፡ ምርጫውን ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ለፈንጠዝያ ፡ ተበታተነና ፡ አስታፕና ፡ አንድሬይ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ አይተውት ፡ የማያውቁ ፡ ታላቅ ፡ የፈንጠዝያ ፡ ሁከት ፡ ተመለከቱ ። የመጠጥ ፡ ቤቶች ፡ እየተበረበሩ ፡ ቮድካና ፡ ሌላውም ፡ መጠጥ ፡ ገንዘብ ፡ ሳይከፈልበት ፡ ተዘረፈ ። ባለመደብሮቹም ፡ ሕይወታቸውን ፡ ስለአተረፉ ፡ ብቻ ፡ ከመደሰት ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ሊያደርጉ ፡ አልቻሉም ። ኮዛኮቹ ፡ ግን ፡ ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ ወታደራዊ ፡ ዘፈን ፡ ሲዘፍኑ ፡ አደሩ ። ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሙዚቃ ፡ መሣሪያ ፡ የያዙ ፡ ዘፋኞች ፡ በየመንገዱ ፡ እየዞሩ ፡ ሲዘፍኑ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልግሎት ፡ በሴቹ ፡ ውስጥ ፡ የተቀመጡ ፡ መዘምራንም ፡ የዛፖሮዥያኑን ፡ ተግባር ፡ ለመቀደስ ፡ ሲያዜሙ ፡ አደሩ ። በመጨረሻ ፡ መጠጡና ፡ ድካሙ ፡ እነዚህን ፡ ብርቱ ፡ ሰዎች ፡ አደከማቸው ። በየስፍራው ፡ አንድ ፡ ኮዛክ ፡ ሜዳው ፡ ላይ ፡ ሲወድቅ ፡ ይታይ ፡ ጀመር ። እዚህ ፡ አንድ ፡ ኮዛክ ፡ ከጓደኛው ፡ ጋር ፡ ተቃቅፎ ፡ ሁለቱም ፡ ተያይዘው ፡ ይወድቃሉ ። እዚያ ፡ ብዙ ፡ ኮዛኮች ፡ አንዱ ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ ተደራርበው ፡ ተከምረዋል ። አንዱ ፡ ደግሞ ፡ ሜዳው ፡ ላይ ፡ ተዘርግቶ ፡ የሚተኛበትን ፡ ስፍራ ፡ ይመርጣል ። ከሁሉም ፡ ብርቱ ፡ የሆነው ፡ ጠንካራ ፡ ኮዛክ ፡ አሁንም ፡ ስልት ፡

የሌለው ፡ ዘፈን ፡ እያጉተመተመ ፡ ጥቂት ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ ስካሩ ፡ አሸንፎት ፡ ወደቀ ።

አሁን ፡ ሴቹ ፡ በሞላ ፡ እንቅልፍ ፡ ተኛ ።

## ምዕራፍ ፡ አራት ።

በማግሥቱ ፡ ታራስ ፡ ቡልባ ፡ ከአዲሱ ፡ ኮሼቮይ ፡ ጋር ፡ ተገናኝቶ ፡ ዛፖሮዥያኖቹን ፡ ወደዘመቻ ፡ ለመላክ ፡ የሚቻልበትን ፡ ዘዴ ፡ መመካከር ፡ ጀመረ ። ኮሼቮዩ ፡ ብልጥና ፡ ጮሌ ፡ ኮዛክ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ዛፖሮዥያኖችን ፡ ጠንቅቆ ፡ ስለሚያውቅ ፡ እንዲህ ፡ በማለት ፡ ንግግሩን ፡ ጀመረ ፤

«መሃላችንን ፡ በምንም ፡ መንገድ ፡ ልንሰብር ፡ አንችልም ፡ ግን ፡ አንድ ፡ መንገድ ፡ አለ ። መሃላችንን ፡ ሳንሰብር ፡ ዘዴ ፡ እንፈልጋለን ። ሕዝቡ ፡ በእኔ ፡ ትእዛዝ ፡ ሳይሆን ፡ በፈቃዱ ፡ እንዲሰበሰብ ፡ አድርግ ። ይህን ፡ ለማድረግም ፡ ከማንም ፡ ይልቅ ፡ አንተ ፡ ትሻላለህ ። ከዚያ ፡ እኔና ፡ ሌሎቹ ፡ ሹማምንት ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ እንዳላወቅን ፡ ሆነን ፡ ሮጠን ፡ ወደ ፡ አደባባዩ ፡ እንሔዳለን ።»

ይህን ፡ በተነጋገሩ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ባልሞላ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ነጋሪቱ ፡ መመታት ፡ ጀመረ ። ኮዛኮቹ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ስካርና ፡ ድካም ፡ ቢሰማቸው ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ተሰበሰቡ ። አንድ ፡ ሚሊዮን ፡ የሚሆኑ ፡ የኮዛክ ፡ ቆቦች ፡ በአደባባዩ ፡ ብቅ ፡ ብቅ ፡ አሉ ። «ማን ፡...? ለምን ፡ ...? ምንድነው ፡ ነገሩ?» እያሉ ፡ ያጉረመርሙ ፡ ነበር ። ግን ፡ ማንም ፡ መልስ ፡ አልሰጣቸው ። በመጨረሻ ፡ ከየስፍራው ፤ «የኮዛክ ፡ ጉልበታችን ፡ በከንቱ ፡ ተበላሸ ፤ ጦርነት ፡ የለም! አለቆቻችን ፡ እየሰነፉ ፡ ሔዱ ፤ ዓይኖቻቸውንም ፡ ሞራ ፡ ሸፈነው! በዚህ ፡ ዓለም ፡ ምንም ፡ ትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ ጠፋ!» የሚል ፡ የቁጣ ፡ ድምጽ ፡ ይሰማ ፡ ጀመር ። ሌሎቹ ፡ ኮዛኮች ፡ በመጀመሪያ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ከአዳመጡ ፡ በኋላ ፤ «በእውነትም ፡ በዓለም ፡



ላይ ፡ ትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ የለም!» በማለት ፡ ሁሉም ፡ ተያይዘው ፡ ማጉረምረም ፡ ቀጠሉ ። ሹማምንቶቹም ፡ ነገሩን ፡ ያላወቁ ፡ መስለው ፡ ሲገረሙ ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ ኮሼቮይ ፡ ነጠል ፡ ብሎ ፡ «ፍቀዱልኝ ፡ ወንድሞቼ ፡ አንድ ፡ ንግግር ፡ ላድርግ ፡» አለ ።

«በል ፡ ተናገር!»

«የንግግሬ ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የተከበራችሁት ፡ ወንድሞቼ ፡ ከኔ ፡ ይበልጥ ፡ ብታውቁት ፡ ብዙ ፡ ዛፖሮዥያኖች ፡ ከየአይሁዱ ፡ የመጠጥ ፡ መደብርና ፡ እንዲሁም ፡ ከራሳቸው ፡ ወንድሞች ፡ በመበደር ፡ ዕዳ ፡ ስለዋጣቸው ፡ አሁን ፡ ከየትም ፡ ሥፍራ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ በዱቤ ፡ ሊያገኙ ፡ አልቻሉም ። ዳግመኛም ፡ ልገልጽላችሁ ፡ የምፈልገው ፡ ጦርነት ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ የማያውቁ ፡ ብዙ ፡ ጐልማሶች ፡ እንዳሉ ፡ ሲሆን ፡ ወዳጆቼ ፡ እናንተም ፡ እንደምታውቁት ፡ ማንም ፡ ወጣት ፡ ያለጦር ፡ ሊኖር ፡ አይችልም ። አንድ ፡ ከሃዲ ፡ እንኳን ፡ ያልገደለ ፡ እንዴት ፡ ዛፖሮዥያን ፡ ሊባል ፡ ይቻላል?»

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ቡልባ ፤ «መልካም ፡ ይናገራል ፡» ብሎ ፡ አሰበ ።

ኮሼቮይ ፡ ወዲያው ፡ ንግግሩን ፡ ቀጠለ ፤

«ነገር ፡ ግን ፡ ይህንን ፡ ስል ፡ ሰላም ፡ ይፍረስ ፡ ማለቴ ፡ አይምሰላችሁ ፤ እውነቱን ፡ ለመግለጽ ፡ ብቻ ፡ ስል ፡ ነው ። ደግሞስ ፡ ያለንን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እስቲ ፡ ተመልከቱት ። በእውነቱ ፡ የሚያሳፍረን ፡ ነው ። ሴቹ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እርዳታ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ዓመታት ፡ ድርጅት ፡ ሲኖር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ግን ፡ የውጭ ፡ መልኩ ፡ ይቅርና ፡ ከውስጥ ፡ እንኳን ፡ ለሥዕሎቹ ፡ ምንም ፡ ጌጥ ፡ የለውም ። ለሥዕሎቹ ፡ ጠርዝም ፡ ማስጌጫ ፡ ብር ፡ አቅልጦ ፡ ለመሥራት ፡ እንኳን ፡ ማንም ፡ የሞከረ ፡ የለም ። ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ አንዳንድ ፡ ኮዛኮች ፡ በኑዛዜ ፡ ካወረሱት ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ንብረት ፡ የለውም ። አውራሾቹም ፡ ሃብታቸውን ፡ በሙሉ ፡ በቁማቸው ፡

የጠጡበት ፣ ስለሆኑ ፣ የተናዘዙት ፣ ሃብትም ፣ ዋጋ ፣ ያለው ፣
አይደለም ። ይህንንም ፣ ስላችሁ ፣ በከሐዲዎቹ ፣ ላይ ፣ እንዝ
መትባቸው ፣ ማለቴ ፣ አይደለም ። ለሡልጣኑ ፣ የሰላም ፣ ቃል ፣
ኪዳን ፣ ገብተናል ። ቃል ፣ ኪዳንም ፣ ስንገባ ፣ በሃይማኖታ
ችን ፣ ምለን ፣ ነውና ፣ ብናፈርሰው ፣ ለነፍሳችን ፣ ከፍ ፣ ያለ ፣
ኃጢአት ፣ ነው ።»

እዚህ ፣ ላይ ፣ ቡልባ ፤ «የዚህ ፣ ሁሉ ፣ መዘላበድ ፣ ትርጉ
ሙ ፣ ምን ፣ ይሆን?» እያለ ፣ ይገረም ፣ ጀመር ።

«ታዲያ ፣ እንግዲህ ፣ ወንድሞቼ ፤ እኛ ፣ ጦርነቱን ፣ ለመ
ጀመር ፣ አንችልም ፣ ማለት ፣ ነው ። የጨዋነት ፣ ክብራችን ፣
አይፈቅድልንም ፣ ነገር ፣ ግን ፣ የአረጀው ፣ አእምሮዬ ፣ እንደ
ሚያሳስበኝ ፣ ጐልማሶቻችንን ፣ በጀልባ ፣ ልከን ፣ የአናቶሊያን ፣
ወደብ ፣ ትንሽ ፣ እንዲያስሱ ፣ ማድረግ ፣ እንችል ፣ ይሆናል ።
ታዲያስ ፣ ምን ፣ ይመስላችሁአል ፣ ወንድሞቼ?»

«ምራን ፣ እንሒድ ፣ ምራን!» እያለ ፣ ሕዝቡ ፣ ከሁሉም ፣
ወገን ፣ ተንጫጫ ።

«ለሃይማኖታችን ፣ ስንል ፣ ከንዳችንን ፣ ለመንተራስ ፣
ዝግጁ ፣ ነን!»

ኮሼቮይ ፣ ደነገጠ ፤ የሰላሙ ፣ ስምምነት ፣ እንዲፈርስ ፣
ስለማይፈልግ ፣ ሕዝቡን ፣ በሞላ ፣ ለዘመቻ ፣ ለመቀስቀስ ፣
አላሰበም ፣ ነበር ።

«ሌላ ፣ ንግግር ፣ እንዳደርግ ፣ ፍቀዱልኝ ፣ ወንድሞቼ ፣»
ብሎ ፣ ቢጠይቅ ፣ «በቃህ! የመጀመሪያውን ፣ ጣዕሙን ፣ ታጠ
ፋዋለህ ፣» እያሉ ፣ ጮሁበት ።

«እንዲህ ፣ ካላችሁ ፣ ይሁን ፤ እሺ ፣ እኔ ፣ እንደፈቃዳ
ችሁ ፣ ታዛዥ ፣ ባርያችሁ ፣ ነኝ ። ማንም ፣ ሰው ፣ እንደሚያ
ውቀው ፣ ቅዱስ ፣ መጽሐፍ ፣ እንደሚለው ፣ የሕዝብ ፣ ድምጽ ፣
የእግዚአብሔር ፣ ድምጽ ፣ ማለት ፣ ነው ። ከመላው ፣ ሕዝብ ፣
የተሻለ ፣ ምንም ፣ ሸንጐ ፣ የለም ። ግን ፣ አንድ ፣ ያሰብኩት ፣
ነገር ፣ አለ ። ወንድሞቼ ፤ እንደምታውቁት ፣ ሡልጣኑ ፣ የጐ



ልማሶቻችንን ፣ አነስተኛ ፣ ዘመቻ ፣ ያለቅጣት ፣ ችላ ፣ ብሎ ፣
የሚያልፈው ፣ አይደለም ። ስለዚህ ፣ እኛ ፣ ኃይላችንን ፣ አደር
ጅተን ፣ ተዘጋጅተን ፣ ልንጠብቀው ፣ ይገባል ፤ ማንንም ፣
የምንፈራበት ፣ ምንም ፣ ምክንያት ፣ የለንም ። ወዲህም ፣
ደግሞ ፣ እኛ ፣ በሌለንበት ፣ ታታሮች ፣ ሴቹን ፣ ሊወርሩ ፣ ይ
ችላሉ ። እነዚያ ፣ ውሻ ፣ ቱርኮች ፣ ግን ፣ ጌታቸው ፣ ባለበት ፣
ቤት ፣ ደፍረው ፣ አይመጡም ፤ ሆኖም ፣ ከኋላ ፣ ከኋላ ፣ መና
ከሳቸው ፣ አይቀርም ። እውነቱን ፣ ለመናገር ፣ እኛ ፣ አሁን ፣
በቂ ፣ ጀልባ ፣ የለንም ፤ ሁሉንም ፣ የሚያዘምት ፣ በቂ ፣ ባሩ
ድም ፣ ተወቅጦ ፣ አልተዘጋጀም ። እኔ ፣ በበኩሌ ፣ ግን ፣ ለፍ
ላጐታችሁ ፣ አገልጋይ ፣ ባርያ ፣ እንደመሆኔ ፣ መጠን ፣ የሐሳባ
ችሁን ፣ ደጋፊ ፣ ነኝ ።»

ተንኮለኛው ፣ አታማን ፣ ይህንን ፣ ተናግሮ ፣ ዝም ፣ አለ ።
ሕዝቡ ፣ በየፊናው ፣ ተከፋፍሎ ፣ ይመካከር ፣ ጀመረ ። የየመ
ንደሩ ፣ አለቆችም ፣ ራስ ፣ ለራስ ፣ ገጥመው ፣ ሸንጐ ፣ ያዙ ።
አጋጣሚ ፣ ሆኖ ፣ ወኔአቸውን ፣ ለመግታት ፣ ያልቻሉት ፣ ጥ
ቂቶች ፣ ብቻ ፣ ስለነበሩ ፣ ይህ ፣ ጠቢብ ፣ የሆነ ፣ የጥንቃቄ ፣
ምክር ፣ ጸደቀ ።

ወዲያው ፣ ከድኔፕር ፣ ማዶ ፣ ወዳለው ፣ የጦር ፣ ሠራዊ
ቱ ፣ የመሣሪያና ፣ የንብረት ፣ ማከማቻ ፣ ሰዎች ፣ ተላኩ ። የተ
ማረከው ፣ ንብረትና ፣ የጦር ፣ መሣሪያ ፣ በከፊል ፣ የሚቀ
መጠው ፣ በዚያ ፣ ሥፍራ ፣ በቄጠማው ፣ መካከል ፣ ከውኃ
ው ፣ ውስጥ ፣ ተቀብሮ ፣ ነበር ። የተላኩት ፣ ሰዎች ፣ ወደዚያ ፣
ሲሔዱ ፣ የቀሩት ፣ ወደ ፣ ጀልባዎቹ ፣ ሔደው ፣ ለዘመቻው ፣
ዝግጅት ፣ ጀመሩ ። ከመቅጽበት ፣ ወደቡ ፣ ሕዝብ ፣ ይርመ
ሰመስበት ፣ ጀመር ። አናጢዎች ፣ መጥረቢያቸውን ፣ እየ
ያዙ ፣ መጡ ። ጸሐይ ፣ ያጠየማቸው ፣ ትከሻማ ፤ ጢማቸው ፣
በሽበት ፣ የገረጣ ፤ ጠና ፣ ያሉ ፣ ዛፖሮዥያኖች ፣ ሱሪአቸውን ፣
ከፍ ፣ ከፍ ፣ አድርገው ፣ ውኃ ፣ ውስጥ ፣ በመግባት ፣ ጀልባ
ዎቹን ፣ በገመድ ፣ ወደ ፣ ወንዝ ፣ ይጐትቱ ፣ ጀመር ። የቀሩት ፣

የደረቁ ፡ ግንዶችና ፡ አዲስ ፡ የተቆረጡ ፡ ዛፎች ፡ እየጐተቱ ፡ የተሰነጠቁ ፡ ጀልባዎችን ፡ ማደስ ፡ ያዙ ። ጠና ፡ ያሉትና ፡ ልምድ ፡ ያላቸው ፡ ለወጣቶቹ ፡ ሥራውን ፡ ያሳያሉ ፤ የሥራው ፡ ጫጫታ ፡ ከየሥፍራው ፡ አስተጋባ ።

ወዲያው ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ጀልባ ፡ ወደ ፡ ወደብ ፡ እየቀረበ ፡ መጣ ። በውስጡ ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ገና ፡ ከሩቁ ፡ እጃቸውን ፡ ያወዛውዙ ፡ ነበር ። ሰዎቹም ፡ የተበጣጠሰ ፡ ልብስ ፡ የለበሱ ፤ እንዲያውም ፡ ግማሾቹ ፡ ከሸሚዝና ፡ በአፋቸው ፡ ከያዙት ፡ አጫጭር ፡ የትንባሆ ፡ ማጨሻ ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ያልነበራቸው ፡ ኮዛኮች ፡ ናቸው ። የመታረዛቸው ፡ ምክንያትም ፡ አንድ ፡ አደጋ ፡ ደርሶባቸው ፡ ወይም ፡ ልብሳቸውን ፡ ሸጠው ፡ እንደፈነጠዙበት ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ዕድሜው ፡ ወደ ፡ ሃምሳ ፡ ዓመት ፡ የሚሆን ፡ ትከሻማ ፡ አጭር ፡ ኮዛክ ፡ ከሌሎቹ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ከሁሉም ፡ ይበልጥ ፡ እጁን ፡ እያወዛወዘ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ድምጽ ፡ ይጮኻል ። ነገር ፡ ግን ፡ ድምጹ ፡ በሠራተኞቹ ፡ ጫጫታ ፡ ተውጦ ፡ አልተሰማም ።

ጀልባዋ ፡ ወደ ፡ ወደቡ ፡ ጠጋ ፡ ስትል ፡ ኮሼቮዩ ፤ «ምን ፡ ወሬ ፡ ይዛችኋል?» ብሎ ፡ ጠየቀ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ በወደቡ ፡ ዳር ፡ የነበሩት ፡ ሠራተኞች ፡ ሁሉ ፡ ሥራቸውን ፡ አቁመው ፡ ቀና ፡ አሉ ።

በጀልባው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ጠብደል ፡ ኮዛክ ፤ «መጥፎ ፡ ወሬ!» ሲል ፡ መለሰ ።

«ምንድነው ፡ እሱ?»

«ንግግር ፡ እንዳደርግ ፡ ትፈቅዱልኛላችሁ ፡ ወንድሞቼ?»

«በል ፡ ተናገር!»

«ወይስ ፡ ራዳ ፡ እንዲሰበሰብ ፡ ትፈልጋላችሁ?»

«ተናገር ፡ ሁላችንም ፡ እዚህ ፡ ነን ፡» ተባለና ፡ ሕዝቡ ፡ ከያለበት ፡ ተሰበሰበ ።

«በሄትማንቺና[1] ፡ ውስጥ ፡ ስለሚፈጸመው ፡ ተግባር ፡ አልሰማችሁም?»



«ምንድነው ፡ የተፈጸመው?» አለና ፡ አንድ ፡ የመንደር ፡ አለቃ ፡ ጠየቀው ።

«እንዴታ! ምንም ፡ ነገር ፡ እንዳትሰሙ ፡ ታታሮች ፡ ጆሮአችሁን ፡ ወትፈውታል ፡ መሰለኝ ።»

«በላ ፡ የሆነውን ፡ ንገረን ።»

«እዚያ ፡ የሚፈጸሙት ፡ ነገሮች ፡ ማንም ፡ ተወልዶ ፡ የተጠመቀ ፡ ሰው ፡ አይቶአቸው ፡ የማያውቅ ፡ ናቸው ።»

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ከሕዝቡ ፡ መሃል ፡ አንዱ ፡ ትዕግሥቱ ፡ ያለቀ ፡ ኮዛክ ፤ «የሆነውን ፡ ነገር ፡ ንገረን ፡ የውሻ ፡ ልጅ!» አለና ፡ ጮኸ ።

«የተቀደሱት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖቻችን ፡ እንኳ ፡ የኛ ፡ ያልሆኑበት ፡ ጊዜ ፡ መጥቶአል ።»

«እንዴት ፡ ነው ፡ የኛ ፡ ያልሆኑት?»

«በኪራይ ፡ ለአይሁዶች ፡ ተሰጡ ፤ አይሁዱ ፡ በቅድሚያ ፡ ካልተከፈለው ፡ ቅዳሴ ፡ አይደረግም ።»

«ሰውየው ፡ አብድዋል ፡ መሰለኝ!»

«ደግሞ ፡ የተረገመው ፡ ውሻ ፡ አይሁድ ፡ በተቀደሰው ፡ የፋሲካ ፡ መክለፍታችን ፡ ላይ ፡ ባልጸዳ ፡ እጁ ፡ ምልክት ፡ ካላደረገበት ፡ ሊፈተት ፡ አይችልም ።»

«ይህ ፡ ሰው ፡ ይዋሻል ፡ ወንድሞቼ! ያልጸዳ ፡ አይሁድ ፡ በተቀደሰው ፡ የፋሲካ ፡ መክለፍት ፡ ላይ ፡ እርማውን ፡ ሊያደርግ ፡ አይችልም!»

«አዳምጡኝ! ይህ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ሮማውያን ፡ ቀሳውስት ፡ በኡክሬይን ፡ በሞላ ፡ በጋሪ ፡ ሲጋልቡ ፡ ይታያሉ ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ችግሩ ፡ ጋሪያቸው ፡ አይደለም ፤ ጉዱ ፡ በፈረስ ፡ ፈንታ ፡ ለጋሪያቸው ፡ መጐተቻ ፡ እርቶዶክስ ፡ ክርስቲያኖችን ፡ መጫናቸው ፡ ነው ። አዳምጡኝ! ይህ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። እንደሚወራው ፡ የአይሁድ ፡ ሴቶች ፡ ከኛ ፡ ቀሣውስት ፡ መጐናፀፊያ ፡ እየወሰዱ ፡ የውስጥ ፡ ልብስ ፡ ሰፍተውታል ፡ ይባላል ። ይኸውላችሁ ፡ ወንድሞቼ ፡ በኡክሬይን ፡ የሚ

ሠራው ፡ ሥራ! ታዲያ ፡ እናንተ ፡ እዚህ ፡ በፈንጠዝያ ፡ ተቀም ጣችሁ ፡ ደግሞ ፡ ታታሮች ፡ አስደንግጠዋችኋል ፡ መሰለኝ ። ዓይንም ፡ ጆሮም ፡ እንደሌለው ፡ ድንጋይ ፡ ሆናችሁ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸመው ፡ ተግባር ፡ ምንም ፡ አታውቁ ።»

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ አንገቱን ፡ አቀርቅሮ ፡ ያዳምጥ ፡ የነበረው ፡ ኮሼቮይ ፡ «ቆይ ፡ ቆይ!» አለ ።

እንዲህ ፡ ባለው ፡ ሰዓት ፡ በመጀመሪያ ፡ ስሜታቸው ፡ ሳይሸነፉ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ በቁጣ ፡ እስኪገነፍሉ ፡ ድረስ ፡ ነገ ሩን ፡ በአዕምሮአቸው ፡ ማሰላሰል ፡ የሁሉም ፡ ዛፖሮዥያን ፡ ጠባይ ፡ ነበር ። ኮሼቮዩ ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ነገሩን ፡ አሰላ ስሎ ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ «ቆይ ፡ እስቲ ፡ ንገረኝ! እናንተ ፡ ምን ፡ ስታደርጉ ፡ ነው ፡ አባቶቻችሁን ፡ ለአጋንንት ፡ ይሰጣቸውና ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ እናንተ ፡ ምን ፡ ታደርጉ ፡ ነበር? ጐራዴ ፡ የላችሁም? እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ሕግ ፡ ወጥ ፡ ሥራ ፡ እንዴት ፡ ፈቀዳችሁ?»

«የፖሊሾቹ ፡ ቁጥር ፡ አምሳ ፡ ሺ ፡ ሲሆን ፡ እናንተስ ፡ ብትሆኑ ፡ ምን ፡ ልታደርጉ ፡ ኖሮአል? ደግሞ ፡ የእኛንም ፡ ኃጢአት ፡ መደበቅ ፡ አይጠቅምም ፡ ከኛውም ፡ መካከል ፡ የነዚያን ፡ ኃይማኖት ፡ የተቀበሉ ፡ አንዳንድ ፡ ውሾች ፡ አል ጠፉም ።»

«ሄትማናችሁና ፡ ኰሎኔሎቻችሁ ፡ የት ፡ ነበሩ?»

«በኰሎኔሎቻችን ፡ ላይ ፡ ከደረሰባቸው ፡ ነገር ፡ እምላክ ፡ ይሰውረን!»

«እንዴት?»

«ሄትማናችን ፡ በብረት ፡ ድስት ፡ ተቀቅሎ ፡ ዋርሶ ፡ ወድ ቆአል ፤ የኰሎኔሎቻችን ፡ ጭንቅላቶቻቸውና ፡ ክንዶቻቸው ፡ ሕዝብ ፡ እንዲያያቸው ፡ ከአደባባይ ፡ አደባባይ ፡ ይዞራሉ ። ይህ ፡ ነው ፡ በኰሎኔሎቻችን ፡ ላይ ፡ የደረሰባቸው!»

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ እንቅስቃሴ ፡ ጀመረ ። ኃይለኛ ፡ ሞገድ ፡ ከመንሣቱ ፡ በፊት ፡ ባሕር ፡ ጸጥ ፡ እንደሚል ፡ ለጥቂ



ት ፡ ጊዜ ፡ በፀጥታ ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ ሁሉም ፡ በአንድነት ፡ ንግ ግር ፡ ሲጀምሩ ፡ ወደቡ ፡ በድምጻቸው ፡ ተናወጸ ።

«እንዴት ፡ አይሁዶች ፡ የክርስቲያን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ይከራያሉ! ሮማውያን ፡ ቄሶች ፡ እንዴት ፡ የኦርቶዶክስ ፡ ክርስቲያኖችን ፡ ለጋሪ ፡ መጐተቻ ፡ ይጭኑአቸዋል! እንዴ ት! ለነዚህ ፡ ለተረገሙ ፡ ካቶሊኮች ፡ ተብሎ ፡ በሩሲያ ፡ ም ድር ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ይሠራል! ኰሎኔ ሎቻችንና ፡ ሄትማናችንን ፡ እንዲህ ፡ እስኪያደርጉዋቸው ፡ ድረስ! የለም ፡ ይህ ፡ አይሆንም ፡ ይህ ፡ አይደረግም!»

እንዲህ ፡ ያሉት ፡ ቃላት ፡ በየሥፍራው ፡ ይሰሙ ፡ ነበር ።

ዛፖሮዥያኖቹ ፡ ለንዴታቸው ፡ መንገድ ፡ ሰጡት ። ኃይ ላቸውም ፡ ተሰማቸው ። አሁን ፡ ስሜታቸው ፡ ቀላል ፡ አዕም ሮ ፡ ያለው ፡ የተጨዋች ፡ ሕዝብ ፡ ስሜት ፡ ሳይሆን ፡ የጠን ካራ ፡ በቀላሉ ፡ የማይናደዱና ፡ ከተናደዱ ፡ ግን ፡ የማይበርዱ ፡ ጥብቅ ፡ ሰዎች ፡ ስሜት ፡ ነው ።

«አይሁዶችን ፡ በሞላ ፡ መስቀል ፡ ነው ፤ ከቄሶቻችን ፡ መጐናጸፊያ ፡ ለሴቶቻቸው ፡ ቀሚስ ፡ እንዳይሰፉ ፤ በተቀደ ሰው ፡ የፋሲካ ፡ መክለፍታችን ፡ ላይም ፡ ምልክታቸውን ፡ እንዳያደርጉ ፡ መቀጣት ፡ አለባቸው! እነሆን ፡ እርጉሞች ፡ ሰብስቦ ፡ ድኔፐር ፡ መጨመር ፡ ነው!» የሚል ፡ ጩኸት ፡ ከሕ ዝቡ ፡ መሃል ፡ ተሰማ ። ከመካከላቸው ፡ አንዱ ፡ የተናገራ ቸው ፡ እነዚህ ፡ ቃላት ፡ የሁሉንም ፡ ደም ፡ ስለአፈላው ፡ በአ ቅራቢያው ፡ መንደር ፡ ያሉትን ፡ አይሁዶች ፡ ለመፍጀት ፡ ሁሉም ፡ ገሰገሱ ።

ያልታደሉት ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በፍርሃት ፡ ተሸ ብረው ፡ በባዶ ፡ የቮድካ ፡ በርሚሎች ፤ በየምድጃው ፡ በሴቶ ቻቸው ፡ ቀሚስ ፡ ውስጥ ፡ እንኳን ፡ ሳይቀር ፡ ተደበቁ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የትም ፡ ቢገቡ ፡ ከኰዛኮች ፡ አላመለጡም ።

እንደ ፡ አጣና ፡ ረጅምና ፡ ቀጭን ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ አይሁ ድ ፡ ኰዛኮቹ ፡ በደረሱበት ፡ ጊዜ ፡ ከጓደኞቹ ፡ መካከል ፡ ወጣ ፡

ብሎ ፡ በፍርሃት ፡ እየተንቀጠቀጠ ፡ «የተከበራችሁ ፡ ጌቶቼ!
የተከበራችሁ ፡ መኳንንት ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ ልናገር ፤ አንዲት ፡
አጭር ፡ ቃል ፡ እንድናገር ፡ ፍቀዱልኝ! ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ያል
ሰማችሁት ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ እንገልጽላች
ኋለን!» አለ ።

ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ የቀረበው ፡ ሰው ፡ የመከራከሪያ ፡ ንግግ
ሩን ፡ እንዲያቀርብ ፡ ሁልጊዜ ፡ ፈቃደኛ ፡ የሆነው ፡ ቡልባ ፡
«ደግ ፡ ነው ፤ ተውአቸው ፡ ይናገሩ ፡» አለ ።

«የተከበራችሁ ፡ መኳንንት! እንደናንተ ፡ ያሉ ፡ መኳን
ንት ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ታይተው ፡ አያውቁም! እንደናንተ ፡
ያለ ፡ ደግ ፡ መልካምና ፡ ጀግና ፡ ሰው ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ አልተ
ፈጠረም! በዛፖሮዥያን ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ ብለን ፡ ክፉ ፡ እና
ስባለን? በኡክሬይን ፡ ወለድ ፡ አግድ ፡ የሚይዙት ፡ የኛ ፡ ወገ
ኖች ፡ አይደሉም!በፍጹም ፡ አይደሉም! እንዲያውም ፡ አይሁ
ዶች ፡ አይደሉም ፤ ምን ፡ እንደሆኑ ፡ ዲያብሎስ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡
የሚያውቀው ፤ ተወግረው ፡ መጣል ፡ የሚገባቸው ፡ ሰዎች ፡
ናቸው! እዚህ ፡ ያለነው ፡ ማነኛችንም ፡ ይህንኑ ፡ ነው ፡ የም
ንለው ። አደለም ፡ ሽሎማ? እውነት ፡ አደለም ፡ ሽሙል?»

በወገኖቻቸው ፡ መካከል ፡ በፍርሃት ፡ ገርጥተው ፡ የቆ
ሙት ፡ ሽሎማና ፡ ሽሙል ፡ «እግዚአብሔር ፡ ያውቃል ፡ እው
ነት ፡ ነው!» ሲሉ ፡ መለሱ ።

ረጅሙም ፡ አይሁድ ፡ ንግግሩን ፡ ቀጠለና ፡ «እኛ ፡ ከጠ
ላቶቻችሁ ፡ ጋር ፡ ተባብረን ፡ አናውቅም ። ካቶሊኮቹንም ፡
እንደሆን ፡ ልናውቃቸው ፡ እንኳን ፡ አንፈልግም ፤ ጋኔል ፡
እንቅልፍ ፡ ይንሳቸው! እኛና ፡ ዛፖሮዥያኖች ፡ ወንድማማ
ች ፡ ማለት ፡ ነን ።»

«ምን! ወንድማማች ፡ ናቸው ፡ ዛፖሮዥያኖች? ይህ ፡
አይደረግም ፤ አንት ፡ የተረገምክ ፡ አይሁድ ! ድኔፐር ፡ ውስ
ጥ ፡ እንጨምራቸው ፡ ጐበዝ! እነዚህን ፡ እርጉሞች ፡ ሁሉንም ፡



ማስመጥ ፡ ነው!» በማለት ፡ ከኮዛኮቹ ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡
ጮኾ ፡ ተናገረ ።

ወዲያው ፡ እነዚህን ፡ ቃላት ፡ ሲሰሙ ፡ ሁሉም ፡ አይሁ
ዶቹን ፡ እየያዙ ፡ ውኃው ፡ ውስጥ ፡ ይጨምሩአቸው ፡ ጀመር ።
ከየሥፍራው ፡ የሚዘገንን ፡ ጩኸትና ፡ ጫጫታ ፡ ሲሰማ ፡
ኮዛኮቹ ፡ ግን ፡ ውኃው ፡ ውስጥ ፡ የሚፍጨረጨሩትን ፡ አይ
ሁዶች ፡ እያዩ ፡ ይስቁ ፡ ነበር ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ አደጋ ፡ ሊያመ
ጣ ፡ የቻለው ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ንግግር ፡ ያደረገው ፡ አይሁድ ፡
ተይዞ ፡ ከቆመበት ፡ እየጮኸ ፡ ቡልባ ፡ እግር ፡ ላይ ፡ ተጠም
ጥሞ ፡ «ክቡር ፡ ጌታዬ ፤ እጅግ ፡ የተከበሩ ፡ ጌታዬ! ሟቹን ፡
ወንድምን ፡ ዶሮሽን ፡ አውቃቸው ፡ ነበር! ታላቅ ፡ መኳንንት ፡
ነበሩ ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ በቱርኮች ፡ ተማርከው ፡ ሳለ ፡ ገንዘብ ፡
ከፍለው ፡ እንዲወጡ ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ዱካት ፡ ከፍየላቸው ፡
ነበር ፡» አለ ።

«ወንድሜን ፡ ታውቀዋለህ?» አለና ፡ ታራስ ፡ ጠየቀው ።

«አዎ ፡ አውቃቸዋለሁ! በጣም ፡ ቸር ፡ መኳንንት ፡
ነበሩ ።»

«ለመሆኑ ፡ ስምህ ፡ ማን ፡ ይባላል?»

«ያንኬል ።»

«ደግ ፡ ነው ፡» ብሎ ፡ ታራስ ፡ ጥቂት ፡ በነገሩ ፡ ከአሰ
በ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ኮዛኮች ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ «ይህን ፡ አይሁድ ፡
ለመስቀል ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ጊዜ ፡ አናጣም ፤ ለጊዜው ፡ ግን ፡
ከኔ ፡ ጋር ፡ ይሁን ፡» አላቸው ።

ከዚያ ፡ ታራስ ፡ ተከታዮቹ ፡ ኮዛኮች ፡ በሠረገላዎቻቸው ፡
አጠገብ ፡ ከቆሙበት ፡ ሥፍራ ፡ ሔዶ ፡ አይሁዱን ፤ «በል ፡
እዚህ ፡ ሠረገላው ፡ ሥር ፡ ግባና ፡ እንዳትንቀሳቀስ ፤ እናንተም ፡
ጠብቁት ፡» ብሎ ፡ ካዘዘ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አደባባዩ ፡ ሔደ ።

አሁን ፡ ሁናቴው ፡ ስለተለወጠ ፡ ዘመቻው ፡ በባሕር ፡
ላይ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ ፈረሶችና ፡ ሠረገላዎች ፡ እንደሚያስ
ፈልጉ ፡ በመገንዘብ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በውኃው ፡ ዳር ፡ ጀልባ ፡

ማዘጋጀቱን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ አደባባዩ ፡ መሰብሰብ ፡ ጀምሮ
አል ። ወጣቱም ፡ ሽማግሌውም ፡ አንድነት ፡ በሽማግሌዎ
ቹና ፡ በአለቆቹ ፡ ምክር ፡ መሠረት ፡ ተስማምቶ ፡ በቀጥታ ፡
ወደ ፡ ፖላንድ ፡ ለመዝመትና ፡ በኃይማኖታቸው ፡ እንዲሁም ፡
በኮዛክ ፡ ክብር ፡ የደረሰውን ፡ ጉዳት ፡ ለመበቀል ፡ ከተሞቹን ፡
ሁሉ ፡ ለመዝረፍ ፤ ሰብልና ፡ መንደሮችንም ፡ ለማቃጠል ፡
ወስነው ፡ ተነሡ ። በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ የጦር ፡ መሣሪ
ያቸውን ፡ ታጥቀው ፡ ለዘመቻው ፡ ተዘጋጁ ። ኮሼቮዩ ፡ እንደ ፡
ቀድሞው ፡ የአንድ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ሕዝብ ፡ ጉዳይ ፡ ፈጻሚ ፡
ሽቁጥቁጥና ፡ ዓይነ ፡ አፋር ፡ ሰው ፡ መምሰሉ ፡ ቀርቶ ፡ አሁን ፡
ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ መሪአቸው ፡ ሆነ ። ትእዛዝ ፡ በሚሰ
ጥበትም ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ እንደልብ ፡ አዳሪዎችና ፡ ጨዋታ ፡
ወዳድ ፡ ሰዎች ፡ ቀና ፡ ብለው ፡ ሊመለከቱት ፡ እንኳን ፡ ባለ
መድፈር ፡ በአክብሮት ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ያዳምጡ ፡
ነበር ። ኮሼቮዩ ፡ በብዙ ፡ የጦር ፡ ሜዳዎች ፡ መሪ ፡ ሆኖ ፡ የተ
ፈተነ ፡ የበሰለ ፡ ኮዛክ ፡ ስለነበር ፡ ትእዛዙን ፡ ሲያስተላልፍ ፡
ያለመርበትበት ፡ በእርጋታ ፡ ነበር ።

«ድርጅታችሁን ፡ ሁሉ ፡ በጥንቃቄ ፡ እንድትመረምሩ ፡
ያስፈልጋል ። ሰረገላዎቻችሁንና ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎቻች
ሁን ፡ ሁሉ ፡ በጥንቃቄ ፡ መርምራችሁ ፡ ዝግጁ ፡ መሆናቸ
ውን ፡ አረጋግጡ ። ብዙ ፡ ልብስ ፡ እንዳትሸከሙ ፤ አንዳን
ድ ፡ ሸሚዝና ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ ሱሪ ፡ ብቻ ፡ ያዙ ። ለምግ
ብም ፡ አንድ ፡ ቶፋ ፡ የገንፎ ፡ ዱቄትና ፡ አንድ ፡ ቶፋ ፡ የተፈ
ጨ ፡ በቆሎ ፡ ይበቃል ። ማንም ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እን
ዳይሸከም ። አስፈላጊው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በሠረገላው ፡ ውስጥ ፡
ይገኛል ። እያንዳንዱ ፡ ኮዛክ ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ ፈረስ ፡ መጫን ፡
አለበት ፤ ደግሞ ፡ ወንዞችን ፡ ለመሻገርና ፡ ለሌላም ፡ ክፉ ፡ ሥ
ፍራዎች ፡ የሚሆኑን ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ጥንድ ፡ ያህል ፡ ሠረ
ገላ ፡ ጐታች ፡ በሬዎች ፡ ያስፈልጉናል ። ደግሞ ፡ ከሁሉ ፡ በላይ ፡
አጥብቄ ፡ የምጠይቃችሁ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ እንድትጠብቁ ፡



ነው ። በዘረፋ ፡ ሲቀናቸው ፡ ዋጋ ፡ ያለውን ፡ ከፈይና ፡ የከበሩ ፡
ጨርቃ ፡ ጨርቅ ፡ ለእግራቸው ፡ መጠቅለያ ፡ የሚቀዳድዱ ፡
ከመሃላችሁ ፡ አንዳንድ ፡ ጐልማሶች ፡ እንዳሉ ፡ አውቃለሁ ።
እንዲህ ፡ ያለውን ፡ የሰይጣን ፡ ልማድ ፡ ተውት ። እንድያውም ፡
ጨርቃ ፡ ጨርቁን ፡ ችላ ፡ ብላችሁ ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ የጦር ፡ መሣ
ሪያ ፡ ብርና ፡ ይህንን ፡ የመሳሰለው ፡ ሃብት ፡ ጠቃሚ ፡ ስለሆነ ፡
እሱን ፡ ብቻ ፡ ፈልጉ ፤ ደግሞ ፡ በዘመቻ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡
ሰክሮ ፡ ቢታይ ፡ ክፉ ፡ ቅጣት ፡ እንደሚደርስበት ፡ አስቀድሜ ፡
እነግራችኋለሁ ። በጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ አለ ፡ የሚባል ፡ ታላቅ ፡
ጀግናም ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ ከአንዱ ፡ ሠረገላ ፡ ጋር ፡ አንገቱን ፡
እንደውሻ ፡ አሳስሬ ፡ በጥይት ፡ ተመቶ ፡ እዚያው ፡ የውሻ ፡
ሞት ፡ ይሞታል ። ሬሣውም ፡ እንኳን ፡ ሳይቀበር ፡ ለአሞሮ
ች ፡ ይጣላል ። በዘመቻ ፡ ላይ ፡ የሚሰክር ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ቀ
ብር ፡ አይገባውም ። እናንተ ፡ ጐልማሶች ፡ በማናቸውም ፡
ረገድ ፡ ጠና ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ ትእዛዝ ፡ መቀበል ፡ አለባ
ችሁ ። ሰውነታችሁን ፡ አንዱ ፡ ላይ ፡ ጥይት ፡ ቢጨርፋችሁ ፡
ወይም ፡ የጐራዴ ፡ ስለት ፡ ቢጭራችሁ ፡ ከምንም ፡ አትቁ
ጠሩት ፤ ትንሽ ፡ ባሩድ ፡ በአንድ ፡ መለኪያ ፡ ቮድካ ፡ በጥብ
ጣችሁ ፡ ጅው ፡ አድርጋችሁ ፡ ስትጠጡት ፡ ደህና ፡ ትሆና
ላችሁ ። ትኩሳትም ፡ ሆነ ፡ ሌላ ፡ ሕመም ፡ አይሰማችሁም ።
ቁስሉም ፡ በጣም ፡ ትልቅ ፡ ካልሆነ ፡ ትንሽ ፡ አፈር ፡ በምራ
ቃችሁ ፡ ለውሳችሁ ፡ ስትደመድሙበት ፡ ይደርቃል ። በሉ ፡
እንግዲህ ፡ ጐበዝ ፤ ወደየሥራችሁ ፡ ከሚያስፈልገው ፡ በላይ ፡
አትጣደፉ ፤ ሁሉንም ፡ ነገር ፡ በጥንቃቄ ፡ መሥራት ፡ ነው!»

ኮሼቮዩ ፡ ይህን ፡ ተናግሮ ፡ ከመጨረሱ ፡ ኮዛኮቹ ፡ ሁሉ ፡
በፍጥነት ፡ ወደየሥራቸው ፡ ተሰማሩ ። በሠፈሩ ፡ ውስጥ ፡
መጠጥ ፡ የሚሉት ፡ ነገር ፡ ታይቶ ፡ እንደማያውቅ ፡ ሁሉ ፡
አንድም ፡ ሰካራም ፡ አይታይም ።

አንዳንዶቹ ፡ የሠረገላቸውን ፡ መሽከርከሪያ ፡ ሲያጠብ
ቁና ፡ ሲለውጡ ፤ አንዳንዶች ፡ ደግሞ ፡ ጓዝ ፡ የጦር ፡ መሣ

ሪያቸውን ፡ ሲጭኑ ፡ የቀሩት ፡ ፈረሶችና ፡ በሮች ፡ ለጭነት ፡ እየነዱ ፡ አመጡ ። የፈረሶች ፡ ኮቴ ፤ የሚፈተኑ ፡ ጠመንጃዎች ፡ ጩኸት ፤ የሚሳሉ ፡ ጐራዴዎች ፡ ኳኳታ ፤ በሬዎች ፡ ሲያገሱና ፡ ሠረገላዎቹም ፡ ሲንቀሳቀሱ ፡ ከየሥፍራው ፡ ይሰማ ፡ ጀመር ። ወዲያው ፡ የኮዛኮቹ ፡ የጦር ፡ ድርጅት ፡ በሜዳው ፡ ላይ ፡ አተርትሮ ፡ ተዘረጋ ። የዚህንም ፡ ሠራዊት ፡ ሰልፍ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከጫፍ ፡ እጫፍ ፡ ሮጦ ፡ ለመድረስ ፡ ቢሞክር ፡ በጣም ፡ አድካሚ ፡ መንገድ ፡ እንደሚሆንበት ፡ አይጠረጠርም ።

ከእንጨት ፡ በተሠራው ፡ በትንሹ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቄሱ ፡ የመሰናበቻ ፡ ጸሎት ፡ አድርሰው ፡ ሠራዊቱን ፡ ሁሉ ፡ ጠበል ፡ ረጩ ። እያንዳንዱም ፡ ኮዛክ ፡ መስቀል ፡ እየተሣለመ ፡ አለፈ ። ጦሩ ፡ ከሠፈሩ ፡ ወጥቶ ፡ ሲሔድ ፡ ዘማቾቹ ፡ ሁሉ ፡ ዘወር ፡ ብለው ፡ ተመለከቱና ፡ «ደህና ፡ ሁኚ ፡ እናታችን! እግዚአብሔር ፡ ከክፉ ፡ ይጠብቅሽ?» ብለው ፡ ጉዞአቸውን ፡ ቀጠሉ ።

ታራስ ፡ ቡልባ ፡ ከጦሩ ፡ ሠፈር ፡ ውጭ ፡ ባለው ፡ መንደር ፡ ሲያልፍ ፡ እሱ ፡ ያዳነው ፡ አይሁድ ፡ ያንኬል ፡ በአንድ ፡ እፍታ ፡ መደብር ፡ አቁሞ ፡ ለዘማች ፡ ወታደር ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ ሸቀጣ ፡ ሸቀጥ ፡ ዳቦ ፡ እንኳን ፡ ሳይቀር ፡ ሲሸጥ ፡ ተመለከተው ። ታራስም ፡ «አይሁዶች ፡ ምን ፡ ያሉ ፡ ሰይጣኖች ፡ ናቸው!» ብሎ ፡ እየተገረመ ፡ ፈረሱን ፡ ወደሱ ፡ ኮልኩሎ ፤ «አንተ ፡ ሞኝ ፡ እዚህ ፡ ተጐልተህ ፡ ምን ፡ ታደርጋለህ? በጥይት ፡ መመታት ፡ አምሮሃል?» አለው ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ያንኬል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምሥጢር ፡ እንደሚናገር ፡ ሰው ፡ ሺክክ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ቡልባ ፡ ተጠጋና ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤

«ጌታዬ ፡ ብቻ ፡ ለማንም ፡ እንዳይናገሩ ፡ እንጂ ፡ አሁን ፡ የኔም ፡ ሠረገላ ፡ ከኮዛኮች ፡ ሠረገላ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ነው ፡ ያለው ፤ ስለዚህ ፡ በጉዞ ፡ ላይ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ነገር ፡



ሁሉ ፡ ማናቸው ፡ አይሁድ ፡ ከሚጠይቀው ፡ ባነሰ ፡ ዋጋ ፡ እሸጣለሁ!»

ታራስ ፡ ቡልባ ፡ በአይሁዶች ፡ የነጋዴነት ፡ መንፈስ ፡ እየተገረመ ፡ ወደ ፡ ሠልፉ ፡ ተመለሰ ።

## ምዕራፍ ፡ አምስት ።

ወዲያው ፡ ደቡብ ፡ ምእራብ ፡ ፖላንድ ፡ በፍርሃት ፡ ይሸበር ፡ ጀመር ። «ዛፖሮዥያኖች! ዛፖሮዥያኖች ፡ ሊመጡ ፡ ነው!» የሚል ፡ ወሬ ፡ በየሥፍራጡ ፡ ተነዛ ። ሸሽተው ፡ ለማምለጥ ፡ የቻሉ ፡ ሁሉ ፡ ተሰደዱ ፤ ነገ ፡ ታታሮች ፡ ለሚያፈራርሱት ፡ ምን ፡ አለፋን ፡ በማለት ፡ ምሽግ ፡ ወይም ፡ የረባ ፡ ሕንጻ ፡ ሳይሠራ ፡ የማር ፡ ጐጆ ፡ ብቻ ፡ በሚታይበት ፡ በዚያ ፡ የግድ ፡ የለሽ ፡ ዘመን ፡ እንደተለመደው ፡ ሁሉ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቀላል ፡ ንብረቱን ፡ እየፈታ ፡ በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በሌለው ፡ ስደት ፡ ተበታተነ ፤ አንዱ ፡ ማረሻና ፡ በሬውን ፡ በፈረስና ፡ በጠመንጃ ፡ ለውጦ ፡ በቀበሌው ፡ ወደሚገኘው ፡ የጦር ፡ ኃይል ፡ ሲገባ ፡ አንዱ ፡ ደግሞ ፡ የሚችለውን ፡ ንብረቱን ፡ ተሸክሞ ፡ ከብቶቹን ፡ እየነዳ ፡ ሸሽቶ ፡ ይደበቃል ። ጥቂቶች ፡ ሰዎች ፡ የጦር ፡ መሣሪያቸውን ፡ ይዘው ፡ ወራሪዎቹን ፡ ለመቋቋም ፡ ከተሰለፉ ፡ በኋላ ፡ ኮዛኮቹን ፡ ግን ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በሽሽት ፡ ይበታተኑ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ዛፖሮዥያኖች ፡ በመባል ፡ የሚጠራው ፡ ጦር ፡ ወዳድና ፡ ኃይለኛ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ላዩን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትና ፡ ድርጅት ፡ ያነሰው ፡ መስሎ ፡ ቢታይም ፡ ውስጡን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የጦር ፡ ስልት ፡ ድርጅት ፡ እንዳለው ፡ ማንም ፡ ያውቅ ፡ ነበር ። በፈረስ ፡ ላይ ፡ የተቀመጡት ፡ ኮዛኮች ፡ ፈረሶቻቸውን ፡ ጭነት ፡ እንዳይከብዳቸውና ፡ እንዳይሞቃቸው ፡ በጣም ፡ ይጠነቀቃሉ ። ከሠረገላዎች ፡ ኋላ ፡ ኋላ ፡ የሚሔዱት ፡ እግረኞችም ፡ ጉዞአቸው ፡ የረጋ ፡ ነው ። መላው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ቀኑን ፡ በየጫካ

ውና ፣ ጭር ፣ ባለው ፣ መስክ ፣ እያሳለፈ ፣ ሌሊት ፣ ብቻ ፣ ነው ፣ የሚጓዘው ። የጠላትን ፣ ሁናቴ ፣ የሚያጣሩ ፣ ሰላዮች ፣ ሁልጊዜ ፣ ከጦሩ ፣ ፊት ፣ ፊት ፣ ይላካሉ ። በዚህ ፣ ረገድ ፣ ኮዛኮቹ ፣ ብዙውን ፣ ጊዜ ፣ ካልታሰበው ፣ ሥፍራ ፣ ድንገት ፣ ከተፍ ፣ እያሉ ፣ የረገጡትን ፣ ቀበሌ ፣ ሁሉ ፣ በሞት ፣ ጥላ ፣ ሸፍነውት ፣ ያልፉ ፣ ነበር ። መንደሮችን ፣ ያቃጥላሉ ፤ የቀንድ ፣ ከብቶችና ፣ ፈረሶች ፣ ተዘርፈው ፣ የጦር ፣ ሠራዊቱ ፣ ይነዳቸዋል ፣ ወይም ፣ እዛው ፣ ይታረዳሉ ። ዘመቻቸው ፣ ከእውነተኛ ፣ ዘመቻ ፣ ይልቅ ፣ የደም ፣ ድግስ ፣ ነበር ፣ መስሎ ፣ የሚታየው ። በዚያ ፣ የአረመኔ ፣ ዘመን ፣ ዛፖሮዥያኖች ፣ የረገጡትን ፣ ምድር ፣ መመልከት ፣ በጣም ፣ የሚዘገንን ፣ ነገር ፣ ነበር ። የተገደሉ ፣ ሕፃናት ፤ ጡታቸው ፣ የተቆረጠ ፣ ሴቶች ፤ የባታቸው ፣ ቆዳ ፣ የተገፈፈና ፣ የተለቀቁ ፣ ምርኮኞች ፣ ይታዩ ፣ ነበር ። በዚህ ፣ ሁናቴ ፣ ኮዛኮች ፣ ቂማቸውን ፣ ይወጡ ፣ ጀመር ።

የኮዛኮቹን ፣ መምጣት ፣ የሰሙ ፣ የአንድ ፣ ገዳም ፣ አለቃ ፣ በመንግሥትና ፣ በእነሱ ፣ መካከል ፣ ጠብ ፣ አለመኖሩንና ፣ ይህ ፣ አሁን ፣ የሚፈጽሙትም ፣ የወረራ ፣ ተግባር ፣ ሕገ ፣ ወጥ ፣ መሆኑን ፣ በመግለጽ ፣ መልዕክት ፣ የሚያደርሱ ፣ ሁለት ፣ መነኮሳት ፣ ላኩ ።

ለመልዕክቱም ፣ መልስ ፣ የኮዛኮች ፣ ኮሼቮይ ፤ «የገዳሙን ፣ አለቃ ፣ ምንም ፣ አይስጉ ፣ በሉዋቸው ፤ ኮዛኮች ፣ ለትንባሆአቸው ፣ የሚሆን ፣ እሳት ፣ ከማንደድ ፣ በቀር ፣ ሌላ ፣ ምንም ፣ አይሠሩም ፣» በማለት ፣ መልስ ፣ ላከላቸው ።

ወዲያው ፣ ብዙ ፣ ሳይቆይ ፣ ያ ፣ የሚያምር ፣ ትልቅ ፣ ገዳም ፣ በእሣት ፣ ተያይዞ ፣ እንደጧፍ ፣ ይንቀለቀል ፣ ጀመር ።

በቀበሌው ፣ የተመደቡት ፣ የጦር ፣ ወታደሮች ፣ ያድኑናል ፣ ተብሎ ፣ ተስፋ ፣ በሚጣልባቸው ፣ ከተሞች ፣ መነኮሣት ፤ አይሁዶችና ፣ ሴቶች ፣ ከአንዱ ፣ ሥፍራ ፣ ተሰደው ፣ እየጐረፉ ፣ ሲገቡ ፣ ሥፍራ ፣ አልበቃቸው ፣ አለ ። አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ ጥቂት ፣ ወታደሮች ፣ ከመንግሥት ፣ ተልከው ፣ ይመጡና ፣ እነሱም ፣ ወይ ፣ ኮዛኮቹን ፣ ማግኘት ፣ ያቅታቸዋል ፣ ወይም ፣ ደግሞ ፣ ተገናኝተው ፣ ገና ፣ ውጊያው ፣ ከመጀመሩ ፣ ወደኋላ ፣ ተመልሰው ፣ በፈጣን ፣ ፈረሶቻቸው ፣ ይፈረጥጣሉ ። በአለፉ ፣ የጦር ፣ ሜዳዎች ፣ ሰፊ ፣ ዝና ፣ ካገኙ ፣ የንጉሡ ፣ የጦር ፣ መኳንኖች ፣ መካከል ፣ ኮዛኮቹን ፣ ጠንክረው ፣ እስከ ፣ መጨረሻው ፣ ለመቋቋም ፣ ያሰቡ ፣ አንዳንድ ፣ ቆራጥ ፣ ጀግኖች ፣ ነበሩ ።

እንዲህ ፣ ባለው ፣ ጊዜ ፣ ወጣቶቹ ፣ ኮዛኮች ፣ ዘረፋውንና ፣ ሌላውን ፣ ነገር ፣ ችላ ፣ በማለት ፣ ችሎታቸውን ፣ ለታላላቆቻቸው ፣ ለማሳየት ፣ ብቻ ፣ ሲሉ ፣ በአማረው ፣ ሰንጋው ፣ ላይ ፣ ተቀምጦ ፣ የካባው ፣ ዘርፍ ፣ በነፋስ ፣ ከሚውለበለበው ፣ ኩሩና ፣ ጅንን ፣ የፖሊሽ ፣ ወታደር ፣ ጋር ፣ እጅ ፣ ለእጅ ፣ ይገጥሙ ፣ ነበር ። የጦርነትን ፣ ጥበብ ፣ መማር ፣ ለወጣቶቹ ፣ ኮዛኮች ፣ እንደ ፣ ጨዋታ ፣ ነው ። ገና ፣ ከአሁኑ ፣ ብዙ ፣ የፈረስ ፣ እቃዎች ፣ ዋጋ ፣ ያላቸው ፣ ጐራዴዎችና ፣ ጠመንጃዎች ፣ ማርከዋል ። በአንድ ፣ ወር ፣ ጊዜ ፣ ውስጥ ፣ እነዚህ ፣ ወጣቶች ፣ በስለው ፣ ሙሉ ፣ ሰው ፣ ሆኑ ። የህጻንነት ፣ ልስላሴ ፣ ይታይበት ፣ የነበረው ፣ ፊታቸው ፣ አሁን ፣ የጠነከረና ፣ ኮስታራ ፣ ሆነ ። ሽማግሌው ፣ ታራስ ፣ ሁለቱ ፣ ልጆቹ ፣ ከዋና ፣ ዋናዎቹ ፣ ጀግኖች ፣ ኮዛኮች ፣ መካከል ፣ ከፍተኛ ፣ ደረጃ ፣ ስለያዙለት ፣ እጅግ ፣ ደስ ፣ አለው ። አስታጥ ፣ ለጦር ፣ ሜዳ ፣ በተለይ ፣ የተፈጠረ ፣ ይመስል ፣ ነበር ። ገና ፣ በሃያ ፣ ሁለት ፣ ዓመቱ ፣ የአሳየው ፣ እርጋታና ፣ የጦር ፣ ሞያ ፣ ወደፊት ፣ መሪ ፣ እንደሚሆን ፣ ምልክት ፣ ሆኖ ፣ ይታይ ፣ ጀመር ።

«ገና ፣ ወደፊት ፣ ጥሩ ፣ ኮሎኔል ፣ ይወጣዋል ፤ ወደፊት ፣ ከገዛ ፣ ባትኩው ፣ እንኳን ፣ የበለጠ ፣ ነው ፣ የሚሆነው ፣» እያለ ፣ ታራስ ፣ በደስታ ፣ ይናገር ፣ ነበር ።

አንድሬይን ፣ ደግሞ ፣ ስለት ፣ ለስለት ፣ ሲጋጭና ፣ የጥይትም ፣ ጩኸት ፣ እንደ ፣ ሙዚቃ ፣ ሆኖ ፣ ይማርከው ፣ ነበር ።

የራሱንም ፡ ሆነ ፡ የጠላቱን ፡ ኃይል ፡ አስቀድሞ ፡ ማመዛዘን ፡ በፍጹም ፡ አይችልም ። በጦርነት ፡ ደስታ ፡ ከመዋጡ ፡ የተነሳ ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ እውር ፡ ይሆናል ። አእምሮው ፡ እሳት ፡ እንደሚነድበት ፡ ሲሆንና ፡ የሚመለከተው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በዓይኖቹ ፡ ላይ ፡ ሲዞር ፡ የሰው ፡ ጭንቅላት ፡ ተቆርጦ ፡ ሲሽከረከር ፡ ፈረሶች ፡ ሲወድቁ ፡ እርሳስ ፡ በጆሮው ፡ እያፏጨ ፡ ጐራዴ ፡ ከፊቱ ፡ እያብለጨለጨ ፡ በጦሩ ፡ መሃል ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ እየሰነዘረ ፡ ሲያልፍ ፡ ከመደሰት ፡ በቀር ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ የሚሰነዘሩትን ፡ መሣሪያዎች ፡ ሁሉ ፡ ከምንም ፡ አይቆጥራቸውም ። አንድሬይ ፡ ውጊያ ፡ ከመውደዱ ፡ የተነሣ ፡ ማናቸውም ፡ የረጋና ፡ አስተዋይ ፡ ሰው ፡ ከማይሞክረው ፡ አደገኛ ፡ ስፍራ ፡ እየገባ ፡ ብዙ ፡ ጀብዱ ፡ ሲፈጽም ፡ አባቱ ፡ እያየው ፡ ይደነቅ ፡ ነበር ። ሽማግሌው ፡ ታራስ ፡ ልጁን ፡ በአድናቆት ፡ ከተመለከተው ፡ በኋላ ፡ «እግዚአብሔር ፡ ይጠብቀው ፡ እንጂ ፡ ጥሩ ፡ ወታደር ፡ ይወጣዋል! ከኦስታፕ ፡ እኩል ፡ አይሆንም ፡ ግን ፡ ጥሩ ፡ ወታደር ፡ የሚሆን ፡ ነው!» ይል ፡ ነበር።

ብዙ ፡ ከበርቴ ፡ ሰዎችና ፡ ብዙ ፡ ሃብት ፡ ይገኝበታል ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ስለተሰማ ፡ የኮዛኮች ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ዱብኖ ፡ ከተማ ፡ ለመጓዝ ፡ አሰበ ። አንድ ፡ ቀን ፡ ተኩል ፡ ከተጓዙ ፡ በኋላ ፡ ከከተማው ፡ ደረሱ ። የከተማው ፡ ኑዋሪዎች ፡ ጠላታቸው ፡ እቤታቸው ፡ እስኪገባ ፡ ከመመልከት ፡ ይልቅ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ተከላክለው ፡ በከተማቸው ፡ አደባባይና ፡ በየመንገዱ ፡ ለመሞት ፡ ቆርጠው ፡ ነበር ። የከተማው ፡ ዙሪያ ፡ በከፍተኛ ፡ የአፈር ፡ ዙሪያ ፡ ተመሽጎ ፡ አል ። በምሽጉ ፡ ውስጥ ፡ ያለውም ፡ የጦር ፡ ኃይል ፡ የአለበትን ፡ ግዴታ ፡ የተገነዘበ ፡ ጠንካራ ፡ ድርጅት ፡ ነበር ። ኮዛኮቹ ፡ ምሽጉን ፡ ጥሶ ፡ ለመግባት ፡ ቢሞክሩ ፡ ከባድ ፡ ተኩስ ፡ ወረደባቸው ። የከተማው ፡ ኑዋሪዎች ፡ በምሽጉ ፡ ጀርባ ፡ ተሰብስበው ፡ ከተማቸውን ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ለመጠበቅ ፡ መቁረጣቸው ፡ በፊታቸው ፡ ላይ ፡ ይነበብ ፡ ነበር ። ሴ



ቶቹ ፡ እንኳን ፡ ሳይቀሩ ፡ በዚህ ፡ የተከላካይነት ፡ ውጊያ ፡ ተካፋይ ፡ በመሆን ፡ ድንጊያ ፤ በርሚል ፤ ያገኙትን ፡ እቃ ፡ ሁሉ ፡ እያነሱ ፡ ከመወርወራቸውም ፡ በላይ ፡ በዓይናቸው ፡ እየገባ ፡ ማየት ፡ እንዲከለክላቸው ፡ አሸዋ ፡ እያፈሱ ፡ በኮዛኮቹ ፡ ላይ ፡ ይበትኑ ፡ ጀመር ። ኮዛኮቹ ፡ መሽጐ ፡ ከተቀመጠ ፡ ጠላት ፡ ጋር ፡ መዋጋት ፡ አይወዱም ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ ኮሼቮይ ፡ ጦሩ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንዲመለስ ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፤ «ግድ ፡ የላችሁም ፡ ወንድሞቼ ፡ ለጊዜው ፡ እናፈግፍግ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አንዳቸውም ፡ እንኳን ፡ ከዚች ፡ ከተማ ፡ የወጡ ፡ እንደሆነ ፡ ክርስቲያንነቴ ፡ ቀርቶ ፡ የተረገመ ፡ ታታር ፡ በላችሁ ፡ ጥሩኝ ። ዝም ፡ በሏቸው ፡ እነዚህ ፡ ውሾች ፡ እዛው ፡ በርሃብ ፡ ይለቁ!» አለ ።

የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ከተማውን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መለስ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ሥራ ፡ እንዳይፈታ ፡ ያህል ፡ ያካባቢውን ፡ መንደሮች ፡ እህሉንም ፡ ማቃጠል ፡ ጀመረ ። በአንዳንድ ፡ ስፍራም ፡ ባልታጨደው ፡ ሰብል ፡ መሃል ፡ የኮዛኮች ፡ ፈረሶች ፡ እንዲመገቡ ፡ ተለቀቁ ። የከተማው ፡ ህዝብ ፡ ምግቡን ፡ የሚያገኘው ፡ ከገጠሩ ፡ እርሻ ፡ ስለነበር ፡ ሰብሉ ፡ ሲበላሽ ፡ በመመልከቱ ፡ ጭንቅ ፡ ያዘው ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ኮዛኮቹ ፡ ሰረገላዎቻቸውን ፡ በሁለት ፡ ረድፍ ፡ ደርድረው ፡ የከተማውን ፡ ዙሪያ ፡ ከከበቡ ፡ በኋላ ፡ በመንደር ፡ ተመድበው ፡ የምርኮ ፡ እቃ ፡ እየተለዋወጡ ፡ በእርጋታ ፡ እየተጫዋወቱ ፡ ተቀመጡ ። በየአንዳንዱ ፡ መንደር ፡ ድንገት ፡ አደጋ ፡ ቢመጣ ፡ የሚያሳይ ፡ ትልቅ ፡ ደመራ ፡ እየነደደ ፡ በእሳቱ ፡ አጠገብም ፡ ንቁ ፡ ዘበኛ ፡ ቆሞ ፡ ሲጠብቅ ፡ ያድራል ።

ነገር ፡ ግን ፡ ኮዛኮቹ ፡ ያለውጊያ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ መቀመጥ ፡ እየሰለቻቸው ፡ ሔደ ። ይህንንም ፡ በመመልከት ፡ ኮሼቮዩ ፡ ደስ ፡ እንዲላቸው ፡ በማለት ፡ የተመደበላቸው ፡ የመጠጥ ፡ ልክ ፡ እጥፍ ፡ እንዲሆንላቸው ፡ አድርጐ ፡ ነበር ፤ ሆኖም ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ኑሮ ፡ ለኮዛኮቹ ፡ አልጣማቸውም ። በተለ

ይም ፡ ለታራስ ፡ ቡልባ ፡ ልጆች ። አንድሬይማ ፡ መሰልቸቱ ፡ በግልጽ ፡ ይታይበት ፡ ነበር ።

ይህንኑ ፡ በመመልከት ፡ ታራስ ፡ ታናሹን ፡ ልጁን ፡ ጠርቶ ፡ «አንተ ፡ እሳት ፡ ጐረምሳ! ገና ፡ መሪ ፡ የምትሆን ፡ ነህና ፡ ሁሉንም ፡ መቻል ፡ አለብህ ። ጥሩ ፡ ጀግና ፡ የሚባለው ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ልበ ፡ ሙሉ ፡ የሚሆነው ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ እርጋታንም ፡ የሚችል ፡ ጭምር ፡ ነው ፡» ሲል ፡ መከረው ።

ነገር ፡ ግን ፡ እሳት ፡ የሆነው ፡ የልጅነት ፡ ዘመንና ፡ የእርጅና ፡ እድሜ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ አይግባቡም ፤ ጠባያቸው ፡ የተለያየ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሳ ፡ አንዱን ፡ ነገር ፡ የተለያየ ፡ መልክ ፡ ያለው ፡ አድርገው ፡ ነው ፡ የሚመለከቱት ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ የቡልባ ፡ ክፍለ ፡ ጦር ፡ በቶቨካች ፡ መሪነት ፡ ዋናው ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ ካለበት ፡ ሥፍራ ፡ ደረሰ ። ከሱም ፡ ጋር ፡ ሁለት ፡ ኤሳውሎችና ፡ ሌሎችም ፡ የጦር ፡ መኮንኖች ፡ አብረው ፡ ነበሩ ። በጠቅላላው ፡ አዲስ ፡ የመጡት ፡ የቡልባ ፡ ክፍለ ፡ ጦር ፡ ኮዛኮች ፡ አራት ፡ ሺ ፡ ይሆናሉ ። ከአዲሱ ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ የመጡት ፡ ሹማምንት ፡ ለሁለቱም ፡ ለቡልባ ፡ ልጆች ፡ ለየአንዳንዳቸው ፡ ከእናታቸው ፡ የተላከ ፡ ከሲፕረስ ፡ እንጨት ፡ የተሠራ ፡ የቅዱሳን ፡ ምስል ፡ አመጡላቸው ። ሁለቱ ፡ ወንድማማቾች ፡ የተቀደሱትን ፡ ምስሎች ፡ በየአንገታቸው ፡ ካሰሩ ፡ በኋላ ፡ የአሮጊት ፡ እናታቸው ፡ ሃሳብ ፡ በአእምሮአቸው ፡ እየመጣ ፡ ያስጨንቃቸው ፡ ጀመር ። የላከችው ፡ ስጦታ ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው? ምን ፡ ሚርት ፡ የያዘ ፡ ይሆን? ጠላታቸውን ፡ ድል ፡ እንዲያደርጉና ፡ ሃብት ፡ ሰብስበው ፡ በደስታ ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ እንዲመለሱ ፡ ምርቃት ፡ ይሆን? ወይስ...? ነገር ፡ ግን ፡ የወደፊቱን ፡ ነገር ፡ የሚያውቅ ፡ የለም ፤ የአንድ ፡ ሰው ፡ የወደፊት ፡ እጣ ፡ በጨፌ ፡ ላይ ፡ እንዳረፈ ፡ የበልግ ፡ ወቅት ፡ ጉም ፡ ያለ ፡ ነው ። በጭጋጉ ፡ ውስጥ ፡ አዕዋፍ ፡ እርስ ፡ በእርስ ፡ ሳይተያዩ ፡ ይበራሉ ፤



ጨልሌው ፡ እርግብዋን ፤ እርግብዋም ፡ ጨልሌውን ፡ ለማየት ፡ ባለመቻል ፡ ምን ፡ ያህል ፡ በሞት ፡ አጠገብ ፡ እንዳሉ ፡ እንዳቸውም ፡ ሳያውቁት ፡ ይተላለፋሉ ።

አስታፕ ፡ ወዲያው ፡ ወደተመደበበት ፡ ተግባር ፡ ተመለሰ ፤ አንድሬይ ፡ ግን ፡ ምክንያቱን ፡ ሳያውቀው ፡ አንድ ፡ ቅር ፡ የሚል ፡ ነገር ፡ ልቡን ፡ አስጨንቀው ። ኮዛኮቹ ፡ እራታቸውን ፡ በልተዋል ፤ ጊዜውም ፡ ከመሸ ፡ ቆይቶአል ። የአማረው ፡ የሃምሌ ፡ ሌሊት ፡ አስደሳች ፡ መልክ ፡ ይዞ ፡ ይታያል ። አንድሬይ ፡ እንዲህ ፡ ባለው ፡ አስደሳች ፡ ሌሊት ፡ ተማርኮ ፡ ወደ ፡ ጐጆው ፡ ለመግባት ፡ ወይም ፡ እንቅልፍ ፡ ለመተኛት ፡ አልቻለም ። ስፍር ፡ ቁጥር ፡ የሌላቸው ፡ ከዋክብት ፡ በሰማዩ ፡ ላይ ፡ ቁልጭ ፡ ብለው ፡ ያንጸባርቃሉ ። ከጠላት ፡ የተዘረፈ ፡ ብዙ ፡ እቃ ፡ የተጫኑ ፡ ሠረገላዎች ፤ በየሜዳው ፡ ይታያሉ ። በሰረገላዎችም ፡ ዙሪያ ፡ ዛፖሮዥያውያን ፡ ተጋድመዋል ። ከረጢት ፡ ባርኔጣ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ አጠገባቸው ፡ ያለውን ፡ ጓደኛቸውን ፡ ተንተርሰው ፡ የተኙት ፡ ኮዛኮች ፡ አስደናቂ ፡ ትርእይት ፡ ሆነው ፡ የሚታዩ ፡ ነበሩ ። አንድ ፡ ኮዛክ ፡ ሲተኛም ፡ ቀን ፡ የታጠቀው ፡ የዘመቻው ፡ መሣሪያ ፡ ሁሉ ፡ አይለየውም ። ሠረገላ ፡ ጐታች ፡ በሬዎች ፡ በሜዳው ፡ ላይ ፡ ተኝተው ፡ ትልልቅ ፡ ጉብታ ፡ ይመስላሉ ። በየስፍራው ፡ የተኙት ፡ ሰዎች ፡ ኩርፊያ ፡ እያየለ ፡ ሔደ ። ከወደ ፡ መስኩም ፡ በችካል ፡ ታስረው ፡ የቆሙት ፡ ፈረሶች ፡ መታሰራቸውን ፡ በመቃወም ፡ ሲያሽካኩ ፡ ይሰማሉ ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ የተዋበው ፡ የሃምሌ ፡ ሌሊት ፡ ከምን ፡ ጊዜውም ፡ የበለጠ ፡ ውበት ፡ ተጐናጽፎ ፡ ነበር ። ተጨማሪ ፡ ውበት ፡ የሰጡትም ፡ ገና ፡ አመድ ፡ ሆነው ፡ ያልጠፉት ፡ አሁንም ፡ የሚነዱት ፡ ያካባቢው ፡ መንደሮች ፡ ናቸው ። በአንዱ ፡ ስፍራ ፡ የእሳቱ ፡ ነበልባል ፡ በዝግታና ፡ በታላቅ ፡ ግርማ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ የሚጓዝ ፡ ይመስላል ። በሌላው ፡ ደግሞ ፡ ነበልባሉ ፡ የሚነድ ፡ ነገር ፡ እያጋጠመው ፡ አውሎ ፡ ነፋስ ፡ እንደ

ሚያነሳው ፡ አፈር ፡ ብትን ፡ ብሎ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አንጻር ፡ ይወረወራል ። ነዶ ፡ የከሰለው ፡ የገዳሙ ፡ ህንጻ ፡ ጥቁር ፡ ሆኖ ፡ ቆሞ ፡ በአካባቢው ፡ ነበልባሉ ፡ በደነፋ ፡ ቁጥር ፡ ወገግ ፡ ብሎ ፡ ይታያል ። በዚህ ፡ ሁሉ ፡ መሃል ፡ አንድ ፡ ያልታደለ ፡ አይሁድ ፡ ወይም ፡ መነኩሴ ፡ ከህንጻው ፡ ግድግዳ ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡ ዛፍ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ተንጠልጥሎ ፡ እሳቱ ፡ ሲለበልበው ፡ ይታያል ። በሰማዩ ፡ ላይ ፡ ርቀው ፡ የሚበሩ ፡ አዕዋፍ ፡ በአንድ ፡ የነበልባል ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ጥቋቁር ፡ መስቀሎች ፡ ይመስላሉ ። የተከበበው ፡ ከተማ ፡ የአንቀላፋ ፡ ይመስላል ። የቤቶቹ ፡ ጣራና ፡ ምሽጉ ፡ በሩቅ ፡ ካለው ፡ ቃጠሎ ፡ በሚደርሳቸው ፡ ውጋጋን ፡ ብዥ ፡ ብዥ ፡ እያሉ ፡ ይታያሉ ።

አንድሬይ ፡ በተደረደሩት ፡ የኮዛክ ፡ ሠረገላዎች ፡ መካከል ፡ ይጓዝ ፡ ጀመር ። ለጥበቃ ፡ የነደዱት ፡ ደመራዎች ፡ ነደው ፡ ሊያልቁ ፡ ተቃርበዋል ። ዘበኞቹም ፡ እንቅልፍ ፡ ወስዶአቸዋል ። አንድሬይ ፡ በዚህ ፡ ግድየለሽነት ፡ ተገርሞ ፤ «ኃይለኛና ፡ የሚፈራ ፡ ጠላት ፡ በአቅራቢያችን ፡ አለመኖሩ ፡ መልካም ፡ ነው ፡» ብሎ ፡ አሰበ ። በመጨረሻ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ሠረገላ ፡ ሒዶ ፡ ወጣና ፡ እጆቹን ፡ ተንተርሶ ፡ በጀርባው ፡ ተጋደመ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እንቅልፍ ፡ ሊወስደው ፡ ስለአልቻለ ፡ ሰማይ ፡ ሰማዩን ፡ ይመለከት ፡ ጀመር ። በከዋክብት ፡ ብርሃን ፡ የሚብለጨለጨው ፡ ሰማይ ፡ ከፊቱ ፡ ተዘርግቶአል ። አየሩ ፡ ንጹሕና ፡ ጣፋጭ ፡ ነበር ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ አንድሬይ ፡ እንደማናወዝ ፡ እያለ ፡ ስስ ፡ መጋረጃ ፡ ከፊቱ ፡ የተጋረደ ፡ ይመስል ፤ ሰማዩ ፡ ለአንድ ፡ አፍታ ፡ ብዥ ፡ ይልበትና ፡ ወዲያው ፡ ደግሞ ፡ ቁልጭ ፡ ብሎ ፡ ይታየዋል ።

እንዲህ ፡ በሚያናውዝበት ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ እንግዳ ፡ የሆነ ፡ የሰው ፡ ፊት ፡ በዓይኑ ፡ ላይ ፡ የተደቀነ ፡ መሰለው ። ይህም ፡ ሲነቁ ፡ ወዲያው ፡ የሚጠፋ ፡ ቅዠት ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ በማሰብ ፡ ዓይኖቹን ፡ ቢገልጥ ፡ በእውነትም ፡ የጠወለገ ፡ ቀጭን ፡ የሰው ፡ ፊት ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ አጐንብሶ ፡ ዓይን ፡ ዓይኑን ፡ ሲመለከተው ፡ አየ ። እንደ ፡ ከሰል ፡ የጠቆረ ፡ ረጅም ፡ ያልተበጠረ ፡ ጠጉር ፡ ጠቆር ፡ ካለ ፡ ሻሽ ፡ ዘልቆ ፡ ወርዶ ፡ ይታያል ። የዓይኖቹ ፡ ልዩ ፡ ሁናቴና ፡ የቀጭኑ ፡ ፊት ፡ የጠወለገ ፡ የሞት ፡ መልክ ፡ ከአንድ ፡ ልዩ ፡ መንፈስ ፡ በቀር ፡ የሌላ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ያዳግታል ። አንድሬይ ፡ ሽጉጡን ፡ ጨበጠና ፤ «ማነህ? ክፉ ፡ መንፈስ ፡ እንደሆንህ ፡ ሒድ ፡ ጥፋ ፤ ሕይወት ፡ ያለህ ፡ ሰው ፡ እንደሆንህም ፡ ቀልድህ ፡ ለዛ ፡ ያጣ ፡ ነው ። አሁን ፡ ካልሔድህ ፡ በጥይት ፡ እገድልሃለሁ ፡» አለ ።

ለዚህም ፡ መልስ ፡ ከፊቱ ፡ የቆመው ፡ መንፈስ ፡ ጸጥታን ፡ በመጠየቅ ፡ ጣቱን ፡ አፉ ፡ ላይ ፡ አድርጐ ፡ ምልክት ፡ ሰጠው ። አንድሬይም ፡ የቃጣውን ፡ ሽጉጥ ፡ ዝቅ ፡ አደረገና ፡ ይህን ፡ ፍጥረት ፡ ትኩር ፡ ብሎ ፡ ሲመለከተው ፡ የጠጉሩ ፡ ርዝመት ፤ አንገቱ ፡ እንዲሁም ፡ በከፊል ፡ ራቁት ፡ የሆነው ፡ ደረት ፡ የሴት ፡ መሆኑን ፡ ተገነዘበ ። ግን ፡ ይቺ ፡ ሴት ፡ የዚህ ፡ አካባቢ ፡ ተወላጅ ፡ አይደለችም ። ፊትዋ ፡ ጠይም ፡ ነው ፤ ሰፊ ፡ የሆኑት ፡ የጉንጭ ፡ አጥንቶቿም ፡ ከጐደጐደው ፡ ጉንጭዋ ፡ ጋር ፡ ሲተያዩ ፡ አብጠው ፡ የሾሉ ፡ ይመስላሉ ። ጠባብ ፡ የሆነው ፡ የዓይኖችዋ ፡ ቅድም ፡ እንደ ፡ ቀስት ፡ ወደላይ ፡ ጠመም ፡ ያለ ፡ ነው ። የሴትዮዋን ፡ መልክ ፡ አተኩሮ ፡ ሲመለከተው ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ያያት ፡ ሴት ፡ እየመሰለችው ፡ ሔደች ። በመጨረሻ ፡ መታገስ ፡ ሲያቅተው ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጠየቃት ፤

«ማን ፡ እንደሆንሽ ፡ ንገሪኝ? አንድ ፡ ሥፍራ ፡ ያየሁሽ ፡ ይመስለኛል ።»

«የዛሬ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ በኪየቭ ፡ ከተማ ፡ ነው ።»

«የዛሬ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡… በኪየቭ ፡ …» እያለ ፡ አንድሬይ ፡ በተማሪ ፡ ቤት ፡ ያሳለፈውን ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ለማስታወስ ፡ ሞከረ ፤ ወዲያው ፡ እንደገና ፡ ትኩር ፡ ብሎ ፡ ከተመለከታት ፡ በኋላ ፡ «የወየወዱ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ደንገጡር ፡ ታታርዋ ፡ ሴትዮ ፡ ነሽ!» ብሎ ፡ በድንገት ፡ ጮኸ ።

ታታርዋም ፡ «ቀስ!» አለችና ፡ በፍርሃት ፡ እየተንቀጠቀጠች ፡ የአንድሬይን ፡ ጩኸት ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ሰምቶት ፡ እንደሁ ፡ ለማረጋገጥ ፡ ትገላመጥ ፡ ጀመር ።

አንድሬይም ፡ ቀስ ፡ ባለ ፡ ሹክሹክታ ፡ «ንገሪኝ ፡ ለምን ፡ መጣሽ? እመቤትሽ ፡ የት ፡ ናት? ለመሆኑ ፡ ደህና ፡ ናት?» አላት ።

«እዚሁ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ነው ፡ ያሉት ።»

«እዚህ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ?» አሁንም ፡ አንድሬይ ፡ ልቡ ፡ ካለመጠን ፡ እየመታ ፡ ጮኸ ፡ ሊናገር ፡ ምንም ፡ አልቀረውም ።

«ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ምን ፡ ታደርጋለች?»

«ጌቶችም ፡ እዚሁ ፡ ከተማ ፡ ነው ፡ ያሉት ፡ የዱብና ፡ ወየወዳ ፡ ከሆኑ ፡ ዓመት ፡ ከመንፈቅ ፡ ያልፋቸዋል ።»

«ባል ፡ አግብታለች? ንገሪኝ ፡ እንጂ! ምን ፡ ግሩ ፡ የሆንሽ ፡ ፍጥረት ፡ ነሽ! እስዋ ፡ እንዴት ፡ ናት?»

«እመቤቴ ፡ እህል ፡ ከቀመሱ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ሆኖአቸዋል ።»

«እንዴት?»

«የከተማው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ቁራሽ ፡ ዳቦ ፡ ከቀመሰ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ አልፎታል ፤ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከአፈር ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ የሚቀመስ ፡ አላገኘም ።»

አንድሬይ ፡ በድንጋጤ ፡ በድን ፡ ሆነ ።

«እመቤቴ ፡ ከከተማው ፡ ቅጥር ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ከዛፖሮዥያኖች ፡ መካከል ፡ እርስዎን ፡ ስለአዩ ፡ ሒጅና ፡ ያንን ፡ መኮንን ፡ ያስታውሰኝ ፡ እንደሁ ፡ ወደኔ ፡ እንዲመጣ ፤ አለዚያም ፡ ባልቴት ፡ እናቴ ፡ ዓይኔ ፡ ሥር ፡ ስትሞት ፡ ከማይ ፡ ቁራሽ ፡ ዳቦ ፡ እንኳን ፡ ቢሰጥሽ ፡ ይዘሽ ፡ ነይ ። እኔ ፡ ከእስዋ ፡ በፊት ፡ ብሞት ፡ ይሻለኛል ፤ ሒደሽ ፡ እግሩ ፡ ላይ ፡ ወድቀሽ ፡ ለምኚው ፤ እሱም ፡ አሮጊት ፡ እናት ፡ ይኖረዋልና ፡ ለሳቸው ፡ ሲል ፡ እንኳን ፡ እህል ፡ ሊሰጠን ፡ ይገባል ፡ ብለው ፡ ወደርስዎ ፡ ዘንድ ፡ ላኩኝ ።»



የወጣቱ ፡ ኮዛክ ፡ ልብ ፡ በተመሰቃቀሉ ፡ ስሜቶች ፡ ታወከ ።

«ለመሆኑ ፡ አንቺ ፡ እንዴት ፡ ደረስሽ? እንዴት ፡ መጣሽ?»

«በምድር ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ የዋሻ ፡ መንገድ ።»

«የዋሻ ፡ መንገድ ፡ አለ?»

«አለ ።»

«የት?»

«አያጋልጡኝ ፡ እንደሆን ፡ ጌታዬ ።»

«ላላጋልጥሽ ፡ በቅዱስ ፡ መስቀል ፡ እምላለሁ?»

«እንግዲያው ፡ እዚያ ፡ ወዲያ ፡ ያሉትን ፡ ቁጥቋጦች ፡ አልፈው ፡ ሸጥዋን ፡ ይሻገሩና ፡ ቄጠማው ፡ እጅብ ፡ ወደአለበት ፡ ሥፍራ ፡ ይሒዱ ።»

«ዋሻው ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ከተማው ፡ ያደርሳል?»

«ቀጥታ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ያገባል ።»

«በይ ፡ አሁኑኑ ፡ እንሒድ!»

«መጀመሪያ ፡ ስለክርስቶስና ፡ ስለቅድስት ፡ ማርያም ፡ ብለው ፡ አንዲት ፡ ቁራሽ ፡ ዳቦ!»

«ጥሩ ። ይሰጥሻል ፤ እዚህ ፡ ሠረገላው ፡ ጐን ፡ ቁሚ ፤ እንዲያውም ፡ ገብተሽ ፡ ብትጋደሚ ፡ ይሻላል ። ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተኝቶአል ፡ ማንም ፡ የሚያየሽ ፡ የለም ። እኔ ፡ አሁኑኑ ፡ እመለሳለሁ ።»

ከዚያ ፡ ዕቃ ፡ ወደተጫነባቸው ፡ ሠረገላዎች ፡ ሔደ ፤ ልቡ ፡ አለመጠን ፡ ይመታ ፡ ነበር ። በአሁኑ ፡ የኮዛክ ፡ ኑሮው ፡ ተገፍቶ ፡ ወድቆ ፡ የነበረው ፡ ያለፈው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እንደገና ፡ ተመልሶ ፡ በተራው ፡ የአሁኑን ፡ ነገር ፡ ሸፈነው ። ያቺ ፡ ኩሩ ፡ ሴት ፡ ከጠሊቅ ፡ ባህር ፡ ብቅ ፡ ያለች ፡ መስላ ፡ ከፊቱ ፡ ተደቀነች ፤ የተዋቡት ፡ ክንዶችዋ ፤ ዓይኖችዋ ፤ የሚስቁት ፡ ከንፈሮችዋ ፡ ጥቅልል ፡ ጥቅልል ፡ ብሎ ፡ ደረትዋ ፡ ላይ ፡ የወደቀው ፡ ቡና ፡ ቀለም ፡ ጠጉርዋ ፡ ተሟልቶ ፡ የተፈ

ጠረው ፡ ለጋ ፡ ሰውነትዋ ፡ እንደገና ፡ በዓይኑ ፡ ላይ ፡ ውል ፡ አለ ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ጊዜው ፡ ለጠየቀው ፡ ኃይለኛ ፡ ስሜት ፡ ሥፍራ ፡ ለቆ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ከአዕምሮው ፡ አልጠፋም ፡ ነበር ። የወጣቱን ፡ ኮዛክ ፡ እንቅልፍ ፡ ስንት ፡ ቀን ፡ ቢያወከው ፡ ኖሮአል! ብዙ ፡ ጊዜም ፡ ከእንቅልፉ ፡ እየነቃ ፡ ምክንያቱን ፡ ሳያውቀው ፡ ሳይተኛ ፡ ይነጋ ፡ ነበር ።

እሁን ፡ ወደ ፡ ሠረገላው ፡ ሲያመራ ፡ እንደገና ፡ እንደሚያየት ፡ በማሰብ ፡ ብቻ ፡ ልቡ ፡ በኃይል ፡ እየመታ ፡ ጉልበቱም ፡ ተንቀጠቀጠ ። ሠረገላዎቹ ፡ ካሉበት ፡ ሥፍራ ፡ ሲደርስ ፡ የመጣበትን ፡ ምክንያት ፡ ጨርሶ ፡ ረስቶታል ፤ ለማስታወስም ፡ ግንባሩን ፡ እያሸ ፡ ብዙ ፡ ካሰበ ፡ በኋላ ፡ ያች ፡ ውብ ፡ ወይዘሮ ፡ በረሃብ ፡ ልትሞት ፡ መሆኑ ፡ ትዝ ፡ ቢለው ፡ ከእግር ፡ እስከ ፡ ራሱ ፡ በፍርሃት ፡ ተንቀጠቀጠ ። ከሠረገላዎቹ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ዘሎ ፡ ወጥቶ ፡ ብዙ ፡ ትልልቅ ፡ ዳቦ ፡ ታቅፎ ፡ ወጣ ። ነገር ፡ ግን ፡ እንዲያ ፡ ያለው ፡ ዳቦ ፡ ለግድ ፡ የለሹ ፡ ዛፖሮዥያን ፡ ተስማሚ ፡ ቢሆንም ፡ ለለስላሳው ፡ ለእስዋ ፡ ተፈጥሮ ፡ እንደማይሆን ፡ አመዛዘነ ። ወዲያው ፡ ያን ፡ ቀን ፡ በእራት ፡ ላይ ፡ ለሦስት ፡ ቀን ፡ የሚሆነውን ፡ የገንፎ ፡ እህል ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ አገነፋችሁት ፡ በማለት ፡ ኮሼቮይ ፡ አብሳዮቹን ፡ መቅጣቱ ፡ ትዝ ፡ አለውና ፡ ብዙ ፡ የተረፈ ፡ ገንፎ ፡ እንደሚያገኝ ፡ እርግጠኛ ፡ ሆኖ ፡ የአባቱን ፡ የገንፎ ፡ ገንቦ ፡ ያዘና ፡ የሠፈሩ ፡ ምግብ ፡ አብሳይ ፡ ወደአለበት ፡ ሥፍራ ፡ ሔደ ። አብሳዩም ፡ አሥር ፡ ገንቦ ፡ በሚይዙ ፡ ትልልቅ ፡ የብረት ፡ ድስቶች ፡ መካከል ፡ ተጋድሞ ፡ እንቅልፍ ፡ ወስዶታል ። ብረት ፡ ድስቶቹ ፡ የተጣዱበት ፡ የብረት ፡ ድስቶች ፡ እሳት ፡ ከስሎ ፡ ገና ፡ አሁንም ፡ አልጠፋም ። አንድሬይ ፡ ወደ ፡ ብረት ፡ ድስቶቹ ፡ ተጠግቶ ፡ ቢመለከት ፡ ሁለቱም ፡ ድስቶቹ ፡ ባዶ ፡ ሆነው ፡ ስላያቸው ፡ ደነገጠ ። ያን ፡ ሁሉ ፡ ገንፎ ፡ የጨረሱት ፡ ልዩ ፡ ፍጥረቶች ፡ እንደሆኑ ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ ሊሆኑ ፡ አይችሉም ። በተለይ ፡ በዚያ ፡ ሠፈር ፡ የተመደቡት ፡ ሰዎች ፡



በሌሎቹ ፡ ከተመደቡት ፡ በቁጥር ፡ ያነሱ ፡ ስለነበሩ ፡ አንድሬይ ፡ በጣም ፡ ተገረመ ። ወደሌሎች ፡ ሠፈሮችም ፡ ሔደ ። ድስቶቹን ፡ ቢፈትሽ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አጣ ። «ዛፖሮዥያኖች ፡ እንደ ፡ ሕፃናት ፡ ናቸው ፤ ትንሽ ፡ ምግብ ፡ ሲኖር ፡ ይበሉታል ፤ ብዙ ፡ ያለ ፡ እንደሆንም ፡ ምንም ፡ አያስተርፉም ፡» የሚባለው ፡ ተረት ፡ ትዝ ፡ አለው ።

እንግዲህ ፡ ምን ፡ ያድርግ? በአባቱ ፡ የጦር ፡ ክፍል ፡ በሚገኝ ፡ አንድ ፡ ሠረገላ ፡ ውስጥ ፡ የገዳሙ ፡ ዕቃ ፡ ቤት ፡ ሲዘረፍ ፡ የተገኘ ፡ አንድ ፡ ከረጢት ፡ ለስላሳ ፡ የስንዴ ፡ ዳቦ ፡ ነበር ። ወዲያው ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ ሠረገላ ፡ ቢሔድ ፡ ከረጢቱ ፡ እዚያ ፡ የለም ፤ እስታፕ ፡ ከረጢቱን ፡ ተንተርሶ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ተጋድሞ ፡ አካባቢው ፡ ሁሉ ፡ እስኪያስተጋባ ፡ ያንኳርፍ ፡ ነበር ። አንድሬይ ፡ ከረጢቱን ፡ በአንድ ፡ እጁ ፡ ያዘና ፡ በኃይል ፡ ሲመነጭቀው ፡ የእስታፕ ፡ ጭንቅላት ፡ ከመሬቱ ፡ ጋር ፡ ተጋጨ ። እስታፕ ፡ ከእንቅልፉ ፡ ባንኖ ፡ ዓይኖቹን ፡ ሳይገልጥ ፡ ቁጭ ፡ እንዳለ ፤ «ያዙት ፡ ይህን ፡ የፖሊሽ ፡ ሰይጣን! ፈረሱን ፡ ያዙት! ያዙት!» ብሎ ፡ በኃይል ፡ ጮኸ ።

አንድሬይም ፡ በድንጋጤ ፡ የያዘውን ፡ ከረጢት ፡ በመቃጣት ፡ አንሥቶ ፡ «ዝም ፡ በል ፡ አለዚያ ፡ እገድልሃለሁ!» ብሎ ፡ ጮኸበት ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ወንድሙን ፡ መግደል ፡ ምንም ፡ አስፈላጊ ፡ አልሆነም ፤ ምክንያቱም ፡ እስታፕ ፡ የቅዠት ፡ ንግግሩን ፡ አቆመና ፡ ወደኋላው ፡ ተፈንግሎ ፡ በዙሪያው ፡ ያለው ፡ ሣር ፡ ሁሉ ፡ እስኪንቀጠቀጥ ፡ ድረስ ፡ ማንኳረፍ ፡ ቀጠለ ። የእስታፕ ፡ ቅዠት ፡ ሌሎች ፡ ኮዛኮችን ፡ ቀስቅሶ ፡ እንደሆን ፡ በማለት ፡ አንድሬይ ፡ አካባቢውን ፡ በጥንቃቄ ፡ ተመለከተ ። አንድ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ከአቅራቢያው ፡ አንገቱን ፡ ቀና ፡ አድርጎ ፡ በእንቅልፍ ፡ ልቡ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ ፡ ወዲያው ፡ ተመልሶ ፡ ሲተኛ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የነቃ ፡ ሰው ፡ አልነበረም ። አንድሬይ ፡ ለማረጋገጥ ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ ደቂቃ ፡ ያህል ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ ከረጢቱን ፡ ተሸክሞ ፡

ሔደ ። ታታርዋ ፡ ሴትዮ ፡ በፍርሃት ፡ ትንፋሽዋን ፡ ውጣ ፡ እንደ ፡ ተጋደመች ፡ ነበረች ።

«ነይ ፤ ተነሺ ፤ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተኝቶአል ፤ ምንም ፡ አትፍሪ ። ሁሉንም ፡ መሸከም ፡ ያልቻልኩ ፡ እንደሆን ፡ አንዱን ፡ ዳቦ ፡ ለመያዝ ፡ ትችይ ፡ ይሆን?» አላትና ፡ ከረጢቱን ፡ በትከሻው ፡ ተሸክሞ ፡ እግረ ፡ መንገዱንም ፡ ከአንድ ፡ ሠረገላ ፡ ላይ ፡ ዱቄት ፡ የተሞላ ፡ ሌላ ፡ ከረጢት ፡ አንሥቶ ፡ ይዞ ፡ ታታርዋን ፡ ተሸካሚ ፡ ያላትን ፡ ዳቦ ፡ እንኳን ፡ ሳይቀር ፡ በክንዱ ፡ አቅፎ ፡ በተኙት ፡ ዛፖሮዥያኖች ፡ መካከል ፡ በድፍረት ፡ መንገድ ፡ ጀመረ ።

ወዲያው ፡ በሽማግሌው ፡ አባቱ ፡ በታራስ ፡ ቡልባ ፡ አጠገብ ፡ ሲያልፉ ፡ አባትየው ፡ «አንድሬይ!» አለና ፡ ተጣራ ።

አንድሬይም ፡ በድንጋጤ ፡ ልቡ ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ከእግር ፡ እስከ ፡ ራሱ ፡ እየተንቀጠቀጠ ፡ ቆመና ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ «ምንድነው?» አለ ።

«ሴት ፡ አብራህ ፡ አለች! ቆይ ፡ ስነሣ ፡ በቁምህ ፡ ነው ፡ ቆዳህን ፡ የምገፈው! ሴቶች ፡ ለምንም ፡ አይጠቅሙህ!» አለና ፡ ቡልባ ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ የተሸፋፈነችውን ፡ ታታር ፡ በቁጣ ፡ ተመለከታት ።

አንድሬይ ፡ የአባቱን ፡ ፊት ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ማየት ፡ ፈርቶ ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ በድን ፡ እቆመበት ፡ ሥፍራ ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ ቀና ፡ ቢል ፡ ቡልባ ፡ እጁን ፡ ትራስ ፡ አድርጎ ፡ ወዲያው ፡ እንቅልፍ ፡ ወስዶታል ። አንድሬይ ፡ ከጭንቅ ፡ በመውጣቱ ፡ አማተበ ። ድንጋጤና ፡ ፍርሃቱም ፡ ከአመጣጡ ፡ በበለጠ ፡ ፍጥነት ፡ ለቅቆት ፡ ሔደ ። ታታርዋን ፡ ለማየት ፡ ዘወር ፡ ቢል ፡ እንደተሸፋፈነች ፡ ሐውልት ፡ መስላ ፡ ከሩቅ ፡ በሚመጣው ፡ የቃጠሎ ፡ ብርሃን ፡ ዓይኖችዋ ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ፍም ፡ ዓይን ፡ ቁልጭ ፡ ብለው ፡ እየታዩ ፡ ቆማለች ። ወዲያው ፡ የቀሚስዋን ፡ እጅጌ ፡ ጐተት ፡ ሲያደርገው ፡ ተከተለችውና ፡ እየተገላመጡ ፡ አንዲት ፡ ቁልቁለት ፡ ወርደው ፡ በቁጥቋጦ ፡ የተሸፈነች ፡ ጠባብ ፡ ሸጥ ፡ ተሻገሩ ።



ቁልቁለቱን ፡ ከወረዱ ፡ ወዲያ ፡ ከኮዛኮቹ ፡ ሠፈር ፡ ተሰውረው ፡ አይታዩም ፡ ነበር ። አንድሬይ ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ሲመለከት ፡ ከአቀበቱ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ የበቀለው ፡ ሣር ፡ ብቻ ፡ ከሰማዩ ፡ ጋር ፡ የገጠመ ፡ መስሎ ፡ ታየው ። በዚያ ፡ ሰዓት ፡ የሚነፍሰው ፡ ቀለል ፡ ያለ ፡ ነፋስ ፡ ጐሕ ፡ ሊቀድ ፡ መቃረቡን ፡ አስታወሰው ። በከተማውም ፡ ሆነ ፡ በተወረረው ፡ አካባቢ ፡ አንድም ፡ ዶሮ ፡ ስለአልተረፈ ፡ የዶሮ ፡ ጩኸት ፡ አይሰማም ። ሸጥዋን ፡ ከተሻገሩ ፡ በኋላ ፡ ከፊታቸው ፡ ያገኙት ፡ አቀበት ፡ ከወረዱት ፡ ቁልቁለት ፡ የባሰ ፡ ረጅምና ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፡ ነበር ። በዚያ ፡ አቅራቢያ ፡ ያለው ፡ የምሽግ ፡ ግንብ ፡ በጣም ፡ አጭርና ፡ ወታደርም ፡ የማይታይበት ፡ ስለነበር ፡ አቀበቱ ፡ በተፈጥሮው ፡ ለከተማው ፡ ምሽግ ፡ ሆኖ ፡ የተሠራ ፡ ይመስላል ፤ ቀጥ ፡ ያለው ፡ አቀበት ፡ በቁጥቋጦና ፡ በአረም ፡ የተሸፈነ ፡ ሲሆን ፡ ከአቀበቱ ፡ መደብና ፡ ከውኃው ፡ መካከል ፡ ረጅም ፡ ሰው ፡ የሚውጥ ፡ ቄጠማ ፡ በቅሎአል ። ከቄጠማው ፡ አለፍ ፡ ብሎ ፡ ቀድሞ ፡ በአታክልት ፡ ዙሪያ ፡ የታጠረ ፡ የፈራረሰ ፡ አጥር ፡ ይታያል ። ከአጥሩም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አታክልቶች ፡ አሉ ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ሥፍራው ፡ ጨፌና ፡ በውኃ ፡ የተሸፈነ ፡ ስለነበር ፡ ታታርዋ ፡ ጫማዋን ፡ አውልቃና ፡ ቀሚስዋን ፡ ሰብስባ ፡ በባዶ ፡ እግርዋ ፡ በጥንቃቄ ፡ ትራመድ ፡ ጀመር ። ወዲያው ፡ ቁጥቋጠዎቹን ፡ ገለጥ ፡ ስታደርግ ፡ ጠባብ ፡ የዋሻ ፡ በር ፡ ብቅ ፡ አለ ። ታታርዋ ፡ ቀድማ ፡ ገባች ፤ አንድሬይም ፡ ከነሸክሙ ፡ ለመግባት ፡ ሲል ፡ በጣም ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ ተከተላት ፤ ወዲያው ፡ ጥቅጥቅ ፡ ያለ ፡ ጨለማ ፡ ዋጣቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ስድስት ።

አንድሬይ ፡ ከረጢቶቹን ፡ እንደተሸከመ ፡ በጨለማው ፡ ዋሻ ፡ ታታርዋን ፡ ተከትሎ ፡ በዳበሣ ፡ ይጓዝ ፡ ጀመር ።

.«በቅርቡ ፡ ብርሃን ፡ እናገኛለን ፤ ፋኖሱን ፡ ከአስቀመ
ጥኩበት ፡ ሥፍራ ፡ ደርሰናል ፡» አለችው ።

በእውነትም ፡ ደብዘዝ ፡ ያለ ፡ ብርሃን ፡ መንገዳቸውን ፡
ያሳያቸው ፡ ጀመር ። ወዲያው ፡ ከአካባቢው ፡ ትንሽ ፡ ሰፋ ፡
ካለ ፡ ሥፍራ ፡ ደረሱ ። ይህ ፡ ሥፍራ ፡ የጸሎት ፡ ቤት ፡ ሳይ
ሆን ፡ አይቀርም ። ምክንያቱም ፡ ከወደ ፡ ጥግ ፡ በኩል ፡ እንደ
መቅደስ ፡ ያለ ፡ አንድ ፡ ጠባብ ፡ ጠረጴዛ ፡ ተቀምጦ ፡ ከበላ
ዩም ፡ መልኩ ፡ በጣም ፡ የተበላሸ ፡ የካቶሊኮች ፡ የማርያም ፡
ሥዕል ፡ ተሰቅሎአል ። ትንሽ ፡ የብር ፡ ኩራዝ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡
ተንጠልጥሎ ፡ በሥዕሉ ፡ ላይ ፡ ደብዘዝ ፡ ያለ ፡ ብርሃን ፡ ይፈ
ነጥቃል ። ታታርዋ ፡ ጐንበስ ፡ ብላ ፡ እዚያው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡
አስቀምጣው ፡ የነበረውን ፡ ከመዳብ ፡ የተሠራ ፡ ፋኖስ ፡ አን
ስታ ፡ ጠፍቶ ፡ ስለነበር ፡ ከሥዕሉ ፡ መብራት ፡ እሳት ፡ አያያዘ
ች ። ብርሃኑ ፡ እየደመቀ ፡ ሔደ ። ከዚያ ፡ ፊትና ፡ ኋላ ፡ ተከ
ታትለው ፡ መንገዳቸውን ፡ ቀጠሉ ። በጤንነት ፡ የተጠበ
ቀው ፡ የአንድሬይ ፡ የተዋበ ፡ የወጣትነት ፡ መልክና ፡ አብ
ራው ፡ ያለችው ፡ ጓደኛው ፡ የከሣ ፡ ፊት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ልዩ
ነት ፡ ነበረው ። ዋሻው ፡ እየሰፋ ፡ ስለሔደ ፡ አንድሬይ ፡ ቀጥ ፡
ብሎ ፡ ለመቆም ፡ ቻለ ። የዋሻውን ፡ ግድግዳ ፡ በመገረም ፡ እየ
ተመለከተ ፡ ኪዩቭ ፡ ያሉት ፡ የዋሻ ፡ መቃብሮች ፡ ትዝ ፡
አሉት ። እንደ ፡ ኪዩቭ ፡ የዋሻ ፡ መቃብሮች ፡ ሁሉ ፡ እዚህ
ም ፡ በግርግዳው ፡ ላይ ፡ ተቆፍረው ፡ በተሠሩ ፡ መደቦች ፡ ላይ ፡
በአንዳንዶቹ ፡ የሬሣ ፡ ሣጥኖች ፡ ቆመው ፡ ሲታዩ ፡ በሌሎ
ች ፡ ደግሞ ፡ በእርጥበት ፡ የሻገተ ፡ የሰው ፡ አጽም ፡ ተከምሮ
አል ። እንዲሁም ፡ በዚህ ፡ ዋሻ ፡ አንዳንድ ፡ ቅዱሳን ፡ የሆኑ ፡
ሰዎች ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ሐዘንና ፡ መከራ ፡ ሸሽተው ፡ በሱ
ባኤ ፡ ሳይቀመጡበት ፡ አልቀሩም ። አንዳንድ ፡ ቦታ ፡ በጣም ፡
ጨለማ ፡ ነበር ። አልፎ ፡ አልፎም ፡ ከእግራቸው ፡ ሥር ፡ ውኃ ፡
ይሰማቸዋል ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አንድሬይ ፡ የጉዞ ፡ ጓደኛው ፡ ድ
ካም ፡ በአረማመድዋ ፡ ይታይ ፡ ስለነበር ፡ እንድታርፍ ፡ መ



ቆም ፡ ግድ ፡ ሆነበት ። አንዲት ፡ ጉርሻ ፡ ዳቦ ፡ ብትውጥ ፡ ሆድ ፡
ቁርጠት ፡ ሆኖባት ፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መራመድ ፡ እያቃታት ፡
ቀጥ ፡ ብላ ፡ ትቆም ፡ ነበር ። በመጨረሻ ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡
የብረት ፡ መዝጊያ ፡ ከፊታቸው ፡ ታያቸው ። «ተመስገን ፡
አምላኬ ፡ ደረስን!» ብላ ፡ ታታርዋ ፡ በሩን ፡ ለማንኳኳት ፡
እጅዋን ፡ ብታነሣ ፡ አቅም ፡ አነሣት ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ አንድ
ሬይ ፡ ሔደና ፡ በሩን ፡ በኃይል ፡ አንኳኳው ። ከበሩ ፡ አልፎ ፡
ሰፊ ፡ ሥፍራ ፡ መኖሩን ፡ የሚያስረዳ ፡ ቀበሌ ፡ ተሰማ ። ወዲ
ያው ፡ ከአንድ ፡ ከሁለት ፡ ደቂቃ ፡ በኋላ ፡ ቁልፍ ፡ ሲንኳኳና ፡
አንድ ፡ ሰው ፡ በደረጃ ፡ ሲወርድ ፡ ተሰማ ። በመጨረሻ ፡ በሩ ፡
ተከፈተና ፡ በአንድ ፡ እጁ ፡ ሻማ ፡ በሌላው ፡ ደግሞ ፡ ብዙ ፡
ቁልፍ ፡ የያዘ ፡ አንድ ፡ መነኩሴ ፡ በጠባብ ፡ የመተላለፊያ ፡
ደረጃ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ አገኙ ። በኮዛኮች ፡ መካከል ፡ እጅግ ፡ ከመ
ጠላታቸው ፡ የተነሣ ፡ ከአይሁዶች ፡ የባሰ ፡ የጭካኔ ፡ ፍርድ ፡
ከሚፈጸምባቸው ፡ የካቶሊክ ፡ መነኮሣት ፡ አንዱ ፡ የሆነው ፡
ይህ ፡ መነኩሴ ፡ እፊቱ ፡ ቆሞ ፡ ሲመለከት ፡ አንድሬይ ፡ ሳ
ያስበው ፡ ደሙ ፡ ፈላ ። መነኩሴውም ፡ የዛፖሮዥያን ፡ ኮዛ
ክ ፡ በማየቱ ፡ ደንግጦ ፡ ሳለ ፡ ታታርዋ ፡ በሹክሹክታ ፡ ስታ
ነጋግረው ፡ ልቡ ፡ ረጋ ። ወዲያው ፡ በሩን ፡ ቆልፎ ፡ በደረ
ጃው ፡ አሳለፋቸውና ፡ በጨለማው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡
ሕንፃ ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ መሆናቸውን ፡ አወቁ ። ረጃጅም ፡ ሻ
ማዎች ፡ በሚበሩበት ፡ በአንዱ ፡ መቅደስ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡
አንድ ፡ ቄስ ፡ ተንበርክከው ፡ በለሰለሰ ፡ ድምጽ ፡ ጸሎት ፡
ያደርሳሉ ። ከቄሱም ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ የለበሱ ፡
ሁለት ፡ ወጣት ፡ ዲያቆኖች ፡ መአጠንት ፡ ይዘው ፡ ተንበርክ
ከዋል ። ቄሱ ፡ የሚያደርሱት ፡ ፀሎት ፡ አንድ ፡ አምላካዊ ፡
ተአምር ፡ ወርዶ ፡ ከተማው ፡ እንዲድን ፤ ምሽጉ ፡ እንዲጠ
ነክር ፤ ሕዝቡም ፡ በደረሰበት ፡ ምድራዊ ፡ ክፉ ፡ ዕድል ፡ ትእ
ግስት ፡ እንዲያገኝ ፡ የሚለማመን ፡ ፀሎት ፡ ነበር ። ጥቂት ፡
ሴቶች ፡ ተንበርክከው ፡ ከድካማቸውም ፡ የተነሣ ፡ እፊታ

ቸው ፡ ያሉትን ፡ የወንበር ፡ ድጋፎች ፡ ተደግፈዋል ። አንዳንድ ፡ ወንዶችም ፡ የሕንፃውን ፡ ምሰሶዎች ፡ እየተደገፉ ፡ በሐዘን ፡ ተክዘው ፡ ተንበርክከዋል ። ከመቅደሱ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቀለም ፡ የተቀባ ፡ የመስኮት ፡ መስተዋት ፡ የጐህ ፡ ብርሃን ፡ ገብቶ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ አዳራሽ ፡ ፈገግ ፡ አለ ። በሚገባውም ፡ ጮራ ፡ ዲያቆናቱ ፡ ከያዙት ፡ መአጠንት ፡ የሚወጣው ፡ የእጣን ፡ ጢስ ፡ እንደ ፡ ቀስተ ፡ ደመና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለማት ፡ ይዞ ፡ ይታይ ፡ ነበር ። አንድሬይ ፡ ከቆመበት ፡ ጨለማ ፡ ሥፍራ ፡ ሆኖ ፡ የገባው ፡ ብርሃን ፡ ያመጣውን ፡ አስደናቂ ፡ ለውጥ ፡ ተመልክቶ ፡ ተገረመ ። ወዲያው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግርማ ፡ ያለው ፡ የኦርጋኑ ፡ ድምጽ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ ሞላው ። ኦርጋኑም ፡ እንደ ፡ ነጐድጓድ ፡ በሚዝገመገምና ፡ ወዲያው ፡ ደግሞ ፡ በለሰለሰ ፡ ጣፋጭ ፡ ስልት ፡ ከተሰማ ፡ በኋላ ፡ ዝም ፡ ሲል ፡ ቀበሌው ፡ ግን ፡ በሕንፃው ፡ ውስጥ ፡ ሲያስተጋባ ፡ ብዙ ፡ ቆየ ። አንድሬይም ፡ አፉን ፡ ከፍቶ ፡ ቆሞ ፡ በዚህ ፡ ባለታላቅ ፡ ግርማ ፡ ሙዚቃ ፡ ተገረመ ። ወዲያው ፡ ታታርዋ ፡ ልብሱን ፡ ጐተት ፡ አደረገችና ፡ «እንሒድ!» አለችው ። ማንም ፡ ሰው ፡ ሳያስተውላቸው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ አቋርጠው ፡ ወጡና ፡ ውጭ ፡ ካለው ፡ አደባባይ ፡ ደረሱ ። አደባባዩ ፡ አራት ፡ ማዕዘን ፡ ሲሆን ፡ በዚያ ፡ ሰዓት ፡ ባዶ ፡ ነበር ። ምናልባት ፡ ከአንድ ፡ ሳምንት ፡ በፊት ፡ በዚህ ፡ አደባባይ ፡ ሽቀጣ ፡ ሸቀጥ ፡ ይገበይ ፡ እንደነበር ፡ የሚያስረዱ ፡ አንዳንድ ፡ የነጋዴ ፡ መደቦች ፡ አሉ ። በዚያ ፡ ዘመን ፡ በየትም ፡ ሥፍራ ፡ እንደሚታየው ፡ ሁሉ ፡ የከተማው ፡ መንገድ ፡ ድንጊያ ፡ በመነጠፍ ፡ ፈንታ ፡ በአፈር ፡ የተደመደመ ፡ ነው ። አደባባዩ ፡ ከጭቃ ፡ ወይም ፡ ከድንጋይ ፡ በተሠሩ ፡ ትናንሽ ፡ ቤቶች ፡ ተከቦአል ። በአንድ ፡ ወገን ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ ምናልባት ፡ የከተማው ፡ አዳራሽ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ የመንግሥት ፡ ድርጅት ፡ የያዘ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ከሌሎቹ ፡ ቤቶች ፡ ጐልቶ ፡ የሚታይ ፡ ረዘም ፡ ያለ ፡ ሕንፃ ፡



አለ ። ይህም ፡ ሕንፃ ፡ ባለሁለት ፡ ፎቅ ፡ ሲሆን ፡ በላዩም ፡ በሚገኝ ፡ ተጨማሪ ፡ ደርብ ፡ ዘበኛ ፡ ቆሞአል ። በዘበኛው ፡ መቆሚያ ፡ ጣራ ፡ ላይ ፡ ሰፊ ፡ የሰዓት ፡ መልክ ፡ ተቀርጾአል ። መላው ፡ አደባባይ ፡ የሞተ ፡ ይመስላል ። አንድሬይ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ የደከመ ፡ የሚያቃስት ፡ ድምጽ ፡ ተሰማውና ፡ ወደኋላው ፡ ዘወር ፡ ሲል ፡ አደባባዩን ፡ አቋርጦ ፡ በወዲያኛው ፡ ገጽ ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ በድን ፡ መስለው ፡ ተጋድመው ፡ አየ ። ተኝተው ፡ ይሆን ፡ ወይስ ፡ ሞተዋል ፡ በማለት ፡ አተኩሮ ፡ እያየ ፡ ለማጣራት ፡ ሲሞክር ፡ ወዲያው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እግሩን ፡ አደናቀፈው ። ወደ ፡ ታች ፡ ሲመለከትም ፡ ያደናቀፈው ፡ ነገር ፡ የአንዲት ፡ የአይሁድ ፡ ሴት ፡ሬሣ ፡ ሆኖ ፡ አገኘው ። ምንም ፡ እንኳን ፡ የተጐሳቆለው ፡ ፊትዋ ፡ አሁን ፡ ሊያረጋግጥ ፡ ባይችልም ፡ ሴትዮዋ ፡ ገና ፡ ወጣት ፡ ሳትሆን ፡ አልቀረችም ። በራስዋ ፡ ላይ ፡ ቀይ ፡ የሃር ፡ ሻሽ ፡ ታሥሮአል ። በጆሮዎችዋ ፡ ላይ ፡ የሉል ፡ ወይም ፡ የጨሌ ፡ ጌጥ ፡ አንጠልጥላለች ። ጐንዋ ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ተጋድሞ ፡ ጡትዋን ፡ በእጁ ፡ እንደጨበጠ ፡ ወተት ፡ ሲያጠባት ፡ ጊዜ ፡ በጭንቅ ፡ ብስጭት ፡ ጠምዝዞ ፡ ይዞታል ። ሕፃኑ ፡ ልቅሶውም ፡ ጩኸቱም ፡ አቁሞአል ። ነፍሱ ፡ ላለመውጣትዋ ፡ ምልክት ፡ የሆነው ፡ በእርጋታ ፡ ሲንቀሳቀስ ፡ የሚታየው ፡ ሆዱ ፡ ብቻ ፡ ነበር ። በአንድ ፡ መንገድ ፡ አጠፍ ፡ ሲሉ ፡ አንድ ፡ እብድ ፡ ሰውየ ፡ አጋጠማቸውና ፡ አንድሬይ ፡ የተሸከመውን ፡ እቃ ፡ በማየት ፡ እብዱ ፡ ሰውየ ፡ «ዳቦ!» ብሎ ፡ ጮኸ ፡ እንደነብር ፡ ጉብ ፡ አለበት ። ነገር ፡ ግን ፡ ጉልበቱ ፡ የእብደቱን ፡ ያህል ፡ ስላልነበር ፡ አንድሬይ ፡ ገፍተር ፡ ሲያደርገው ፡ በጀርባው ፡ ወድቆ ፡ ተዘረጋ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ አንድሬይ ፡ በርኅራኄ ፡ ልቡ ፡ ተነክቶ ፡ አንድ ፡ ዳቦ ፡ ሲጥልለት ፡ ዳቦውን ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ አበደ ፡ ውሻ ፡ ተናነቀው ። ነገር ፡ ግን ፡ ለብዙ ፡ ቀናት ፡ እህል ፡ አልቀመሰም ፡ ነበርና ፡ ወዲያው ፡ እዚያው ፡ ያለበት ፡ ሥፍራ ፡ ሆድ ፡ ቁር

ጠት ፡ ያሰቃየው ፡ ጀመር ። በየደረሱበት ፡ ርሃቡ ፡ ያደረሰውን ፡ አሰቃቂ ፡ ነገር ፡ ያይ ፡ ጀመር ። ብዙዎቹ ፡ ሰዎች ፡ ስቃያቸውን ፡ በቤታቸው ፡ ውስጥ ፡ እንዳሉ ፡ ለመቀበል ፡ ስለ አልቻሉ ፡ በአንድ ፡ ዓይነት ፡ ታምር ፡ ከአየሩ ፡ መድኃኒት ፡ የሚያገኙ ፡ ይመስል ፡ ወደውጭ ፡ በየመንገዱ ፡ ላይ ፡ ወጥተው ፡ ኖሮአል ። በአንድ ፡ ቤት ፡ ደጃፍ ፡ ላይ ፡ አንዲት ፡ ባልቴት ፡ ተቀምጠው ፡ ሞተው ፡ እንደሁና ፡ እንቅልፍ ፡ ይውሰዳቸው ፡ ለማወቅ ፡ ያዳግታል ። ሆኖም ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ የተቀመጡት ፡ ባልቴት ፡ ሳይንቀሳቀሱ ፡ ድርቅ ፡ ከማለታቸው ፡ የተነሣ ፡ ማየት ፡ ወይም ፡ መስማት ፡ እንደማይችሉ ፡ ግልጽ ፡ ነበር ። ከሌላ ፡ ቤት ፡ ጣራ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ በገመድ ፡ የተንጠለጠለ ፡ አንድ ፡ የተሸማቀቀ ፡ ሬሣ ፡ ይታያል ። ይህ ፡ ያልታደለ ፡ ሰው ፡ የርሃብን ፡ ስቃይ ፡ መቻል ፡ ሲያቅተው ፡ ጊዜ ፡ ሕይወቱን ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ ማጥፋት ፡ መርጦ ፡ በገመድ ፡ ታንቆ ፡ ሞቶአል ።

ይህን ፡ ሁሉ ፡ አሰቃቂ ፡ የርሃብ ፡ ውጤት ፡ በመመልከቱ ፡ አንድሬይ ፡ አላስችል ፡ አለውና ፡ ታታርዋን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጠየቃት ፤

«ሕይወታቸውን ፡ ለማቆየት ፡ ያህል ፡ እንኳን ፡ በእውነት ፡ የሚቀምሱት ፡ ነገር ፡ አጥተው ፡ ነው? መቼም ፡ ሰው ፡ ችግር ፡ ሲበዛበት ፡ ያለውን ፡ በልቶ ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ በሕግ ፡ የተከለከሉትን ፡ ፍጥረቶች ፡ እንኳን ፡ መመገብ ፡ አለበት ።»

ታታርዋም ፡ «ሁሉም ፡ ተበልቶአል ፤ ያለው ፡ እንስሳት ፡ ሁሉ ፡ ለምግብ ፡ ሆኖአል ፤ አንድ ፡ ፈረስ ፡ ወይ ፡ አንድ ፡ ውሻ ፡ አንዲት ፡ አይጥ ፡ እንኳን ፡ በከተማው ፡ ውስጥ ፡ አይገኝም ። በከተማው ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ ስንቅ ፡ አከማችተን ፡ አናውቅም ፡ ነበር ። ምግብ ፡ ሁሉ ፡ የሚመጣልን ፡ በአካባቢው ፡ ካሉት ፡ መንደሮች ፡ ነው ።» አለችው ።



«ታዲያ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ አሰቃቂ ፡ ሞት ፡ እየሞታችሁ ፡ አሁንም ፡ ከተማውን ፡ እንደያዛችሁ ፡ ለመቆየት ፡ እንዴት ፡ ታስባላችሁ?»

«አዎ ፤ ወየወዳ ፡ እንኳን ፡ ተስፋ ፡ ቆርጠው ፡ ባስረከቡ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ትላንት ፡ ጠዋት ፡ በቡድዣኒ ፡ ያሉት ፡ ኰሎኔል ፡ ከተማው ፡ ለጠላት ፡ እንዳይለቀቅ ፡ በመከልከል ፡ መልዕክት ፡ የያዘ ፡ አንድ ፡ አሞራ ፡ ልከው ፡ እሳቸው ፡ ለእርዳታ ፡ ሊደርሱልን ፡ ተጨማሪ ፡ ጦር ፡ የያዙ ፡ ኰሎኔል ፡ በመጠበቅ ፡ ላይ ፡ መሆናቸውን ፡ ስለገለጹ ፡ ይኸው ፡ አሁን ፡ ይመጣሉ ፡ ተብለው ፡ ይጠበቃሉ ። ይኸው ፡ አሁን ፡ ከቤቱ ፡ ደረሰን ።»

ከሌሎቹ ፡ ሁሉ ፡ የተለየ ፡ ምናልባት ፡ በኢጣልያ ፡ መሐንዲስ ፡ የተሠራ ፡ አንድ ፡ ቤት ፡ አንድሬይ ፡ ገና ፡ ከሩቁ ፡ ተመልክቶ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ቤት ፡ ባለሁለት ፡ ፎቅ ፡ ሲሆን ፡ በተዋበ ፡ ጡብ ፡ ድንጋይ ፡ የታነጸ ፡ ነው ። ይህ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቅስት ፡ ያጌጠው ፡ ሕንፃ ፡ በበሩ ፡ መድረክ ፡ ወደ ፡ አደባባዩ ፡ የሚያወርድ ፡ ቀለም ፡ ከተቀቡ ፡ ሸክላዎች ፡ የተሠራ ፡ ሰፊ ፡ ደረጃ ፡ ነበረው ። ከደረጃው ፡ ሥር ፡ በአንድ ፡ እጃቸው ፡ ጦራቸውን ፡ ይዘው ፡ በሌላው ፡ ደግሞ ፡ ያቀረቀረውን ፡ እራሳቸውን ፡ የደገፉ ፡ ሁለት ፡ ዘበኞች ፡ ተቀምጠዋል ። ዘበኞቹ ፡ ከሰው ፡ ይልቅ ፡ ሐውልት ፡ መስለው ፡ ይታዩ ፡ ነበር ። እንቅልፍ ፡ የወሰዳቸው ፡ አይመስሉም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ዘበኛ ፡ ሆነው ፡ ተቀምጠው ፡ በደረጃው ፡ የሚወጡትን ፡ ሰዎች ፡ ቀና ፡ ብለው ፡ እንኳን ፡ አይመለከቱም ። ከደረጃው ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ የከበረ ፡ የብረት ፡ ልብስ ፡ የለበሰ ፡ ጦረኛ ፡ አንድ ፡ የጸሎት ፡ መጽሐፍ ፡ ገልጦ ፡ ይዞ ፡ ቆሞአል ። እሱም ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ በደከሙት ፡ ዓይኖቹ ፡ ሲመለከታቸው ፡ ታታርዋ ፡ ቀረብ ፡ ብላ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ነገረችውና ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ጸሎት ፡ መጽሐፉ ፡ አቀረቀረ ። ሰፊ ፡ ከሆነው ፡ ከመጀመሪያው ፡ አዳራሽ ፡ ሲገቡ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ከፖሊሶች ፡ መኳንንት ፡ በማይለየው ፡

6—401

ክብርና ፡ ወግ ፡ መሠረት ፡ ወታደሮች ፡ ጋሻ ፡ ጃግሬዎችና ፡ ሌሎችም ፡ አሽከሮች ፡ በየስፍራው ፡ ግድግዳውን ፡ ተደግፈው ፡ ተቀምጠው ፡ አዳራሹን ፡ ሞልተውታል ። ነዶ ፡ ያለቀ ፡ ሻማ ፡ ሽታ ፡ ይሸታል ። ሁለት ፡ ሻማዎች ፡ ደግሞ ፡ የሰው ፡ ቁመት ፡ በሚያህል ፡ የሻማ ፡ ማስቀመጫ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የጠዋቱ ፡ ብርሃን ፡ በመስኮት ፡ ቢገባ ፡ አሁንም ፡ እንደበሩ ፡ ናቸው ።

አንድሬይ ፡ በተዋበ ፡ ቅርጻቅርጽ ፡ የተሠራ ፡ ማንቃ ፡ ወዳለው ፡ ሰፊ ፡ በር ፡ ሲያመራ ፡ ታታርዋ ፡ የልብሱን ፡ ጫፍ ፡ ጐተተችና ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ ያለች ፡ አንዲት ፡ ትንሽ ፡ በር ፡ አመለከተችው ። በዚችም ፡ በር ፡ አልፈው ፡ ከአንድ ፡ ክፍል ፡ ሲደርሱ ፡ አንድሬይ ፡ ክፍሉን ፡ በመደነቅ ፡ እየተገላመጠ ፡ ያስተውል ፡ ጀመር ። በመስኮቱ ፡ መዝጊያ ፡ ጭላንጭሎች ፡ የሚገባው ፡ ጨረር ፡ ድምቅ ፡ ቀይ ፡ የሆነውን ፡ መጋረጃና ፡ እንዲሁም ፡ ግድግዳው ፡ ላይ ፡ የተሰቀለ ፡ አንድ ፡ ሥዕል ፡ አጉልቶ ፡ ያሳያል ። ታታርዋ ፡ አንድሬይን ፡ እዚያው ፡ እንዲቆይ ፡ ምልክት ፡ ሰጠችውና ፡ በሩን ፡ ከፍታ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ክፍል ፡ ስትገባ ፡ ከወዲያኛው ፡ ክፍል ፡ የሚመጣ ፡ የሻማ ፡ ብርሃን ፡ ታየው ። ወዲያውም ፡ የለሰለሰ ፡ የሹክሹክታ ፡ ድምጽ ፡ ሲሰማ ፡ ጊዜ ፡ ልቡ ፡ ተሸበረ ። ገርበብ ፡ ባለው ፡ መዝጊያ ፡ ረጅም ፡ ያማረ ፡ ጠጉር ፡ በትከሻዋ ፡ ላይ ፡ የተንዠረገገ ፡ የአንድ ፡ የተዋበች ፡ ሴት ፡ ቅርጽ ፡ ታየው ። ወዲያው ፡ ታታርዋ ፡ ተመለሰችና ፡ አስገባችው ። እሱ ፡ ግን ፡ እንዴት ፡ እንደገባና ፡ በሩም ፡ ከኋላው ፡ እንዴት ፡ እንደተዘጋ ፡ በፍጹም ፡ ትዝ ፡ አይለውም ።

በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ ሻማዎች ፡ ይበራሉ ። በአንድ ፡ ሥዕል ፡ አጠገብም ፡ የሚበራ ፡ አንድ ፡ ኩራዝ ፡ አለ ። በሥዕሉ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ለጸሎት ፡ መንበርከኪያ ፡ ደረጃዎች ፡ ያሉት ፡ ረጅም ፡ ጠረጴዛ ፡ ይታያል ። አንድሬይ ፡ እነዚህን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ለመመልከት ፡ ስሜትም ፡ አልነበ



ረው ። ዘወር ፡ ሲል ፡ አንድ ፡ ሴትዮ ፡ ቆማ ፡ አየ ። ለመራመድ ፡ አስባ ፡ እዚያው ፡ ደርቃ ፡ የቀረች ፡ በድንገት ፡ ወደ ፡ ድንጋይ ፡ የተለወጠች ፡ ትመስላለች ። ወደሱ ፡ ልትዘል ፡ ስትል ፡ ሰውነትዋን ፡ በግድ ፡ ገትታ ፡ ያቆመችው ፡ ስትመስል ፡ እሱም ፡ እንደዚሁ ፡ በመገረም ፡ ደንዝዞ ፡ ከፊትዋ ፡ ቆሞአል ። አሁን ፡ እንደሚያያት ፡ ሆና ፡ አገኛታለሁ ፡ ብሎ ፡ አላሰበም ፡ ነበር ፤ ተለውጣለች ፡ ቀድሞ ፡ ያወቃት ፡ ልጃገረድ ፡ አይደለችም ። አሁን ፡ የቀድሞው ፡ መልኳ ፡ ምንም ፡ አይታይም ። ከቀድሞው ፡ ይልቅ ፡ አሁን ፡ በአጠፌታ ፡ የበለጠች ፡ ቆንጆና ፡ በውበትዋ ፡ የምትማርክ ፡ ሆናለች ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በጅምር ፡ እንዳለ ፡ ነገር ፡ ነበረች ፡ አሁን ፡ ግን ፡ አዋቂ ፡ ሠዓሊ ፡ ለመጨረሻው ፡ ጊዜ ፡ በጠቢብ ፡ ብሩሹ ፡ ነካክቶ ፡ ያስተካከላት ፡ ግሩም ፡ ሥዕል ፡ መስላለች ። ቀድሞ ፡ ቀበጥ ፡ ብትሆንም ፡ ደስ ፡ የምትል ፡ ልጃገረድ ፡ ነበረች ። አሁን ፡ ግን ፡ ውበትዋ ፡ ያበበ ፡ ሙሉ ፡ ሴት ፡ ናት ። ዓይኖችዋ ፡ በበሰለ ፡ ስሜት ፡ ያበራሉ ። ይህም ፡ እንዲያው ፡ የስሜት ፡ ምልክት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ስሜት ፡ ራሱ ፡ በሙሉ ፡ መልኩ ፡ ነው ። ገና ፡ ያልደረቀው ፡ የእንባዋ ፡ እርጥበት ፡ ለዓይኖችዋ ፡ ልዩ ፡ መልክ ፡ ሰጥቶት ፡ ይታያል ። ደረትዋ ፤ አንገትዋና ፡ ትከሻዋ ፡ ከሙሉ ፡ ውበት ፡ ልክ ፡ ደርሰዋል ። ቀድሞ ፡ በፊትዋ ፡ ይበተን ፡ የነበረው ፡ በስሱ ፡ ጥቅልል ፡ ጥቅልል ፡ ያለው ፡ ጠጉርዋ ፡ አሁን ፡ በብዛት ፡ አምሮ ፡ ግማሹ ፡ ተጐንጉኖ ፡ የቀረው ፡ በደረትዋ ፡ ወርዶ ፡ እስከ ፡ ጭንዋ ፡ ድረስ ፡ ተንዠርጐዋል ። በጠቅላላው ፡ መላው ፡ መልኳ ፡ ተለውጦአል ። አእምሮውን ፡ ሲያስጨንቀው ፡ ከኖረው ፡ መልኳ ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ቢፈልግ ፡ አንድም ፡ አላገኘም ። የፊትዋ ፡ መገርጣት ፡ አስደናቂውን ፡ ውበትዋን ፡ ምንም ፡ አላበላሸውም ። እንዲያውም ፡ አስደናቂ ፡ ተጨማሪ ፡ ለዛ ፡ ሰጥቶታል ። አንድሬይ ፡ በፍጹም ፡ ተማርኮ ፡ እፊትዋ ፡ ቆሞ ፡ ቀረ ። እሱዋም ፡ የጐልማሳነትን ፡ ሙሉ ፡ ውበት ፡ ተጐናጽፎ ፡ እፊ

ትዋ ፡ የቆመውን ፡ ኮዛክ ፡ በማየትዋ ፡ የተገረመች ፡ ትመስላለች ። ሃር ፡ የመሰሉት ፡ ቅንድቦቹ ፡ ቀስት ፡ መስለው ፤ ጸሐይ ፡ የጠገቡት ፡ ጉንጮቹ ፡ የወጣትነት ፡ ወዝ ፡ ይነበብባቸዋል ። ገና ፡ የበቀለው ፡ የጐልማሳነት ፡ ጥቁር ፡ ጢሙ ፡ እንደ ፡ ሃር ፡ የለሰለሰ ፡ ነው ።

እንደ ፡ ብር ፡ ቃጨል ፡ የጠራው ፡ ድምጽዋ ፡ እየተንቀጠቀጠ ፤ «ቸሩ ፡ መኳንንት ፡ ሆይ ፤ ላመሰግንህ ፡ አቅም ፡ ያንሰኛል ። ዋጋህን ፡ ሊከፍልህ ፡ የሚችለው ፡ አምላክ ፡ ብቻ ፡ ነው ። እኔ ፡ አንዲት ፡ ደካማ ፡ ሴት ፡ ነኝ ፡…» አለችውና ፡ ዓይኖቿን ፡ አቀረቀረች ። የተዋበው ፡ ፊቷም ፡ በማቀርቀር ፡ ደፋ ፡ ሲል ፡ የሃፍረት ፡ ቅላት ፡ ለብሶ ፡ ነበር ። አንድሬይ ፡ መናገር ፡ እንኳን ፡ ተሳነው ። በልቡ ፡ የሚያስጨንቀውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ሊገልጽላት ፡ ተመኘ ፤ ግን ፡ አልቻለም ። ምላሱ ፡ እንደታሰረና ፡ ከልሳኑም ፡ ድምጽ ፡ እንደማይወጣ ፡ ተሰማው ። በተማሪ ፡ ቤትና ፡ እንደ ፡ ዘላን ፡ ኑሮ ፡ ባለው ፡ በዘመቻ ፡ ኑሮ ፡ ላደገው ፡ ለእሱ ፡ እንዲህ ፡ ላለው ፡ ንግግር ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ የማይቻለው ፡ መሆኑን ፡ በመገንዘብ ፡ የኮዛክነት ፡ ተፈጥሮውን ፡ ረገመ ።

ወዲያው ፡ ታታሩዋ ፡ ገባች ። የመጣውን ፡ ዳቦ ፡ ቆራርጣ ፡ በወርቅ ፡ ሳህን ፡ ላይ ፡ አድርጋ ፡ ለእመቤቷ ፡ አቀረበች ። ውቢቱ ፡ ወይዘሮም ፡ በፊት ፡ ገረድዋን ፤ ከዚያም ፡ ዳቦውን ፡ ከተመለከተች ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አንድሬይ ፡ ቀና ፡ አለች ። የደረሰባት ፡ ሥቃይና ፡ ልትገልጸው ፡ ያልቻለችው ፡ ስሜት ፡ ሁሉ ፡ በዓይኖቿ ፡ ላይ ፡ ይነበብ ፡ ነበር ። አንድሬይም ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ ከንግግር ፡ ሊረዳው ፡ ከሚችለው ፡ ይበልጥ ፡ ተረዳው ። ወዲያውም ፡ ከልቡ ፡ እየቀለለው ፡ ሄደ ፤ ሰውነቱ ፡ ሁሉ ፡ ከእስራት ፡ እንደተፈታ ፡ ሆኖ ፡ ተሰማው ። በአንድ ፡ ባልታወቀ ፡ እጅ ፡ እንደታሠረ ፡ ሆኖ ፡ የነበረው ፡ ስሜቱ ፡ ሁሉ ፡ ነፃ ፡ ሆኖ ፡ በማይገቱ ፡ ቃላት ፡ እየጐረፈ ፡ ለመውጣት ፡ ጓጓ ። ግን ፡ ወዲያው ፡ ያቺ ፡ ቆንጆ ፡ ልጅ ፡ ድንገት ፡ ወደ ፡



ታታሩዋ ፡ ዘወር ፡ አለችና ፡ «እናቴስ? ለሷም ፡ ውስደሽላታል?» ብላ ፡ ጠየቀች ።

ታታሩዋም ፤ «ተኝተዋል ፡» አለች ።

«አባቴስ?»

«አዎ ፡ ወስጀላቸዋለሁ ። መኰንኑን ፡ ለማመስገን ፡ እኔው ፡ እራሴ ፡ እመጣለሁ ፡ ብለዋል ።»

ከዚያ ፡ ልጅቷ ፡ አንድ ፡ ቁራሽ ፡ ዳቦ ፡ አነሳችና ፡ ሉል ፡ በመሳሰሉት ፡ ጣቶቿ ፡ ሰበር ፡ አድርጋ ፡ ስትጐርስ ፡ አንድሬይ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ በማይባል ፡ ደስታ ፡ ተመልቶ ፡ ይመለከታት ፡ ነበር ። ግን ፡ ወዲያው ፡ ያ ፡ በረሃብ ፡ ያበደው ፡ ሰውየ ፡ ቁራሽ ፡ ዳቦ ፡ በመዋጥ ፡ የደረሰበት ፡ ሥቃይ ፡ ትዝ ፡ አለውና ፡ በድንጋጤ ፡ ጠውልጐ ፤ «በቃ! ብዙ ፡ ቀን ፡ እህል ፡ ስላልቀመስሽ ፡ አሁን ፡ ዳቦው ፡ መርዝ ፡ ይሆንብሻል ፡» አለና ፡ እጇዋን ፡ ያዛት ። እሷም ፡ ወዲያው ፡ ዳቦውን ፡ አስቀመጠችና ፡ እንደታዛዥ ፡ ሕፃን ፡ ቀና ፡ ብላ ፡ ዓይን ፡ ዓይኑን ፡ ትመለከተው ፡ ጀመር ። እንዲያ ፡ ባለው ፡ ሰዓት ፡ በአንዲት ፡ ቆንጆ ፡ ወጣት ፡ ዓይኖች ፡ ላይ ፡ ምን ፡ እንደሚነበብና ፡ ዓይኖቿን ፡ የሚመለከተውም ፡ ጐልማሳ ፡ ስሜት ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ለመግለጽ ፡ ምንም ፡ የሥዕል ፡ ቀለማት ፡ ወይም ፡ የንግግር ፡ ቃላት ፡ አይገኙለትም ።

አንድሬይ ፡ ልቡ ፡ ነፍሱም ፡ መላ ፡ ተፈጥሮው ፡ በስሜት ፡ ገንፍሎ ፡ እንዲህ ፡ አላት ፤

«ንግሥት ፡ ሆይ! ምን ፡ የምትሽው ፡ ነገር ፡ አለ? ምን ፡ የሚያሰኝሽ ፡ ነገር ፡ አለ? እኔን ፡ አዝዥኝ! በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሊፈጸም ፡ የማይቻል ፡ ተግባር ፡ ፈጽም ፡ ብለሽ ፡ አዝዥኝ! ከሞት ፡ የሚያደርሰኝ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳን ፡ አደርገዋለሁ! አዎ ፡ አደርገዋለሁ! ለአንቺ ፡ ሲሉ ፡ መሞት ፡ እጅግ ፡ ጣፋጭ ፡ ሞት ፡ እንደሆነ ፡ በቅዱስ ፡ መስቀል ፡ ስም ፡ እምላለሁ ! የግሌ ፡ የሆኑ ፡ ሶስት ፡ መንደሮች ፡ አሉኝ ። የአባቴ ፡ የፈረስ ፡ መንጋ ፡ ግማሹ ፡ እናቴ ፡ ይዛው ፡ የገባችው ፡ ሃብት ፡ በሙሉ ፡

ከአባቴ ፣ ደብቃ ፣ የምታስቀምጠው ፡ እንኳን ፣ ሳይቀር ፡ ሁሉም ፣ የኔ ፣ ነው! የኔን ፣ ያህል ፣ የጦር ፣ መሣሪያ ፣ ያለው ፡ ማንም ፣ ከዛክ ፣ አይገኝም ። የጐራዴዬ ፣ እጀታ ፣ ብቻ ፣ አንድ ፡ መንጋ ፣ ምርጥ ፣ ፈረሶችና ፣ ሶስት ፣ ሺ ፣ በጐች ፣ ሊገዛልኝ ፡ ይችላል ። ይህን ፣ ሁሉ ፣ ከአንቺ ፡ አፍ ፣ በሚወጣ ፣ አንድ ፡ ቃል ፣ ወይም ፣ በተዋበው ፣ ጥቁር ፡ ቅንድብሽ ፣ ንቅናቄ ፣ ባሕር ፣ ውስጥ ፣ ልጥለው ፤ ላቃጥለው ፡ ዝግጁ ፣ ነኝ! ምናልባት ፡ ንግግሬ ፣ ያለ ፣ ጊዜውና ፣ ያለ ፣ ሥፍራው ፣ የተደረገ ፣ የሞኝ ፣ ንግግር ፣ ይሆናል ። በተማሪ ፣ ቤትና ፣ በዛፖሮዥያኖች ፣ መካከል ፣ ኖሬ ፣ እንደ ፣ ነገሥታት ፣ እንደ ፣ ልዑላንና ፣ እንደ ፡ ጨዋ ፣ መኳንንት ፣ ልናገር ፣ አልችልም ። አንቺ ፣ ከሁላችንም ፣ የተለየሽ ፣ የእግዚአብሔር ፣ ፍጥረት ፣ እንደሆንሽ ፣ አውቃለሁ ። ሌሎች ፣ የጨዋ ፣ ሚስቶችና ፣ ልጆች ፣ ሁሉ ፣ ከአንቺ ፣ በታች ፣ ናቸው ። እኛ ፣ ባሮችሽ ፣ ለመሆን ፣ እንኳን ፣ አንበቃም ። አንቺን ፣ ለማገልገል ፣ የሚገባቸው ፡ የሰማይ ፡ መላዕክት ፣ ብቻ ፣ ናቸው ።»

ልጅቷ ፣ አካላቷ ፣ ሁሉ ፣ ጆሮ ፣ ሆኖ ፣ አንድም ፣ ቃል ፡ ሳያመልጣት ፣ ኃይለኛ ፣ የወጣት ፣ መንፈስ ፣ እንደመስታዋት ፣ የሚያሳየውን ፣ ይህን ፣ ንግግር ፣ ከፍ ፣ ባለ ፣ አድናቆት ፣ ታደምጥ ፣ ነበር ። የተዋበውን ፣ ፊቷን ፣ ወደሱ ፣ ቀና ፡ አድርጋ ፣ ግንባሯ ፣ ላይ ፣ የተበታተነውን ፣ ጸጉርዋን ፣ ወደኋላ ፣ አደረገችና ፣ ብዙ ፣ ስታስተውለው ፣ ቆየች ። ልትናገርም ፣ አስባ ፣ ወዲያው ፣ ይህ ፣ ወጣት ፣ ዛፖሮዥያን ፣ መሆኑንና ፣ አባቱ ፣ ወንድሞቹና ፣ ሃገሩ ፣ ለበቀል ፣ ታጥቀው ፣ የተሰለፉ ፡ መሆናቸውን ፤ ከተማዋን ፣ የከበቧት ፣ ዛፖሮዥያኖች ፣ ጨካኞች ፣ መሆናቸውንና ፣ የከተማው ፣ ኑዋሪዎች ፣ ሁሉ ፣ በአሰቃቂ ፣ የሞት ፣ ጥላ ፣ ሥር ፣ እንዳሉ ፣ በማስታወስ ፣ ምላሷን ፡ ሰበሰበች ። በዚህን ፣ ጊዜ ፣ ሳታስበው ፣ በዓይኖቿ ፣ እንባ ፡ ተንቀረዘዘና ፣ በጥልፍ ፣ ያጌጠ ፣ አንድ ፣ የሃር ፣ መሐረብ ፡ አንስታ ፣ ከዓይኗ ፣ ስታስጠጋው ፣ መሐረቡ ፣ ወዲያው ፣ ራ



ሰ ። በሃዘን ፡ ስትንሰቀሰቅም ፡ እሱ ፡ እንዳያያት ፡ መርዘኛ ፣ እባብ ፡ እንደነደፋት ፣ ሁሉ ፣ የተዋበውን ፣ ራሷን ፣ ወደኋላ ፣ ዘንበል ፣ አድርጋ ፣ በረዶ ፣ በመሰሉት ፣ ጥርሶቿም ፣ ከንፈሯን ፡ ነክሳ ፣ ዓይኖቿን ፣ በመሐረቡ ፣ ሸፍና ፡ ብዙ ፣ ቆየች ።

«አንድ ፣ ቃል ፣ ብቻ ፣ እንኳን ፣ ተናግረሽ ፡ ድምጽሽን ፡ ልስማው!» አለና ፣ አንድሬይ ፣ ለስላሳውን ፣ እጅዋን ፣ በእጁ ፡ ጨበጠ ። በዚህን ፣ ጊዜም ፣ አንድ ፣ ዓይነት ፡ የሚያንገበግብ ፡ እሳት ፣ በደም ፣ ሥሩ ፣ ሁሉ ፣ ተሰራጭቶ ፣ እጅዋን ፣ ጠበቅ ፣ አድርጐ ፣ ጨበጠው ።

እሷ ፣ ግን ፣ መሐረቡን ፣ ከፊቷ ፣ ሳታነሳ ፤ ሳትንቀሳቀስ ፣ ዝም ፣ አለች ።

«ለምን ፣ ተከዝሽ? ንገሪኝ ፤ ለምንድን ፣ ነው ፣ ያዘንሽው?» አላት ።

በዚህን ፣ ጊዜ ፣ መሐረቡን ፣ ከፊቷ ፣ አንስታ ፣ ዓይኖቿ ፣ ላይ ፣ የተበተነውን ፣ ረጅም ፣ ጸጉሯን ፣ ወደ ፣ ጐን ፣ መለስ ፣ አደረገችና ፤ ቀስ ፣ ባለ ፣ ድምጽ ፤ ሃዘን ፣ የተመላ ፣ ንግግር ፣ ጀመረች ፤

«በዕውነት ፣ እኔ ፣ ሊታዘንልኝ ፣ የሚገባ ፣ ፍጥረት ፣ አይደለሁምን? የወለደችኝስ ፣ እናቴ ፣ ምንኛ ፣ ልታዝን ፣ ይገባታል ፣ ተፈጥሮዬ ፣ ሁሉ ፣ መሪር ፣ ነው ። ወይ ፣ ክፉ ፣ ዕድሌ! ያለርኅራኄ ፣ የምታሰቃየኝ ፣ አንተ ፣ አይደለህምን? ወይ ፣ ክፉ ፣ ዕድሌ! ከፍተኛ ፣ መኳንንት ፤ ሃብታም ፣ ጨዋዎች ፤ የውጭ ፣ መንግሥታት ፣ ባላባቶች ፣ አንተው ፣ አምጥተህ ፡ ከእግሬ ፣ ሥር ፣ ጣልህልኝ! ሁሉም ፣ ወደዱኝ ። ከነሱም ፣ ማንኛቸውንም ፣ ወደድሁህ ፣ ብለው ፣ ታላቅ ፣ ክብር ፣ አድርጐ ፣ በቆጠረው ፣ ነበር ። ትንሽ ፣ ምልክትም ፣ ባሳየው ፣ ኖሮ ፤ ከነሱ ፣ መካከል ፣ በትውልድም ፣ በውበትም ፣ የላቀው ፣ አንዱ ፣ የኑሮ ፣ ጓደኛዬ ፣ በሆነ ፣ ነበር ። ነገር ፣ ግን ፣ ጨካኙ ፡ ዕድሌ ፣ ልቤን ፣ ከሃገራችን ፣ ስመጥሩ ፣ መኳንንት ፡ ሳይሆን ፡ በአንድ ፣ እንግዳ ፣ ሰው ፤ በጠላታችን ፣ እንዲማረክ ፡ አደረ

ግኸው ። ምን ፡ ኃጢአት ፡ ሠርቼ ፡ ይሆን ፤ ቅድስት ፡ የአምላክ ፡ እናት ፡ ሆይ! ምን ፡ ኃጢአት ፡ ምን ፡ ከባድ ፡ ወንጀል ፡ ብሠራ ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ በጭካኔ ፡ የፈረድሽብኝ? ጊዜዬን ፡ ሁሉ ፡ በተትረፈረፈ ፡ የሃብት ፡ ኑሮ ፡ አሳለፍሁት ። ማለፊያ ፡ ምግቦችና ፡ ጣፋጭ ፡ ወይኖች ፡ ሁሉ ፡ የኔ ፡ ነበሩ ። ታዲያ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ለምን ፡ ኖሩዋል? መጨረሻው ፡ ምን ፡ ሊሆን? በመንግሥቱ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ የመጨረሻው ፡ መናጢ ፡ ድሃ ፡ እንኳን ፡ የማይሞተውን ፡ አሰቃቂ ፡ ሞት ፡ እንድሞት ፡ ነው? ደግሞ ፡ ይኸው ፡ አሰቃቂው ፡ መጨረሻዬ ፡ ሳያንሰኝ ፤ ሃያ ፡ ጊዜ ፡ ተደጋግሞም ፡ ቢሆን ፡ በሥቃይ ፡ ልሞትላቸው ፡ የምመኘውን ፡ አባትና ፡ እናቴን ፡ ከኔ ፡ ቀድመው ፡ በሥቃይ ፡ ሲሞቱ ፡ ልመለከት ፡ ነው ። ይህም ፡ ሳይበቃ ፡ ቀርቶ ፡ ይኸው ፡ ተጨማሪ ፡ ሥቃይ ፡ ደረሰብኝ ። በዚች ፡ በመጨረሻዬ ፡ ሰዓት ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በሕልሜ ፡ እንኳን ፡ ታይቶኝ ፡ የማያውቅ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ንግግር ፡ ለመስማትና ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ፍቅር ፡ ለማየት ፡ በቅቼ ፡ በንግግሩ ፡ ልቤ ፡ እንዲጨነቅና ፡ መሪሩ ፡ ዕጣዬ ፡ የባሰ ፡ መሪር ፡ እንዲሆን ፡ ሆንሁ ። አሟሟቴ ፡ የበለጠ ፡ መሪር ፡ ሞት ፡ እንዲሆን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ጸጸት ፡ ደረሰብኝ ። ስሞትም ፤ ክፉው ፡ ዕድሌ ፡ ሆይ ፡ እነሆ ፡ እረግምሃለሁ ። የተቀደስሽ ፡ የአምላክ ፡ እናት ፡ ሆይ ፡ ኃጢአቴን ፡ ይቅር ፡ በይኝና ፡ አንቺንም ፡ እንዲሁ ፡ እረግምሻለሁ!»

ይህንን ፡ ተናግራ ፡ ዝም ፡ ስትል ፡ የመጨነቅና ፡ የተስፋ ፡ መቁረጥ ፡ መልክ ፡ ፊቷን ፡ አለበሰው ። በሃዘን ፡ ከተኮሰተሩት ፡ ቅንድቦቿና ፡ ከአቀረቀሩት ፡ ዓይኖቿ ፡ ጀምሮ ፡ በደማም ፡ ጉንጮቿ ፡ ላይ ፡ እስከሚወርዱት ፡ የእንባ ፡ ዘለላዎች ፡ ድረስ ፡ ጠቅላላው ፡ ገጽዋ ፤ «ከእንግዲህ ፡ የደስታ ፡ መንፈስ ፡ አይገኝም!» የሚል ፡ ቃል ፡ የተጻፈባቸው ፡ ይመስሉ ፡ ነበር ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ አንድሬይ ፡ እንዲህ ፡ አላት ፤

«እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ በፍጹም ፡ ተሰምቶ ፡ አይታወቅም! በፍጹም ፡ ሊሆን ፡ አይችልም! የሴቶች ፡ ሁሉ ፡ የበላይ ፡



የሆነች ፡ ቆንጆ ፡ የተፈጠረችው ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ማናቸውም ፡ ጥሩ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ቅድስት ፡ አድርጐ ፡ እንዲሰግድላት ፡ ሲሆን ፡ እንዲህ ፡ ባለ ፡ መሪር ፡ ዕድል ፡ ልትሠቃይ ፡ አትችልም! የለም ፤ አትሞችም! በትውልዴና ፡ እንዲሁም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በምወዳቸው ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ እምላለሁ ፤ በፍጹም ፡ አትሞችም! ግን ፡ ቢሆንም ፡ እንኳን ፡ ይህንን ፡ ጨካኝ ፡ ዕድል ፡ ኃይልና ፡ ድፍረት ፡ ወይም ፡ ጸሎት ፡ ሊያሸንፈው ፡ ካልቻለ ፡ አብረን ፡ እንሞታለን ፤ ከአንቺም ፡ ቀድሜ ፡ እኔ ፤ እፊትሽ ፤ ከተዋቡት ፡ እግሮችሽ ፡ ሥር ፡ እሞታለሁ ። ሊነጥለን ፡ የሚችለው ፡ ሞት ፡ ብቻ ፡ ነው ።»

እሷም ፡ የተዋበውን ፡ አንገቷን ፡ በእርጋታ ፡ እየነቀነቀች ፡ እንዲህ ፡ አለችው ፤

«መኰንኔ ፡ ሆይ ፤ እኔንንም ፡ እራስህንም ፡ አታታልል ። እምነትህንና ፡ ያለብህን ፡ ግዴታ ፡ ስለማውቅ ፡ ልትወደኝ ፡ እንደማትችል ፡ በሃዘን ፡ ተገንዝቤያለሁ ። እኛ ፡ ጠላቶችህ ፡ ስንሆን ፤ አባትና ፡ ወገኖችህ ፡ ሃገርህም ፡ ይበልጡብሃል ።»

አንድሬይ ፡ ራሱን ፡ ነቀነቀና ፡ እንደ ፡ ረጅም ፡ ምሰሶ ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ቆሞ ፤ «ታዲያ ፡ አባቴ ፤ ወገኖቼ ፤ ሃገሬስ ፡ ለእኔ ፡ ምኖቼ ፡ ናቸው? ምርጫ ፡ ከመጣ ፤ ምንም ፡ ነገር ፤ ማንንም ፡ ሰው ፡ ለማወቅ ፡ አልፈልግም! ማንንም!» አለና ፡ በተለመደው ፡ የኰዛኮች ፡ የቆራጥነት ፡ አነጋገርና ፡ ድምጽ፤ «ኡክሬይን ፡ የኔ ፡ ሃገር ፡ ናት ፡ የሚል ፡ ማን ፡ ነው? ሃገሬ ፡ እንድትሆን ፡ ማን ፡ ነው ፡ የሰጠኝ? ሃገር ፡ ማለት ፡ ልባችን ፡ የሚጓጓለትና ፡ ከሁሉ ፡ አብልጠን ፡ የምንወደው ፡ ነገር ፡ ነው ። አንቺ ፡ …አዎ ፡ አንቺ ፡ ነሽ ፡ የኔ ፡ ሃገር! እንዲህ ፡ ያለችውን ፡ ሃገር ፡ በሕይወት ፡ እስካለሁ ፡ ድረስ ፡ በልቤ ፡ ተሸክሜያት ፡ እኖራለሁ ። ሊነጥቀኝ ፡ ቢሞክርም ፡ ማናቸውንም ፡ ኰዛክ ፡ እቋቋመዋለሁ! ለዚች ፡ ሃገር ፡ ያለኝን ፡ ንብረት ፡ ሁሉ ፡ ልፈታ ፡ ሃብቴንም ፡ ልበትን ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ!» አለ ።

ለአጭር ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ ደርቃ ፡ የተዋበች ፡ ሃውልት ፡ መስላ ፡ ከተመለከተችው ፡ በኋላ ፡ እንባዋ ፡ ይረግፍ ፡ ጀመር ። ከዚያም ፡ ዘልላ ፡ አንገቱን ፡ በረዶ ፡ በመሰሉት ፡ ክንዶቿ ፡ አቅፋ ፡ ጮኻ ፡ ተንሰቀሰቀች ።

ልክ ፡ በዚያ ፡ ሰዓት ፡ ከውጭ ፤ ራቅ ፡ ያለ ፡ የጫጫታና ፡ የጡሩምባ ፡ ድምጽ ፡ ተሰማ ። ለአንድሬይ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ድምጽ ፡ አልተሰማውም ። ለእሱ ፡ የሚሰማው ፤ የተዋቡት ፡ ከንፈሮቿና ፡ ሞቃት ፡ ትንፋሿ ፤ ጉንጩን ፡ የሚነካው ፡ እንባዋ ፤ ፊቱን ፡ ያለበሰው ፡ ሐር ፡ የመሰለው ፡ ጸጉሩዋ ፡ መዓዛ ፡ ብቻ ፡ ነበር ።

ወዲያው ፡ ታታሩዋ ፡ ገረድ ፤ «ዳንን! ዳንን!» በማለት ፡ በደስታ ፡ እየጮኸች ፡ ገባችና ፤ «ወታደሮቻችን ፡ ከተማ ፡ ገብተዋል ። እህልና ፡ እንዲሁም ፡ የተማረኩ ፡ ዛፖሮዥያኖችን ፡ ይዘው ፡ መጥተዋል ፡» አለች ።

ነገር ፡ ግን ፡ የተቃቀፉት ፡ ልጂቱና ፡ ጐልማሳው ፤ የማን ፡ ወታደሮች ፡ ከተማ ፡ እንደገቡ ፤ ምንስ ፡ ይዘው ፡ እንደመጡ ፤ የተማረኩት ፡ ዛፖሮዥያውያኖችስ ፡ እነማን ፡ እንደሆኑ ፡ በፍጹም ፡ አላዳመጡም ። አንድሬይ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ በማይገኝ ፡ የደስታ ፡ ስሜት ፡ ተውጦ ፡ ጉንጩን ፡ የሚነካኩትን ፡ ጣፋጭ ፡ ከንፈሮች ፡ ይስም ፡ ጀመር ። እሷም ፡ መልሳ ፡ ትሰመው ፡ ነበር ። በዚያ ፡ ሰዓት ፡ ሁለቱንም ፡ የተሰማቸው ፡ ስሜት ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ በሕይወቱ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ የሚሰጥ ፡ ስሜት ፡ ነው ።

ኮዛኩ ፡ ከእንግዲህ ፡ ጠፋ ፡ ማለት ፡ ነው! ከኮዛክ ፡ መኳንንትነት ፡ ኮበለለ! ከእንግዲህ ፡ ዛፖሮዥዬን ፤ የአባቱን ፡ መንደሮች ፤ የአምላኩንም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አያይም! ኡክሬይንም ፡ ሊጠብቋት ፡ ከታጠቁት ፡ ልጆቿ ፡ ሁሉ ፡ የላቀውን ፡ ጀግና ፡ ልጅዋን ፡ ከእንግዲህ ፡ አታየውም ። ሽማግሌው ፡ ታራስ ፡ ከሸበተው ፡ ጸጉሩ ፡ አንድ ፡ ጭብጥ ፡ ነጭቶ ፡ እንዲህ ፡ የሚያሳፍረውን ፡ ልጁን ፡ የወለደበትን ፡ ቀን ፡ ይረግማል ።



## ምዕራፍ ፡ ሰባት ።

ጩኸትና ፡ ሽብር ፡ የዛፖሮዥያንን ፡ ሠፈር ፡ መላው ። በመጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ወታደሮቹ ፡ እንዴት ፡ አልፈው ፡ ከከተማው ፡ እንደገቡ ፡ ማንም ፡ ሊያውቅ ፡ አልቻለም ። በኋላ ፡ ግን ፡ በከተማው ፡ የስርቆሽ ፡ በር ፡ ሠፍሮ ፡ የነበረው ፡ የፔሬያስላቭ ፡ መንደር ፡ ጦር ፡ ጥምብዝ ፡ ብሎ ፡ ሰክሮ ፡ ስለነበር ፡ አንዳቸውም ፡ ሳይሰሙ ፡ የጠላት ፡ ወታደሮች ፡ ደርሰው ፤ ግማሻቸውን ፡ ገድለው ፡ የተረፉትን ፡ ማርከው ፡ መሄዳቸው ፡ ታወቀ ። ጫጫታውን ፡ የሰሙ ፡ የጐረቤት ፡ ሰፈር ፡ ዛፖሮዥያኖች ፡ መሳሪያቸውን ፡ ይዘው ፡ ሲነሱ ፡ ወታደሮቹ ፡ ከተማውን ፡ ገብተው ፡ ኖሮ ፡ ያለ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ተሯሩጠው ፡ የተከተሉትንም ፡ እንቅልፍ ፡ ያልለቀቃቸው ፡ ኮዛኮች ፡ የወታደሮቹ ፡ የደጀን ፡ ጦር ፡ ተታኩሶ ፡ መለሳቸው ።

ወዲያው ፡ ኮሼቮይው ፡ ሁሉም ፡ እንዲሰበሰቡ ፡ አዝዞ ፡ ሁሉም ፡ ተሰበሰቡና ፡ ባርኔጣቸውን ፡ አውልቀው ፡ ዙሪያውን ፡ በጸጥታ ፡ ሲቆሙ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«ዛሬ ፡ ሌሊት ፡ የደረሰውን ፡ አያችሁ ፡ ወንድሞቼ ። ስካር ፡ ምን ፡ እንዳደረሰ ፡ ተመለከታችሁ! ጠላት ፡ እንዴት ፡ እንዳሳፈረን ፡ ይኸው ፡ አያችሁ ። ሁልጊዜ ፡ ይኸው ፡ ናችሁ! የሚሰጣችሁ ፡ ቮድካ ፡ ትንሽ ፡ በርከት ፡ ካለላችሁ ፡ ትጋቱ ፡ ትጋቱና ፡ የክርስቲያን ፡ ወታደሮች ፡ ጠላት ፡ ሱሪያችሁን ፡ መጐተት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ፊታችሁ ፡ ላይ ፡ ቢያነጥስባችሁም ፡ አትሰሙትም!»

ኮዛኮቹ ፡ ሁሉ ፡ ጥፋታቸውን ፡ በመገንዘብ ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ቆሙ ። የኔዛማይ ፡ መንደር ፡ አለቃ ፡ ኩኩቤንኮ ፡ ብቻ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መልስ ፡ ሰጠ ፤

«ቆይ ፡ እስቲ ፡ ባትኮ! ምንም ፡ እንኳን ፡ ኮሼቮይው ፡ ሲናገር ፡ ማቋረጥ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ቢሆንም ፤ ጉዳዩ ፡ አንተ ፡ እንዳልኸው ፡ ባለመሆኑ ፡ ልናገር ፡ ይገባኛል ። ይህን ፡ የክርስ